ጅማ ዩኒቨርሲቲ

የሶሻል ሳይንስና ሂዩማኒቲስ ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ-ፅሑፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል

ድኅረ ምረቃ መርሀ ግብር

# የፎክሎራዊ ጉዳዮች ፋይዳ ትንተና በመኤኒት እና በእምቢታ ታሪካዊ ልቦለድ ተተኳሪነት

በ

ዘይባ ሁሴን

በኢትዮጵያ ሥነ-ፅሁፍና ፎክሎር ለሁለተኛ ዲግሪ

ማሟያነት የቀረበ ጥናት

2012 ዓ.ም

ጅማ

ጅማ ዩኒቨርሲቲ

የሶሻል ሳይንስና ሂዩማኒቲስ ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ-ፅሑፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል

ድኅረ ምረቃ መርሀ ግብር

# የፎክሎራዊ ጉዳዮች ፋይዳ ትንተና *በመኤኒት እና በእምቢታ ታሪካዊ* ልቦለድ ተተኳሪነት

በ

ዘይባ ሁሴን

በኢትዮጵያ ሥነ-ፅሁፍና ፎክሎር ለሁለተኛ ዲግሪ

ማሟያነት የቀረበ ጥናት

አማካሪ

ማንያለዉ አባተ (ዶ/ር)ዋና

ሃብታሙ እንግዳው (ኤም. ኤ) (ረዳት)

2012ዓ.ም

ጅማ

# ምስጋና

ከሁሉ አስቀድሜ ለዚህ ያበቃኝን ፈጣሪዬን ከልቤ አመስግናለሁ፡፡ “አልሃምዱሊላህ!”፡፡በዚህ ጥናት ውስጥ በተለያየ መልኩ የበኩላቸውን ድጋፍ እና ትብብር ያደረጉልኝ ሰዎች ለሥራዬ መሳካት የነበራቸው ተሳትፎ የጎላ ነበር። ከእነዚህም ውስጥ ከፍተኛውን ድርሻ የተወጣችሁ በፎክሎርና በሥነ-ፅሁፍ የትምህርት ዘርፎች የተሻለ እውቀት እንዲኖረኝና በሁለቱ መካከል ያለውን ዝምድና በመጠቆም የድርሻዬን እንድወጣ ያገዛችሁኝ የኮርስ መምህሬ እናአማካሪዬ ዶክተር ማንያለው አባተ እንዲሁም ዶክተር ለማ ንጋቱ ላደረጋችሁልኝ በቃላት የማይገለፅ የእውቀትም ሆነ የሞራል ድጋፍ ከልብ የመነጨ ምሥጋናዬን አቀርባለሁ። ክፉ አይንካብኝ!፡፡ የጥናት ፅሁፌን በማረም ገንቢ አስተያየት ለለገስከኝ መምህር ሃብታሙ እንግዳው ምስጋናዬ ከልብ ነው።

ውድ እናቴ ወ/ሮ ፋጡማ ሃስን እና ኮልታፋዋ ልጄ ሒላል ቢኒያም ስጨነቅ ተጨንቃችሁ፤ ሳነብ ድምጻችሁን አጥፍታችሁና ተንከባክባችሁ ጥናቴን ለዚህ አብቅታችሁታልና ይሂውውጤቱ! ምስጋናዬ ይድረሳችሁ፡፡ በሌላኛውጎን ደግሞ በሚዛን ቴፒ ዩኒቨርሲቲ በቴፒ ግቢ በውጭና ህዝብ ግንኙነት ስራ ክፍል የምትገኙ ባልደረቦቼ መክያ ፤አሳዬና ደረጄ ለጥናቴ ጊዜ እንድሰጥ የኔንም ስራ እየሸፈናችሁ ቢሮዬን ዘግታችሁ ላለመረበሽ እየተንሾካሾካችሁ የምታወሩትን ሁሉ ሳስበው ለካስ ሰው አለኝ እንድል አድርጋችሁኛልና እናንተ መልካም ሰዎች ሁሌም ኑሩልኝ፡፡

## ማውጫ

**ርዕስ** **ገፅ**

ምስጋና ........................................................................................................................i

ሙዳዬ ቃላት ..............................................................................................................v

አጠቃሎ .......................................................................................................................vi

## ምዕራፍ አንድ

መግቢያ.........................................................................................................................1

1.1 ዳራ ..........................................................................................................................2

1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት..........................................................................................3

1.3 የጥናቱ የምርምር ጥያቄዎች ......................................................................................4

1.4 የጥናቱ ዓላማ ...........................................................................................................3

1.5 የጥናቱ ጠቀሜታ.........................................................................................................4

1.6 የጥናቱ ወሰን..............................................................................................................5

## ምዕራፍ ሁለት

ክለሳ ድርሳናት.............. ...................................................................6

2.1 ንድፈ ሃሳባዊ ቅኝት ........................................................................................6

2.1.1 የስነ-ፅሁፍ ምንነት ....... ...........................................................................6

2.1.1.1. የመባያ ጉዳይ በስነፅሁፍ ውስጥ.............................................................8

2.1.1.2 የዘመን መንፈስ በስነፅሁፍ ውስጥ ...........................................................9

2.1.2 የፎክሎር ምንነትና ምደባ ...........................................................................10

2.1.2.1 ሥነ ቃል ................. .................................................................................11

2.1.2.2. ሃገረሰባዊ ልማድ...... ................................................................................12

2.1.2.3. ቁሳዊ ባህል................ ..............................................................................13

2.1.3 ፎክሎርና ሥነ-ጽሁፍ... ..................................................................................13

2.1.3.1 ፎክሎር ለስነ-ፅሁፍ እድገት .......................................................................17

2.1.3.2 ሥነ-ፅሁፍ ለፎክሎር እድገት .......................................................................17

2.1.3.3 የጥናቱ ትወራ………… ......................................................................18

2.2 የተዛማጅ ስራዎች ቅኝት... ......................................................................22

ምዕራፍ ሶስት

የጥናቱ ዘዴና ንድፍ……………………………………………………28

3.1 የጥናቱ ዘዴና አካሄድ……. ......................................................................28

3.2 የመረጃ ምንጮች........... ......................................................................28

3.3 የናሙና አመራረጥ ዘዴ…......................................................................28

3.4 የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ......................................................................29

ምዕራፍ አራት

4.1 የእምቢታ እና የመኤኒትልቦለዶች አፅህሮተ ታሪክ......................................................31

4.1.1የእምቢታ ታሪካዊ ልቦለድ አፅህሮተ ታሪክ ...............................................31

4.1.2 የመኤኒት ልቦለድ አፅህሮተ ታሪክ ..........................................................33

4.2 የፎክሎራዊ ጉዳዮች ፋይዳ ትንተና በመኤኒትና እምቢታ ልቦለዶች.............................35

4.2.1 ሥነ-ቃል.................... ......................................................................36

4.2.1.1 እርግማንና መሃላ ..........................................................................36

4.2.1.2 ምርቃት .......................................................................................38

4.2.1.3 ምሳሌያዊና ፈሊጣዊ ንግግሮች ................................................41

4.2.1.4 ፉከራ .............................................................................................43

4.2.1.5 ቃል ግጥም ......................................................................................44

4.2.2 ሃገረሰባዊ ልማድ……......................................................................46

4.2.2.1 ሃገረሰባዊ እምነት..............................................................................46

4.2.2.2ክብረ በዓል…………… ......................................................................59

4.2.2.3 ሃገረሰባዊ ስያሜ ..............................................................................62

4.2.3 ቁሳዊ ባህል ................. ………………………………………………….66

4.2.3.1 ባህላዊ አልባሳትና ጌጣጌጦች ....................................................................67
4.2.3.2 ሃገረሰባዊ ምግብና መጠጥ ......................................................................68
4.2.3.3 ህዝባዊ ቦታዎች……… ......................................................................71
4.2.3.4 ሃገረሰባዊ ትዕምርት ......................................................................73

## ምዕራፍ አምስት

ማጠቃለያና ይሁንታ......................................................................87
5.1. ማጠቃለያ ......................................................................87
5.2 ይሁንታ......................................................................88
ዋቢዎች......................................................................91

## ሙዳዬ ቃላት

አንቂት፡- የጉራጊኛ ቃል ሲሆን ጥሬ ትርጉሙ የሴት ልጅ እርግማን ማለት ነው፡፡ ወንዶች ሴቶችን ፊትቼሻለሁ እስካላሉ ድረስ ሌላ ባል እንዳያገቡ የሚከለክል እርግማን ነው፡፡

አሻ፡- የመኤኒተኛ ቃል ሲሆን ትርጉሙም የገዳይ ቤተሰብ ለሟች ቤተሰብ በካሳነት የሚከፍሏት ሴት ልጅን ይወክላል፡፡

ጀፎረ፡- ቃሉ ጉራጊኛ ሲሆን ጥሬ ትርጉሙ በመንደርና መንደር መካከል የሚገኝ የጋራ አደባባይ ወይም የጋራ ባህላዊ አውራጎዳና ማለትነው፡፡

ዌየግ፡-በጉራጌ ማህበረሰብ ዘንድ ክብር ያላቸውና አኩሪ ወይም ትልቅ ታሪክ የሰሩ ግለሰቦች፣ ቤተሰቦች ወይም ጎሳዎችን ለማወደስ የሚገጠም ግጥም ሲሆን አንዱ የዌየግ ግጥም ሁለት ወይም ሶስት ደቂቃ ሊረዝም ይችላል፡፡

# አጠቃሎ

ይህ ጥናት በደራሲ እንዳለ ጌታ ከበደ *እምቢታ* የተሰኘው *ታሪካዊ* ልቦለድና በአንዷለም አባተ*መኤኒት* በተሰኘ ልቦለድ ላይ የተካሄደ ነው፡፡ ጥናቱ በአራት ክፍሎች የተደራጀ ሲሆን አካሄዱ ደግሞ በሁለቱም ልቦለዶች ውስጥ የተነሱ ፎክሎራዊ ጉዳዮችን በመለየት፣ በትዕምርትነት የተገለፁትን ከልቦለዶቹ አዉድ በመነሳ በመተርጎም ፎክሎራዊ ጉዳዮቹ ለልቦለዱ መሳካት ያበረከቱትን ፋይዳ በመተንተን ነዉ፡፡ ጥናቱ የተከተለው አይነታዊ ምርምር ዘዴን ሲሆን ዓላማ ተኮር የንሞና ዘዴ ተግባር ላይ ዉሏል፡፡ በጥናቱ የስነጽሁፍንና ፎክሎርን መላመድ (ተዛምዶ) ለማሳየት የIntertextuality ንድፈ ሃሳብ በመተንተኛነት አገልግሎት ላይ የዋለ ሲሆን በዋናነት ያተኮረው በልቦለዶቹ ውስጥ በተነሱ የስነቃል ምድቦች መካከል ምርቃት ፣ እርግማን ፣ መሃላ ፣ ምሳሌያዊና ፈሊጣዊ አነጋገሮች በሁለቱም ስራዎች ውስጥ የሚገኙ ሲሆን በእምቢታ ታሪካዊ ልቦለድ ውስጥ የውዳሴ ቃል ግጥሞች በመኤኒት ልቦለድ ውስጥ ደግሞ ፉከራዎች ይገኙበታል፡፡ ሃገረሰባዊ ልማዶችን በተመለከተ በሁለቱም ሥነ-ፅሁፋዊ ስራዎች ውስጥ ሰፊውን ቦታ የያዙ ሲሆን ክብረ በዓላትና ሃገረሰባዊ ስያሜዎችም ተወስተዋል፡፡ቁሳዊ ባህሎችንበሚመለከቱ ባህላዊ አልባሳቶች፣ ጌጣጌጦች፣ ሃገረሰባዊ ምግብና መጠጦችና ባህላዊ ቦታዎች በሁለቱም ስራዎች ውስጥ የተገኙ ሲሆን “በእምቢታ ታሪካዊ ልቦለድ ውስጥ ደግሞ ሃገረሰባዊ ትዕምርቶች ተገኝተዋል፡፡ በዚሁ መሰረት በሁለቱም ስራዎች ውስጥ የተለዩት እነዚህ የፎክሎራዊ ጉዳዮች ፋይዳ ጠቅለል ባለ መልኩ ሲታይ በልቦለዶቹ ውስጥ የተሳሉትን ገፀባህሪያት ማንነት በቀላሉ ለመረዳት፣ በዘመኑ የነበረውን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ባህላዊ አጠቃላይ መንፈስ ለማሳየት፣ የልቦለድ የጀርባ አጥንት የሆነውን ግጭት ለማክረርና በተቃራኒዉ ግጭቱን በማብረድ አንባቢን እፎይታ ለመስጠት፣ ጭብጡን ለመንገርና ለማጉላት፣ የልቦለዱን ትልም ለማዋቀር፣ በንግር ቴክኒክ ታሪኩ በአንባቢያን እንዲገመት በማድረግ ረገድ ኪናዊ ፋይዳ ያላቸው መሆኑን የጥናቱ ውጤት ያመላክታል፡፡ እነዚህን ፋይዳዎች መነሻ በማድረግም ደራሲያን በድርሰት ስራዎቻቸው ውስጥ ፎክሎራዊ ጉዳዮችን አገልግሎት (ጥቅም) ላይ ማዋል ቢችሉ ለሥነ-ፅሁፍ እድገትም ሆነ ለፎክሎር በዘላቂነት ተቀርሶ መቆየት ከፍተኛ ጠቀሜታ ሊኖረው መቻሉን  በጥናቱ ይሁንታ ክፍል ውስጥ ቀርቧል፡፡

# ምዕራፍአንድ

## መግቢያ

### 1.1 የጥናቱ ዳራ

ፎክሎርና ስነ-ፅሁፍ በማህበራዊ ጥናት ዘርፍ የቅርብ ግንኙነት ካላቸዉ የጥናት መስኮች መካከል ተጠቃሾች ናቸዉ፡፡ ፎክሎርን ስናነሳ የፎክሎሩ ባለቤት የሆነውን ማህበረሰብ እናነሳለን ስነ-ፅሁፍ ደግሞ በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉትን የጋራ እውቀቶች፣ ጥበቦችና መረጃዎችን ሳቢ እና ማራኪ በሆነ መንገድ የሚገልፅበት መንገድ ነው፡፡

የፎክሎር አንድ ዘርፍ የሆነዉን ስነ ቃል ከስነ-ፅሁፍ ጋር ያለዉን ትስስር ፈቃደ(1991) "በስነቃልና በስነ-ፅሁፍ መካከል መሠረታዊ ልዩነት የለም፡፡ ከጠባያቸው የሚመነጭ አንድ ልዩነት ቢኖር አንዱ ቃላዊ አንዱ ጽሁፋዊ መሆኑ ነው፡፡ በተረፈ ሁለቱም በቃላት ጡብ ነው የሚገነቡት፡፡ ሁለቱም የሃሳብና የውበት መከሰቻ ይሆናሉ፣ የራሳቸው ዘዴ፣ ዘርፍ፣ መዋቅርና ባህሪ አላቸው፡፡ ሁለቱም ምናባዊ ናቸው" ሲሉ፡፡ በተመሳሳይም Finegan(1970) "ስነቃል ስነ-ፅሁፍ የሚገለፅበትን መንገድ ሁሉ ሊገለፅበት እንደሚችል በማሰብ ስነቃል ራሱን የቻለ ስነ-ፅሁፍ ነው፡፡ ስነቃል እንደስነ-ፅሁፍ ያስተምራል፤ያዝናናል፤ የማህበረሰቡን እውነት ያንፀባርቃል፤ የራሱ መለያ ባህሪ አለው፡፡" በማለት ያስረዳሉ፡፡

የዚህ ጥናት ዋና አላማ *በመኤኒትእና እምቢታ* በተሰኘ ታሪካዊ ልቦለድ ዉስጥ የተነሱ ፎክሎራዊ ጉዳዮችን በመለየት ለምን ፋይዳ እንደገቡ መፈተሽ ሲሆን ፎክሎራዊ ጉዳዮቹ በስነ-ፅሁፍ ስራዉ ዉስጥ የገቡት እንደ መባያ ጉዳይ ሆነዉ ነዉ? ለስነ-ፅሑፍ ስራዉ ማጠንጠኛ በመሆን አገልግለዋል? የገፀ ባህሪያትን ማንነት ከማሳየትና ሎቹብጡን ከማጉላት አንፃርስ ምን ሚና ነበራቸዉ? ግጭቱን ለማጦዝ አልያም ለማብረድስአገልግለዋል? ፎክሎራዊ ጉዳዮቹ የገቡት ለስነ ፅሑፍ ቅርፅንና ቴክኒክን በማውረስ ነዉ? መቼቱን ከመግለፅና የዘመኑን መንፈስ ከማሳየት አንፃርስ ምን ሚና ነበራቸዉ? ደራሲያኑ ፎክሎራዊ ጉዳዮችን በማንሳት የስነ-ፅሁፍ ስራዎቻቸዉን ትልም ለማዋቀር ተጠቅመዉበታል? ወዘተ በአጠቃላይ የፎክሎራዊ ጉዳዮቹ መኖር ለስነ-ፅሁፍ ስራዉ ያበረከተዉ አስተዋጽኦ ተፈትሾበታል፡፡

ለጥናቱ የተመረጡት ሥነ ፅሁፋዊ ስራዎች ሁለት ሲሆኑ የደራሲ እንዳለ ጌታ ከበደእምቢታ የተሰኘዉ ታሪካዊ ልቦለድ አንዱ ነዉ፡፡ ደራሲዉ በኢትዮጵያዉያን ስነ-ፅሁፍ  ታሪክ ዉስጥ የተለያዩ ዘዉጎችን በመጠቀም በርካታ አስተዋፅኦ እያበረከተ የሚገኝ ሲሆን ከአሁን በፊትም ረጃጅም ልቦለዶችን፣ አጫጭር ትረካዎችን፣ የግጥም ስብስቦችንና ኢልቦለዳዊ ስራዎችን ለአንባቢ አበርክቷል፡፡ እምቢታ በተሰኘዉ ስራዉ  የዛሬ አንድ መቶ ሃምሳ ሁለትዓመትአካባቢ (በ1850ዎቹ) ማለትም በአፄ ቴዎድሮስ የንግስና ዘመን በጉራጌ ብሄረሰብ መካከል የሴቶች በደል ቆርቁሯት የተነሳች “የቃቄ ወርድወት” የተሰኘች እንስትን ታሪክ የሚተርክ ነዉ፡፡ ሁለተኛዉ መኤኒት የተሰኘ የደራሲ አንዷለም አባተ(የአፀደ ልጅ) ስራ ሲሆን ይህ  የደራሲዉ የበኩር ስራ እንደሆነ የሚነገርለት ልቦለድ ደራሲዉ የ2ኛ ዲግሪ የመመረቂያ ጥናቱን ለመስራት ወደ ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ መኤኒት ማህበረሰብ ዘንድ ተጉዞ ያደረገዉ ጥናት ሼልፍ ላይ ከመቀመጥ ይልቅ ፈጠራ አክሎበት በልቦለድ መልክ ያሳተመደራሲ ነዉ፡፡

ለጥናት የያዝኩት ርዕሰ ጉዳይን በተመለከተ በሁለተኛ ዲግሪ ደረጃ ባደረኩት ፍተሻ በጂማ ዩኒቨርሲቲ ዉስጥ ባሉ ቤተ-መጻሕፍት ከዚህ በፊት በዚህ ርዕሰ ጉዳይ የተደረገ ምንም አይነት መረጃአላገኘሁም፡፡ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ዉስጥ የተሰሩ ከያዝኩት ርዕሰ ጉዳይ ጋርተቀራራቢ የሆኑ አምስት ስራዎችን ለማየት ሞክሬያለሁ፡፡ ተዛማጅ ስራዎቹ በምዕራፍ ሁለት ስር ሰፋ ያለ ማብራሪያ የሚሰጥባቸዉ ሲሆን በጥቅሉ ግን የአምስታችንም ጥናት ልዩ ትኩረት የሆነዉ ከተለምዷዊዉ የልቦለድ አላባዉያን ተገቢነትና ኢተገቢነትን ከመመርመር በዘለለ የስነ ፅሁፍን ፈርጀ ብዙ የጥናት መስክነት (በይነ ዲሲፒሊናዊነት) በማሳየት ሥነ ጽሁፍ ከሌሎች ዘርፎች ጋርም መጠናት እንደሚችል መጠቆም ላይ ማተኮሩ  ከዚህ ጥናት ጋር ተመሳስሎ የሚታይበት ሲሆን ከልቦለድ ስራዎቹ ምርጫ መለያየት፣ ስነ ፅሁፍን ያዛመድንበት መንገድ ፎክሎርን ከታሪክ መፃህፍትና ዜና መዋዕሎች ጋር ስነ-ፅሁፍን ከሚቶሎጂ ጋር፣ ስነ-ፅሁፍን ከሥዕልና ከፎክሎር ጋር እንዲሁም ፎክሎርን ከተዉኔት ጋር መሆኑ ዋነኛዉ ልዩነታችን ሲሆን በአላማ ይዘነው የተነሳነው ሃሳብ እንዲሁም የተጠቀምነዉ ንድፈ ሃሳባዊ ቅኝትም ለየቅል ነው፡፡

ጥናቱ በምዕራፍ አንድ የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት፣የጥናቱ ዋናና ዝርዝር አላማዎች፣ ጥናቱ የሚመልሳቸዉ መሪ ጥያቄዎች፣ የጥናቱ ጠቀሜታና የጥናቱ ወሰንን ያካተተ ሲሆን በምዕራፍ ሁለት ደግሞ ክለሳ ድርሳናት የቀረቡበት ሆኖ ሁለት ንዑሳን ክፍሎችም አሉት፡፡

በመጀመሪያዉ ክፍል ስለሚሰራበት ርዕሰ ጉዳይ የንድፈ ሃሳብ ቅኝት የተደረገበት ሲሆን በሁለተኛዉ ደግሞ ከዚህ ጥናት ጋር የሚዛመዱ ቀደምት ጥናቶች ተመሳስሎና ልዩነቶች ተዳሰዉበታል፡፡

ምዕራፍ ሶስት የጥናቱ ዘዴንና ንድፍ በመያዝ በዉስጡም የመረጃ ምንጮችን ፣ ንሞናን፣ የመረጃ አሰባሰብ ዘዴን አቅፎ ይዟል ፡፡

በምዕራፍ አራት ትንተናዉ በምዕራፍ አምስት ደግሞ ማጠቃለያ እና ይሁንታ ተሰጥቶበታል፡፡ በመጨረሻም ዋቢዎች ቀርበዋል፡፡

## 1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

ይህ የምርምር ርዕስ ይመረጥ ዘንድ ዓበይት ምክንያቴ የፎክሎርና ስነ-ፅሁፍ ተማሪ እንደመሆኔ በግል ከሁለቱም ጥበባት ጋር ባለኝ ቅርበት አንዱ በሌላኛው ውስጥ ሲገባ ሊኖረው የሚችለውን ፋይዳ በክፍል ውስጥ በሚሰጠኝ አሳይመንት በሌሎች ልቦለዶች ላይ ስሰራ በዚያ ወቅት ይህንን ዝምድና ከማጤኔ በተጨማሪ ፎክሎርና ሥነጽሁፍ በባሕርይ እና በግብር ተዛምዶ እንዳላቸው ያስተዋልኩ በመሆኑ ይህንን የጠበቀ ትስስር በመረጃ አስደግፌ ለማሳየት ያደረብኝ ፅኑ ፍላጎት ሲሆን

ሁለተኛው በስነ-ፅሁፍም ሆነ በፎክሎር ጥናት መስክ ከላይ በዳራዬ ከጠቀስኳቸዉና ከጥቂት ግለሰቦች ግላዊ ጥረት በቀር የጎላ ተቋማዊ ምርምርም ሆነ ትኩረት ሲደረግባቸው አላየሁም፡፡ በዚህ ጥናትም በባሕርይም ሆነ በግብር የተገለጹት ፈርጀ ብዙ ዝምድናዎችና አንዱ በሌላኛው ላይ የሚጫወተው ሚና በመመርመር በዘርፉ ለሚታየው ክፍተት የበኩሉን አስተዋፅኦ ሊያበረክት ይችላል በሚል ዕምነት ወደ ጥናቱ ለመግባት ተችሏል፡፡

## 1.3 የምርምር ጥያቄዎች

ይህ ጥናት ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች ይመልሳል ተብሎ ይታሰባል ፡፡

- *በመኤኒትና እምቢታ ታሪካዊ* ልቦለድ ውስጥ የሚታዩት ፎክሎራዊ ጉዳዮች ምን ምን ናቸው?
- *በመኤኒትና እምቢታ ታሪካዊ* ልቦለድ ዉስጥ የሚገኙት ትዕምርታዊነትን የያዙ ጉዳዮች በቀረቡበት አዉድ ምን ትርጉም ይሰጣሉ?

- ❖ ደራሲያኑ በልቦለዶቻቸው ውስጥ ፎክሎራዊ ጉዳዮቹን ማንሳታቸው ለስነ ጽሁፍ ስራው ምን ፋይዳ አስገኝቶላቸዋል?
- ❖ በሁለቱም ልቦለዳዊ ስራዎች ዉስጥ የፎክሎርና የስነ ጽሁፍ ትስስር እስከምን ድረስ ነው?

## 1.4 የጥናቱ ዓላማ

ከላይ የተዋቀሩትን የምርምር ጥያቄዎች ለመመለስ ቀጣዮቹ አብይና ዝርዝር ዓላማዎች ተነድፈዋል፡፡

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በመኤኒት እና "በእምቢታ ታሪካዊ ልቦለድ ውስጥ የሚነሱ ፎክሎራዊ ጉዳዮች ለምን ፋይዳ እንደመጡ መመርመር ሲሆን በንዑስነትም፡-

- ❖ በመኤኒትና እምቢታ ታሪካዊ ልቦለድ ውስጥ የሚታዩትን ፎክሎራዊ ጉዳዮች መለየት፤
- ❖ በሁለቱም የልቦለድ ስራዎች ዉስጥ የሚገኙ ትዕምርቶችን በቀረቡበትን አዉድ መፈከር
- ❖ በሁለቱም ስራዎች ውስጥ የሚገኙትን ፎክሎራዊ ጉዳዮች እየመዘዙ ለአጠቃላይ የሥነ-ጽሑፍ ስራው ያበረከቱትን ፋይዳ በመፈተሽ የፎክሎርና የስነ ጽሁፍ ትስስር እስከምን ድረስ እንደሆነ መጠቆም የሚሉት ይገኙበታል፡፡

## 1.5 የጥናቱ አስፈላጊነት

የዚህ ሥነጽሑፋዊ ጥናት አስፈላጊነት

ለዘርፉ እድገት ከላይ በአነሳሽ ጉዳይ ላይ እንደተገለጸው የፎክሎርና የስነ ፅሁፍን ፈርጀ ብዙ ዝምድናዎችና አንዱ በሌላኛው ላይ የሚጫወተው ሚና በወጉ ቢመረመር ብሎም በሥነጽሑፍ እና በፎክሎር መካከል ያሉ የጋራ ወሰኖችን ከማመላከት አኳያ ለዘርፉ እድገት የራሱን አስተዋፅኦ ሊያበረክት ይችላል፡፡

ለአንባቢያን እያንዳንዱ ብሄረሰብ የማንነቱ መገለጫ የሆኑ ባህላዊ እሴቶች ባለቤት እንደሆነ ለማሳወቅና አንዱ ከሌላው ባህል ጋርእንዲተዋወቅ ለማስቻል ጠቀሜታ ሲኖራቸው በተለይም የባህሉ ባለቤት ለሆነ አንባቢ በተለያዩ የስነ-ፅሁፍ ስራዎች ውስጥ የአንድን

ማህበረሰብ ባህል፣ ወግና፣ ልማድ መጠቀም ማህበረሰቡ ባህሌንና እኔነቴን የሚገልፅልኝ የራሴ ስነ-ፅሁፍ አለኝ ብሎ እንዲያስብ ያደርገዋል ተብሎ ይታሰባል ፡፡

ለጸሃፊያን የተለያዩ የፎክሎር ዘሮችን በስነ-ፅሁፍ ስራዎቻቸው ውስጥ በማስገባት ፅሁፉ ኪናዊ ውበት እንዲኖረውና የስነ-ፅሁፍ ስራዎቻቸው ከይዘት አንፃር ጉልበት እንዲኖራቸው በማድረግ አዲስ እይታን ሊያመላክት ይችላል ፡፡

በቀጣይ በዘርፉ ምርምር ለሚያደርጉ ምሁራን አጋርዥ (ፍንጭ ሰጪ) መረጃ በመሆን ሊያገለግል ይችላል ተብሎ ይታሰባል ፡፡

## 1.6 የጥናቱ ወሰን

የጥናቱ ወሰን ከተመረጡት ስነ ፅሁፋዊ ስራዎችና ከፎክሎር ዘሮች አንፃር የሚታይ ነው፡፡ ከልቦለዶቹ አንፃር በመኤኒት እና "በእምቢታ" ታሪካዊ ልቦለዶች ላይ ብቻ ያተኮረ ሲሆን ዋነኛ ትኩረቱ ፎክሎራዊ ጉዳዮችን መዳሰስ እንጂ የአላባውያንን ተገቢነትና ኢተገቢነት በጥልቀት አልተመለከተም፡፡ይህ ማለት ግን ከፎክሎራዊ ጉዳዮች ትንተና ጋር በተያያዘ አልተነሱም ማለት አይደለም፡፡

ከፎክሎር ዘርፎች አንፃር ጥናቱ የሚመለከተው ሃገረሰባዊ ልማዶች ፣ ቁሳዊ ባህልና ስነ ቃሎችን ሲሆን ሃገረሰባዊ ትዉን ጥበባትን ግን በልቦለዶቹ ዉስጥ ማግኘት ያልተቻለ በመሆኑ በትንተናዉ አልተካተተም፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

## ክለሳ ድርሳናት

### 2.1 ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝት

ይህ ምዕራፍ በሁለት ዓበይት ክፍሎች ተዋቅሮ የቀረበ ነው፡፡ የመጀመርያው ክፍል የስነ-ፅሁፍ ምንነት፣ የፎክሎር ምንነትና ምደባዎችን እንዲሁም የስነ ጽሁፍና የፎክሎርን ትስስር በተመለከተ ምሁራን የሰጧቸውን ሃሳቦች በማጣቀስ ንድፈ ሀሳባዊ ዳራ የተደረገበት ሲሆን ሁለተኛው ክፍል ደግሞ ከዚህ ቀደም ለጥናት ከተያዘው ርእስ ጉዳይ ጋር ሊዛመዱ የሚችሉ ወደ አምስት የሆኑ የሁለተኛና የሶስተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናቶች በተዛማጅ ጽሁፍነት ቅኝት ተደርጎባቸዋል፡፡

#### 2.1.1. የስነ-ፅሁፍ ምንነት

ስነ-ፅሁፍ ስሜትን መግለጫ፣ የገሀዱን አለም ማንፀባረቂያ፣ የሰው ልጆችን ውበትና መጥፎ ገጠመኞች የምናሳይበት የአእምሮ ግኝት ነው፡፡ ስነ-ፅሁፍ ዘመን ተሻጋሪ የሆነ፣ የሰው ልጆችን የህይወት ተሞክሮ መሠረት በማድረግ ውብ በሆነ የቋንቋ አገላለፅና ስልት የተደራሲያንን ባህል፣ እውቀትና የአኗኗር ጥበብ መግለጫ መንገድ ነው፡

> ስነ-ፅሁፍ በተለያዩ ቅርፆች በቋንቋ አማካኝነት የሚከሰት፣ ስለሰዎች፣ በስዎች፣ ለሰዎች የሚዘጋጅ የገጠመኝ ማንፀባረቂያና ህይወትንና እውነትን እንዲሁም ባህልን በአንድ አጣምሮ የሚይዝ ህልውናው በቃልም፣ በፅሁፍም የሆነ የፈጠራ ስራ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ስነ-ፅሁፍ የሰው ልጅ ባህል፣ ገጠመኝ ማንፀባረቂያ፣ የሰው ልጅ ህይወት መልኮች መግለጫ ነው፡፡ ህይወት ባለብዙ ፈርጅ፣ ባለብዙ ቀለም መሆኗም ግልፅ ነው፡፡ ስለዚህ የስነ-ፅሁፍ ክልል እዚህ ድረስ ነው ተብሎ ሊገደብ አይችልም ማለት ነው (ዘሪሁን1992፣3)፡፡

ስነ-ፅሁፍ ማንኛውንም በሰው ልጅ ገጠመኝ የተከሰተንና ሊከሰት የሚችልን ነገር እንዲሁም በሰው የምናብ አድማስ ሊሆን ይችላል ተብሉ የሚታሰብ ነገር ሁሉ ሊያካትት ይችላል፡፡ መጠነ ርእዩ ሰፊ ብቻም ሳይሆን ገደብ አልባም ነው፡፡ሥነ ጽሑፍ እንደሙያ መታየት ከጀመረበት ከ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ የተለያዩ የአጠናን ስልቶች ተቀምረዋል፡፡ የስነ ፅሁፍን ከተለያዩ ዘርፎች ጋር መዛመድን በይነ-ዲሲፕናዊ ነው የሚሉት ቴዎድሮስ ገብሬ፣ በግርጌ ማስታወሻቸው ላይ ቃሉን ሲፈቱ፣ "ከአንድ በላይ በሆኑ

ዲሲፕሊኖች ጥምረትና ውህደት የማሰብ፣ የመጠየቅ፣ የማጥናት እና የመመርመር ልማድ ነው" ይሉታል (ቴዎድሮስ፤2001፣xiii)፡፡

ስነ-ፅሁፍ ባለብዙ ፈርጅ ባለ ብዙ ቅርንጫፍና ከአያሌ የእውቀት ዘርፎች ጋር የሚነካካ የኪነ ጥበብ ዘርፍ ነው(ዘሪሁን፤1992፣1)፡፡

ቴዎድሮስ (2001) እንደሚያስረዱት"ሥነ ጽሑፍ አንድም ብዙም የሚሆን ጥበብ ነው፡፡ ሥነ ጽሁፍን ለብያኔ ፈጽሞ የማይገራ ጥበብ ካደረጉት መሀል ዋነኛው ይህ የባህርይው ብዙነት ይመስለኛል፡፡ ሥነ-ጽሑፍ በአንዳንድ ቅርፆቹ አማካይነት ከሌሎች ዲሲፕሊኖች ጋር ይጎራበታል፤ በሌሎቹ ቅርጾቹ ይዛመዳል፤ በተቀሩት ደግሞ በመሀል የተሰመረ ድንበር እስኪፈርስ ድረስ ከሌሎች ዲሲፒሊኖች ጋር ይደባለቃል፣ ይቃየጣል፣ ይዋሃዳል" (ቴዎድሮስ 2001፣140)፡፡

የስነ ጽሁፍ ኪን በምናብ አማካይነት የሚፈጠር ዓለም ነው፡፡ የከያኒው ቀዳሚ ምርጫ በትክክል ከተደረጉና ከሆኑ ግለሰባዊ ገጠመኞች ይልቅ በጥቅሉ የሰው ልጅ ህይወት ውስጥ ሊኖሩና ሊደርሱ ይችላሉ ተብለው የሚታመንባቸው ገናን እውነታዎች አበይት ትኩረቶቹም ከምናብ የመነጩ የስሜትና የእስብ ገጠመኞች ናቸው፡፡"ስነ ጽሁፍ ይፈጥራል እንጂ አይዘግብም፡፡ ህይወትን ይተረጉማል የሰው ልጅን ይፈክራል እንጂ አይገለብጥም የአደራረስና የአከያየን ሂደቱ ምልዓት ያለው ፍች የመፍጠር ሂደት ነው" (ቴዎድሮስ፤ 2001፣140)፡፡ አክሎም ስነ-ፅሁፍ ራሱ የባህል ክንውን ዘርፍ መሆኑንም ይነግረናል፡፡ከዚህ ከፍ ሲል ደግሞ ስነ-ፅሁፍ የባህል መፍጠሪያም ነው የሚል የጠነከረ አስተያየት አለው፡፡ ከዚህ በመነሳት ስነ-ፅሁፍና ባህል አንፃር ለአንፃር የቆሙና አንዱ ለሌላው "ባዕድ" (external) ሁነው የተሰለፉ አለመሆናቸውን እንረዳለን፡፡ ይህ ማለት ባህልና ስነ-ፅሁፍ ቁርኝት አላቸው ማለት ሲሆን ባህል በስነ-ፅሁፍ አማካይነት የሚገለጸውን ያህል ስነ-ፅሁፍም ከሚገለጸው ባህል የሚመነጭ መልሶም በባህል ላይ ተጽእኖ የሚያደርግ ነው ማለት ይቻላል፡፡ (ዘሪሁን፤1992፡7) እንደሚያስረዱት

> በአጠቃላይ ሥነ-ፅሁፍ የአንድን ማህበረሰብ ኢኮኖሚያዊ ፣ፖለቲካዊና ማህበራዊ መልኮች ከማሳየቱም በላይ ቅርጹ በሚፈቅደው መሰረት ግለሰቦችና ህዝቦች ከነዚህ ከሶስቱ ጋር ያላቸውን ግንኙነት ፣አሰራርና ሁኔታ ያንጸባርቃል፡፡ሥነ-ፅሁፍ የአንድን ማህበረሰብ ወግና ልማድ እንዲሁም ባህል ለሚቀጥለው ትውልድ በማስተላለፍ ረገድ የሚጫወተው ሚና ከፍ ያለ ነው፡፡ ማህበረሰቡ በአኗኗር

> ስርዓቱም ሆነ በእምነቱ የሚከተላቸውን ልዩ ልዩ አቅጣጫዎች በቅርስነት በማቆየት ተከታዩን ትውልድ የማስተማርና የማሳወቅ ተግባር ይፈፅማል፡፡

ከላይ የሥነ-ፅሁፍን ምንነት በተመለከተ በተለያ ጊዜያት የተገኙ ምንጮችን በማጣቀስ ለመግለጽ የተሞከረ ሲሆን በቀጣይም በሥነ-ፅሁፍ ምርምር ውስጥ ገናን የሚባሉ ፅንሰ ሃሳቦችን ለማየት ተሞክሯል፡፡

### 2.1.1.1.የመባያ ጉዳይ በሥነ-ፅሁፍ ውስጥ

የመባያ ጉዳይ በሥነ- ጽሑፍ ምርምር ውስጥ እጅግ ገናን ከሆኑ ጽንሰ ሐሳቦች መሃል አንዱ ነው፡፡ ይህ ፅንሰ ሐሳብ በተለያዩ መንገዶች ሊከሰት ወይም የተለያዩ ጉዳዮችን ሊያጠቃልል ይችላል፡፡ ቴዎድሮስ ገብሬ በይነ ዲሲፒሊናዊ የስነ-ፅሁፍ ንባብ በሚለው መጽሃፍ ውስጥ እንዲህ ይገልፁታል፡-

> አንድ ጉዳይ መባያ ነው ለመባል በተለያዩ የኪነ ጥበብ ዝርያዎች ወይም በብዙ ሥነ ጽሑፋዊ ሥራዎች ውስጥ ተደጋግሞ መታየት፤ አልያም ቢያንስ በአንድ ስራውስጥ ተመላልሶ መምጣት እንዳለበት የስነ-ፅሁፍ ተመራማሪዎች ያስረዳሉ (Abrams 1999፣169-170 እና Abbott፣ 2002፣ 88-89)፡፡ሌሎች ተመራማሪዎች (ለምሳሌ፣Hawthorn 2001፣157)እንደሚያስረዱት ደግሞ መባያዎች ተደጋግሞ ከመምጣት ጋርበአመዛኙ ትዕምርታዊነት አያጣቸውም፡፡ ስለዚህ ቃሉ፤ መባያ በጥቅሉ፣በአንድ በኩል ለሚባለውእና ለሚመሰለው ጉዳይ ማለትም (object of [re]presentation)፤ በሌላ በኩል ደግሞ ጉዳዩ ለሚባልበት ሁኔታና ለሚመሰልበት መንገድ(mode of [re]presentation) በመጠርያነት እኩል ሊያገለግል ይችላል (ቴዎድሮስ፤2001፣104)፡፡

የመባያ ጉዳይ በስነ-ፅሁፍ ስራ ውስጥ ልቦለዱ የሚባልበት አብይ ጉዳይ ማለት ሲሆን ከ (theme) ከልቦለዱ ጭብጥ ጋርግንኙነት ያለው ፅንሰ ሃሳብ ነው፡፡ ይህ ማለት ግን ሁለቱ ተመሳሳይ ናቸው ማለት አይደለም፡፡ በሁለቱ መካከል መሰረታዊ ልዩነት ያለ ሲሆን አንዱ ለሌላኛው አጋዥ በመሆን የሚያገለግል ነው፡፡

> In a literary work, a motif can be seen as an image, sound, action, or other figure that has a symbolic significance, and contributes toward the development of a theme. Motif and theme are linked in a literary work, but there is a difference between them. In a literary piece, a motif is a recurrent image, idea, or symbol that develops or explains a theme, while a theme is a central idea or message (lehner.E 1950)

በአንድ የሥነ-ፅሁፍ ስራ ውስጥ ጭብጡን ለማጉላት በተደጋጋሚ የሚገቡት መባያ ጉዳዮች የማህበረሰቡ ፍልስፍና፣ አመለካከት፣ እምነትና ባህል ውጤቶች ናቸው፡፡ እነዚህን ጉዳዮች ለመተንተን በማህበረሰቡ ዘንድ ያላቸውን ውክልና ማወቅ በእጅጉ አስፈላጊ ይሆናል፡፡ ለጥናት ከተያዙት ሁለት ስራዎች ዉስጥ በእምቢታ ታሪካዊ ልቦለድ ዉስጥ የሚገኙ ቁሳዊ ባህሎች በልቦለዱ ዉስጥ ትዕምርታዊ ፍቺን በመያዝ እንደ መባያ ጉዳይ ሆነዉ ሲመጡ ተስተዉለዋል፡፡ እያዳንዳቸዉም በትንተናዉ ዉስጥ ተፈክረዉ ቀርበዋል፡፡

### 2.1.1.2 የዘመን መንፈስ በሥነ-ፅሁፍ ውስጥ

እያንዳንዱ የስነ-ፅሁፍስራ በአንድም ሆነ በሌላ መልኩ የተፃፈበትን ዘመን ይገልፃል፡፤ ፀሃፊው በዘመኑ የነበረው መንፈስ ፖለቲካ ይሁን ስደት ፤ትምህርት ይሁን ፤ድንቁርና ሰላም ይሁን ጦርነት ወዘተ በአጠቃላይ ፅሁፉ በፃፈበት ዘመን የነበረውን አጠቃላይ ድባብ በተለያዩ መንገዶች ተጠቅሞ ለአንባቢው ለመንገርና አንባቢውም ዘመኑን በሃሳብ እየሳለ እንዲከተለውና የልቦለዱን መቼት በቀላሉ እንዲረዱት ይሞክራል፡፡ (ቴዎድሮስ፤2001) የዘመን መንፈስን ሲያብራራው

> የዘመን መንፈስ ፅንሰ ሃሳቡ እንደሚያመለክተው በዋናነት በተወሰነ ዘመን ውስጥየተከናወኑና የሆኑ ነገሮችን ፤ ራሳቸውን ሳይሆን ነገሮቹ በሰዎች ልቦና ውስጥ የሚያሳድሩትን ተፅዕኖ ይመለከታል፡፡ ለዘመን መንፈስ ሳይንስ እና ቴክኖሎጂ  አይደለም አብይ ጉዳዩ አብዮት አይደለም ግዱ ጅሃድ ወይም የመስቀል ጦርነትአይደለም ትኩረቱ፡፡ትኩረቱ እነዚህ ክስተቶች በማህበሩ ልቦና ውስጥ የሚፈጥሩት ወረራ ወይም በባህሉ ላይ የሚጥሉት ድባብ ነው፡፡ በብዙዎቹ ሃያሲያን እና የማህበረሰብ አጥኚዎች እምነት ደግሞ ሥነ-ፅሁፍ ለዚህ ዓይነቱ ዝንቅ መንፈስ የተመቸ ማደሪያ ነው(ቴዎድሮስ፤2001፣265 )፡፡

እያንዳንዱ የሥነ-ፅሁፍ ስራ በአንድም ሆነ በሌላ መልኩ የተፃፈበትን ዘመን ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊም ሆነ ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ ያንፀባርቃል፡፡ ይህ አሁን እኛ ባለንበት ዘመን ማለትም ከ1983 በኋላ ያለው ዘመን ትልቅ ለሥነ-ፅሁፍ ግብአት በመሆን የሚነሳው የሳንሱር ነፃነቱ ከቀድሞዎቹ የተሻለ የሆነበት ዘመን በመሆኑና በርካታ ማተሚያ ቤቶች መከፈታቸውም ሌላው ግብዓት ሲሆን ወጣት ደራሲያንም የተበራከቱበት ዘመን ነው፡፡ በዚህ ዘመን የሚፃፉት ስነ-ጽሁፋዊ ስራዎች አብዛኞቹ ስነ-ፅሁፍ ራስንና ማንነትን መፈለጊያ ነው የሚል ሃሳብ የሚነሱባቸው ናቸው፡፡ ሌላው በዘመኑ የብሄረሰቦችን ማንነት የሚመለከቱ (ባህላዊ) ጉዳዮች በሥነ-ፅሁፍ ስራዎች ውስጥ መታየት የጀመሩበትና የአንድን ዘመን ባህል የስነ-ፅሁፍ  ግብዓት አድርጎ መፃፍ ይቻላል በማለት ደፍረው የሚገቡ በርካታ

ደራሲያን እየታዩበት ያለ ዘመንም ነው፡፡ ለዚህ ጥናት የተመረጡት ሁለት ስራዎችም የቅርብና የተቀራራቢ ዘመን በመሆናቸዉ ብሎም ኢትኖግራፊክ የአፃፃፍ ስልትን የተከተሉና ስነ ፅሁፍን ከባህል ጋር እያዋደዱ የተፃፉ በመሆናቸዉ በወል ጥናትነት ተመርጠዉ ለመተንተን ችለዋል፡

### 2.1.2 የፎክሎር ምንነትና ምደባ

"ፎክሎር" "ፎክ" እና "ሎር" ከሚሉ ሁለት የእንግሊዘኛ ቃላት የተዋቀረ ፅንሰ ሃሳብ ነው፡፡ "ፎክ" የሰዎች ስብስብ ሲሆን "ሎር" ደግሞ እውቀት ወይም ሰዎችን ያሰባሰበው ርዕሰ ጉዳይ ማለት ነው፡፡ እንደ Dundes.(1980፣1) አገላለጽ የሁለቱ ቃላት ጥምረት "የቡድን እውቀት" የሚል ነው፡፡ Dundes.(1980፣6) "የጋራ ጉዳይ ያሰባሰባቸው ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎች ስብስብ ፎክ ይባላል" ይላል፡፡ ብያኔው ውስጥ የቡድኑ አባላት ለመሰባሰብ ምክንያት የሆናቸው የጋራ ባህርይ እንዳለ ያስገነዝባል፡፡ Toelken.(1996፣56) ቡድን መገለጫቸው ባህልን መሰረት ያደረገ ተግባቦት ያላቸው ሰዎች ስብስብ ነው ብለዋል፡፡ በመሆኑም ፎክሎር የሚለው ጽንሰ ሀሳብ ሲነሳ ሁሌም የሰው ልጅ እና ህይወቱ ይቃኛሉ፡፡

ሰለሞን (2007) ማርታና ማርቲን (2005፣8)ን ጠቅሶ እንደገለፀው"Folklore is informally learned, unofficial knowledge about the world, ourselves, our communities, our beliefs, our cultures and our traditions, that is expressed creatively through words, music, customs, behabiours and materials."ይላል፡፡ የአማርኛ ትርጉሙ "ፎክሎር በመደበኛ ህግ የማይገዛ (ባህላዊ የሆነ) በኢመደበኛ አኳኋን የሚለመድ፣ በፈጠራዊ ቃል፣ ሙዚቃ፣ ልማድ፣ ባህርይና ቁሳቁስ የሚገልጽ፤ ስለዓለም፣ ስለራሳችን፣ ስለ ማህበረሰባችን፣ ስለእምነታችን፣ስለ ባህላችንና ስለ ትውፊታችን ያለን እውቀትነው" የሚል ይሆናል፡፡ Ben-Amos,(1979) ፎክሎር ማህበረሰቡ በቋንቋው አማካይነት ባህላዊ እሴቶቹን የሚገልጽበት መስታወት ከመሆኑ አንፃር የማህበረሰቡ ማንነት መግለጫና በውስጡም በርካታ እሴቶችን ያካተተ መሆኑን ይናገራል።በመሆኑም ፎክሎር አገልግሎት የሚሰጥበት ማህበረሰብ ቁሳዊና መንፈሳዊ ንብረቱ እንደመሆኑ መጠን የህዛቦችን ልማድ፣ ወግ፣ እምነት እና ጥበቦችን ያካተተ የባህል ዘርፍ መሆኑንም አመልክቷል።

የፎክሎር ምደባን በተመለከተ Dorson በመስኩ የሚደረግ ምርምርን ስርዓት ለማስያዝና መልክ ለመስጠት ሲል ፎክሎርን በአራት ዋና ዋና ዘርፎች የከፈለ መሆኑን ፈቃደ (1991፣ 2-4) ይገልጻል። እነርሱም ስነቃል (Oral Literature) ፣ሀገረሰባዊ ልማድ (Folk Custom) ቁሳዊ ባህል (Material Culture)እና ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት (Performring Folk Arts) ናቸው። ዩኒስኮ ደግሞ ይህን ምደባ እንዳለ ይወስድና ሀገረሰባዊ ልማድን በሁለት በመክፈል "Intangible Cultural Heritage" የሚለውን ጨምሮ በአምስት መድቧቸዋል። አምስተኛውንም "የተፈጥሮ እውቀትና ትግበራ" ይለዋል። ይህ ደግሞ ራሱን ችሎ የሚወጣ ሳይሆን በሀገረሰባዊ ልማድ ውስጥ ሊካተት የሚችል ጽንሰ ሀሳብን የያዘ ነው። ሰለሞን 2007ም ይህን Dorson አከፋፈል እንዳለ ወስዶ ሃገረሰባዊ ውክልናና ማህበረ ፖለቲካዊ ተቋም የሚሉትን በመጨመር በስድስት ይከፍላቸዋል፡፡ ይሁንና ሰለሞን የጨመራቸው ሁለቱ የፎክሎር ዘርፎች ራሳቸውን ችለው ለብቻ ወጥተው የሚገኙ ሳይሆኑ በአራቱ ዋናዋና የፎክሎር ዘርፎችውስጥ በመግባት የሚገለፁ በመሆናቸው በዚህ ጥናት በፈቃደ (1991) እንደተገለፀው ፎክሎርን በአራት አበይት ዘርፎች ከፍሎ የሚታይ ይሆናል፡፡ ይሁንና ለጥናት በተመረጡት ሁለቱም ስራዎች ዉስጥ የሚገኙት ስነቃል፤ሃገረሰባዊ ልማድና ቁሳዊ ባህል በመሆናቸዉ በሶስቱ ላይ ብቻ ትንተና ተሰጥቶባቸዋል፡፡

### 2.1.2.1 ስነቃል

ከስሙ እንደምንገነዘበው "ሥነ-ቃል" የሚለው ሐረግ ከሁለት ሥርወ-ቃላት የተወሰደ ሲሆን "ሥነ"- 'ተውህቦ'፣ 'ውበት'፣ 'ጥበብ'፣ የሚሉትን ፍችዎች ይጠቅሳል። "ሥነ" የሚለው ቃል በአገናዛቢ ሥነ-ፅሁፍ፤ ሥነ-ጥበብ፣ ሥነ-ምድር፣ ሥነ-ፍጥረት፣ ሥነ-ሰብዕ፣ ሥነ-ውበት፣ ወዘተ. እየተባለ ለልዩ ልዩ የጥናት መስኮች ስያሜ በመሆን ያገለግላል።

በዚህ አገባብ ሥነ-ቃል በጥሬ ትርጉሙ "የቃል ጥናት" እንደማለት ሲሆን "ሥነ" የሚለውን ቃል በቁሙ ከወሰድን "የተዋበ ቃል"፣ "የቃል ውበት"፣ "ውበት ያለው ቃል"፣ "ጥበብ ያለው ወይም ጥበብ የተሞላበት" ወዘተ እንደማለት ይሆናል፡፡

"ሥነ-ቃል" ከሰው ልጅ ታሪክ ተነጥሎ የማይታይ እንዲሁም በሥነ-ሰብዕና በማህበረሰብ ሳይንስ፣ በፍልስፍና፣ በሥነ-አምልኮ፣ በሥነ-ፅሑፍ፣ ወዘተ. መስኮች ለረጅም ዘመናት ሲጠና ቢቆይም ለፅንሰ-ሀሳቡ ከተግባራዊ ብያኔ በስተቀር እስካሁን የተጠቃለለ ንድፈ-ሀሳባዊ ብያኔ አልተሰጠውም።

ሥነቃል የአንድ ህዝብ ቁሳዊና መንፈሳዊ እሴት መግለጫ፣ የኑሮውና የስሜቱ ነፀብራቅ እንደሆኑ ይገልፃሉ (ፈ.ቃደ፤1991)፡፡ሥነ-ቃል ለፈጠረው ማህበረሰብ ከፍ ያለ ፋይዳ ያለው ሲሆን ይኸውም አንድ ማህበረሰብ በሥነ-ቃሉ አማካኝነት ማንነቱንና ምንነቱን ያሳውቅበታል፡፡ ከነዚህም ውስጥ የህዝቦች የትመጣቸውን፣ የዘር ሀረጋቸውን ይነግሩበታል፣ ሰዎች አመለካከታቸውን፣ ፍልስፍናቸውን ይገልጹበታል ፤የማንነታቸው መገለጫ የሆነው ባህላቸው ተጠብቆ እንዲቆም ያደርጉበታል፤ በአጠቃላይ ብሶታቸውን፣ ሀዘናቸውን፣ ጥላቻቸውን፣ ደስታቸውን፣ ፍቅራቸውን፣ ናፍቆታቸውን…ይፋ ያወጡበታል

ሥነቃል በርካታ ቅርንጫፎች ያሉት ሲሆንእንደ (ዘሪሁን፤1992) ገለፃም የስነ ቃል ምድቦች "ተረት፣ ምሳሌያዊ አነጋገሮች ፈሊጦች፣ እንቆቅልሽ፣ እንካስላንቲያ፣ አፈታሪክ፣ ምርቃን፣ እርግማን፣ ፉከራና ቀረርቶ፣ የሙሾ፣ የቡሄና የእንቁጣጣሽ ግጥሞች፣ የአካባቢ ስያሜዎች፣ ቀልዶች፣ቃል ግጥሞች (የህፃናት ጨዋታ ግጥሞች)፣ (የልመና ግጥሞች)፣ (የብሶት መግለጫ ግጥሞች)፣(የሙገሳ ግጥሞች ስለሰው፣ እንስሳና ተፈጥሮ አፈጣጠርና ባህሪ የሚገልፁ ሀተታ ተፈጥሮዎች ወዘተ ይካተታሉ"፡፡

### 2.1.2.2 ሀገረሰባዊልማድ

ሀገረሰባዊ ልማድ የሚባለው የአንድ ማህበረሰብ የጋራ ይዞታ የሆነ፣ ነባርና ቋሚ ዘልማዳዊ የአኗኗር መንገድ ነው፡፡ ነባር ሲባል የቆዬ (የጥንት)፣ ቋሚ ሲባል ዘላቂ፣ ሊጠፉ የማይችሉ ማለት ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ የተወሰኑ ቡድኖች ወይም የማህበረሰብ አባላት የወል የኑሮ ዘይቤ ነው፡፡

ሃገረሰባዊ ልማዶችን በተመለከተ እንደ ሰለሞን (2007) ገለፃ "ሃገረሰባዊ ልማድ ማህበረሰቡ በተደጋጋሚ የሚከውናቸው ድርጊትና ቅደም ተከተላዊ ሥርዓትን መሰረት በማድረግ የሚቀርቡ ጥበቦች ጥቅል መጠሪያ ነው" ፡፡"በሀገረሰባዊ ልማዶች ሰዎች አጥብቀው የያዟቸው እምነቶችና ልማዶች መነሻ ምንጫቸው ምንድነው? የተወሰኑ ስርዓቶችንና እምነቶችን ስለምን ይከተላሉ? እና የመሳሰሉ ጥያቄዎችን በተለይ ፈላስፎች፣ ደራሲያን፣ ስነሰበኞችና ፎክለረኞች ጊዜ ወስደው የተመራመሩባቸውና ዛሬም የሚመራመሩባቸው ጥያቄዎች ናቸው" ፈ.ቃደ (1991፣13) ፡፡ከላይ ከቀረበው ሀሳብ ለመገንዘብ እንደሚቻለው ሀገረሰባዊ ልማድች ሰዎች በዘመናቸው አጥብቀው የያዟቸው አመለካከቶች ናቸው ማለት ይቻላል፡፡

ሀገረሰባዊ ልማዶች የአንድ ህዝብ የባህል እና የእምነት መገለጫዎች ናቸው፡፡ልማዳዊ ህጎች ማህበረሰባዊ ስርዓት እንዳይናጋ፣ ተከባብሮ መኖር እንዲሰፍን፣ዘላቂ ሰላም እንዲኖር ወዘተ. የሚጫወቱት ሚና ከፍ ያለ ነው ፡፡የሃገረሰባዊ ልማድ እንደወግ ማዕረግ (የሕይወት ሽግግር) ፤ ሀገረሰባዊ እምነቶችና አምልኮዎች ፤ ሀገረሰባዊ መድሃኒቶች ፤ ሀገረሰባዊ ሃይማኖቶች ፣ ባሕላዊ መዝናኛዎች ጨዋታዎችና ሃገረሰባዊ ስያሜዎችንም ይጨምራል፡፡

### 2.1.2.3 ቁሳዊ ባህል

ቁሳዊ ባህል (Material Culture) አንዱ የባህል መገለጫ የሆነ የፎክሎር ዘርፍ ነው፡፡ በዚህ ዘርፍ ውስጥ የሚካተቱት በአይን የሚታዩ በእጅ የሚዳሰሱና በምላስ የሚቀመሱ ተጨባጭ የባህል አይነቶች ናቸው፡፡ እነዚህ ባህላዊ ቁሶች የማህበረሰቡን ፍልስፍና ፣ ታሪክ፣ እምነት፣ ሀይማኖት፣ ባህል ወዘተ መሰረት በማድረግ የማህበረሰቡን የዘመን ተሞክሮ አሻራዎች የሚያሳዩ የጥበብ ውጤቶች ናቸው፡፡

ሰለሞን (ሔነሪ ግላሲ ፣ 1968፣10) ን ጠቅሶ እንደገለፀው አንድ ማህበረሰብ የቁሳዊ ባህሎች እውቀትና የአሰራር ክህሎት ቁሶቹ ሲሰሩ በማየት፣ በማስታወስና በመስራት ከትውልድ ትውልድ ያስተላልፋል፡፡በአጠቃላይ ቁሳዊ ባህል የሰው ልጅ ከጥንታዊ ጋርዮሽ ስርአት ጀምሮ በባህላዊ መንገድ ድንጋርይ ጠርቦ ፤ እንጨት አለስልሶ ፣ጭቃ አብኩቶ፣ ብረት አቅልጦ ፣ቆዳ አልፍቶ ፣ ጥጥ ፈትሎ እንዲሁም ከተለያዩ የእፅዋት ቅርፊቶችና ስራስሮች ቀለም አዘጋርጅቶ የራሱን ጥበብ መሰረት በማድረግ የሚሰራቸው ልብሶች ፣ ጫማዎች ፣ ጌጣጌጦች፣ ቤቶች ፣ ድልድዮች ወዘተ ናቸው፡፡

በቁሳዊ ባህል የፎክሎር ዘውግ ስር ሀገረሰባዊ ሥነሕንጻ ፤ሀገረሰባዊ ጌጣጌጦችና ቅርጻቅርጾች ሀገረሳባዊ አልባሳት ፣ ሀገረሰባዊ ምግብና መጠጥ፣ ሀገረሰባዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች እና ባሕላዊ ቦታዎች ይካተታሉ፡፡

## 2.1.3 ፎክሎርና ስነ-ፅሁፍ

ፎክሎርና ስነ-ፅሁፍ እጅግ የተጣመሩ መስኮች ናቸው፡፡ ፎክሎርን ስናነሳ የፎክሎሩ ባለቤት የሆነውን ማህበረሰብ እናነሳለን ማለት ነው፡፡ ስነ-ፅሁፍ ደግሞ በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉትን የጋራ እውቀቶች፣ ጥበቦችና መረጃዎችን ሳቢ እና ማራኪ በሆነ መንገድ የሚገልፅበት ነው፡፡ ስነ-ፅሁፍ ሲወሳ ፀሀፊው አብሮ ይነሳል፡፡ ፀሀፊው ደግሞ ሲነሳ ለስነ-ፅሁፍ መነሻ የሆነው

ማህበረሰብ አብሮ ይነሳል ማለት ነው፡፡ ፎክሎር የአንድ ማህበረሰብ የረጅም ዘመናት ልምዶችን እና የባህል ውጤቶችን አቅፎ የያዘ በመሆኑ ለስነ-ፅሁፍ ውበትና መጎልበት ትልቅ ፋይዳ ይኖረዋል፡፡

ፎክሎርና ስነ-ፅሁፍ የአንድ ማህበረሰብ ባህል፣ እውቀት፣ ጥበብና ፍልስፍና የሚንፀባረቅባቸው የጋራ ሀብቶች ናቸው፡፡ እነዚህ ጥበቦች ከማህበረሰቡ የእለት ከእለት ህይወት ጋር የጠበቀ ግንኙነትና ትስስር ያላቸው ናቸው፡፡ የፎክሎር አንድ ዘውግ የሆነውን ስነቃልን ብንወስድ ለዘመናዊ ስነ-ፅሁፍ ቃላዊው ስነ-ፅሁፍ መሠረት እንደሆነ ይነገራል፡፡ ተረቶች ለአጭር ልቦለዶች፣ ቃላዊ ግጥሞች ደግሞ ለዛሬዎቹ ግጥሞች መሠረቶች ናቸው፡፡

በኢትዮጵያ ፎክሎርና ስነ-ፅሁፍ የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር ስር ከሚሰጡት የፎክሎር ኮርሶች አብዛኞቹ የሚያነሱት የፎክሎርን ዘርፈ ብዙ የሙያ መስክነት ሲሆን ፎክሎር ከስነሰብዕ፣ ከስነ ልሳን፣ ከስነ ፅሁፍና ከመሳሰሉት ሙያዎች ጋርየጠበቀ ቁርኝት ያለው መሆኑን ነዉ::

Finegan (1970) የፎክሎር አንድ ዘርፍ የሆነውን ሥነ ቃል በተመለከተ“ስነቃል ስነ-ፅሁፍ የሚገለፅበትን መንገድ ሁሉ ሊገለፅበት እንደሚችል በማሰብ ስነቃል ራሱን የቻለ ስነ-ፅሁፍ ነው፡፡ ስነቃል እንደስነ-ፅሁፍ ያስተምራል፣ ያዝናናል፣ የማህበረሰቡን እውነት ያንፀባርቃል፣ የራሱ መለያ ባህሪ አለው፡፡ በቋንቋ አማካኝነት ይገለፃል፡፡ የራሱ የዘርፍ አድናቂዎች አሉት፡፡”በተጨማሪም Finegan (1970፣25) “ስነቃል የስነ-ፅሁፍ ዘርፍ ሆኖ ክዋኔ፣ ተስተላልፎ፣ እና ማህበራዊ አውድን የሚይዝ መለያ ባህርይ አለው” ይላሉ፡፡

ፊቃደ ትውፊት ምንድነው በሚለው መጣጥፋቸውውስጥ አንድ ደራሲ አላማው ሕይወትን ማሳየት ፣መተርጎምና የወደፊቱን መጠቆም ስለሆነ የሚፅፈው ሁሉ ከህዝቡ ሕይወት ሊርቅ ወይም ጨርሶ ሊወጣ አይገባውም፡፡ የዛሬው የኢትዮጵያ ህዝብ በኑሮው ከትውፊት ዘርፎች ባንዱ እንኳ ሳይገለገል የማይውል ስለሆነ የዚህን ህዝብ ህይወት ሲቀርፁ ይህንን የህይወቱን ገፅታ አብረው ማሳየት እንዳለባቸውም ይገልፃሉ፡፡ Jani የዛሬ ስነፅሁፍ መገኛዉና መሰረቱ ቃላዊነቱ ነዉ፡፡ ስነፅሁፍ በዘፈቀደ የተገኘ ሳይሆን የረጅም ግዜ የፈጠራና የጥረት ዉጤት ነዉ በማለት እንዲህ ይገልፀዋል፡፡

> ጽሁፍ ማህበራዊ ህይወትን ለማንፀባረቅ እና የፀሐፊያንን ሐሳቦች እና ስሜቶች ለመግለፅ እንደ ቋንቋ የሚጠቀሙበት ስልት ነው፡፡ የስነ-ፅሁፍ መገኛው በቃል

ነው እሱም በአጠቃላይ ከሙዚቃ ጋር የተያያዙ እንደዝማሬ የዘፈን ግጥም አይነት ነበሩ፡፡ ስነ-ፅሁፍ ባህላዊና ማህበራዊ ክስተት እና የረጅም ጊዜ ፈጠራ ውጤት ነው፡፡ በተመሳሳይ ጊዜም ታሪካዊ ክስተት ነው ይህም ቁሳዊ ባሕልን, የተቋማዊ ባህልና የሥነልቦና ባህልን ይጨምራል "Jane Bin Sun,t Jun,(2018፣ 7)፡፡

በተጨማሪም Dundes የስነ ጽሁፍ መገኛዉ ስነቃል ከሆነ የሁለቱን የጋራ ባህሪያት አያይዞ ማጥናት ደግሞ ፎክሎር በስነ-ፅሁፍ ውስጥ ሲቀርብ ከነአውዱና ከነከዋኞቹ በመሆኑ ስሜት ሰጪነቱ አይጓደልም፡፡ ብሎም ፎክሎር በቃል ብቻ የሚገኝ ሳይሆን ከፅሁፍ ጥበብ ጋርም ግንኙነት ያለው በመሆኑ ይንንንም ግንኙነት አውጥቶ ለማሳየት ስነ ፅሁፍና ፎክሎርን አያይዞ ማጥናት ጠቃሚ ነው፡፡ እነዚህን የጥናት ዘርፎች በአንድ ላይ ማጥናት ደግሞ የደራሲውን ምናብ የመፍጠር አቅምም ለማወቅ ይጠቅማል፡፡ ምክንያቱም ድርሰቱ በተከየነባቸው ፎክሎራዊ ጉዳዮች ላይ ምን አይነት ኪናዊ ፈጠራ እንደታከለባቸው በግልፅ ማየት ስለሚቻል ነው ይለናል፡፡ Dundes (1990፣33)፡፡

Bennett በበኩሉ ፎክሎርና ሥነፅሁፍ ያላቸውን ዝምድና በሶስት መንገድ ይገለፃል "የመጀመሪያው ፎክሎር በቀጥታ እንደ ሥነ-ጽሁፍ ሲያገለግል (The use of folklore directly as literature) ሁለተኛው ደግሞ ፎክሎሩ በተለወጠ ቅርፅ እንደ ሥነ-ጽሁፍ ሆኖ ሲያገለግል (The use of folklore in a modified form as literature) እና የመጨረሻው ፎክሎሩ ለሥነ -ፅሁፍ መፈጠር እንደ ማተያያ ሆኖ ሲያገለግል (The use of folklore as a plane of reference in the production of literature) ነው" ይላል፡፡ Bennett.(1952፣33) ፡፡

ይህ ሃሳብ ሲብራራ ፎክሎር በሥነፅሁፍ ውስጥ ሲገኝ በሁለቱ መካከል ያለዉ ዝምድና ማለትም ፎክሎሩ በተገኘበት ቅርጽና ይዘት እንዳለ በጥሬው በመውሰድ በፅሁፍ ስራውውስጥ ማስፈር የሚለውን የሚገልፅ ሲሆን በምሳሌነት የቅኔ መፃህፍት፣የምሳሌያዊና ፈሊጣዊ አነጋገር የያዙ መጻህፍትንና ሌሎችንም የስነ ቃል ስብስቦች የያዙ የስነጽሁፍ መፃህፍትን መጥቀስ ይቻላል፡፡ ሁለተኛው ዝምድና የፎክሎራዊ ትልሙ ሳይለወጥ መቼት ፣ ገፀባህሪና ሌሎችም አላባውያን ታክለውበትና በነርሱ ላይ ኪናዊ ለውጥ ተደርጎባቸው ሲቀርብ ነው፡፡ ሶስተኛው ሃሳብ ፎክሎራዊ ትዕምርቶችን ደራሲው በፅሁፉ ለሚፈጥራቸው ሁነቶች ማለትም ለደራሲው ኪናዊ ፈጠራ ማተያያ ሞዴል አድርጎ ሲጠቀምባቸው ነውበዚህ

ወቅት ተደራሲው አዲስ ልምድና እውቀት ማግኘት የሚችልበትንም እድል ሊፈጥር ይችላል የሚሉ ትርጓሜዎችን ይይዛል ፡፡

ፈቃደ ትውፊት ምንድነው በሚለው መጣጥፉቸው ውስጥ እሳቤውን ፣ የደራሲውንና የሃያሲውን ተግባር እንዲሁም ትውፊት በስነ ጽሁፍ ውስጥ ያለውን ግልጋሎት እንዲህ ይገልፁታል

> ትውፊት በስነ-ፅሁፍ ውስጥ የሚለው እሳቤ ልዩ ልዩ የትውፊት ቅርጾችን ምሳሌ (ተረት፣እንቆቅልሽ፣አምልኮ፣ታሪክ ወዘተ) በልዩ ልዩ የፈጠራ ስራዎች ውስጥ ለምሳሌ (በግጥም፣ በልቦለድ፣በተውኔት ወዘተ) መገኘትን ወይም መግባትን የሚያመላከት ነው፡፡" ይላሉ በተጨማሪም አንድ ደራሲ ለድርሰቱ የሚያውለውን ትውፊት የሚያገኘው በተለያየ መንገድ እንደሆነና በቃል በሚነገርበት ቅርጹ ሊያገኘው እንደሚችል፤ በጽሁፍ አልያም በቴፕ ተቀርፆና ተሰብስቦ ሊያገኘው እንደሚችልና ሃያሲውም በተመሳሳይ በአንድ ድርሰትና የትውፊት ቅርጹ መሃል የሚታየውን ግንኙነት በተለያዩ መንገዶች ማግኘት እንደሚችል ለምሳሌ የደራሲውን የህይወት ታሪክ በማጥናት ደራሲው ምን ያህል ከትውፊት ጋርየተቀራረበ ህይወት እንዳለውና እውቀቱን ያገኘው በቀጥታ ወይስ በተዘዋዋሪ የሚለውን ለመረዳት ያችለዋል፡፡ ሌላው በድርሰቱ ውስጥ የትውፊቱ መገኛ ምክንያትንም ለመመርመር በድርሰቱ ውስጥ ትውፊቱ ያለው ልዩ ሚና ምንድነው የሚለውንም ለማጥናት ይረዳዋል ፡፡

ፍቃደ በማጠቃለያቸው ክፍልም ከአፍሪካ ደራሲያን መሃል ትውፊትን በልዩ ልዩ መልኩ በሥነ-ፅሁፍ ስራዎቻቸውውስጥ ሲያስገቡና ሲገለገሉ የሚገኙት ምዕራብ አፍሪካውያን በተለይም ናይጀሪያውያን እንደሆኑ ይጠቁማሉ፡፡ ለምሳሌነትም አቼቤ በልቦለድ ውስጥ ትውፊትን እንደሚጠቀም ቮይንካን ደግሞ በተውኔትና ግጥም ስራዎቹ ውስጥ ትውፊትን እንደሚያስገባ ያስቀምጣሉ፡፡ አቼቤ የልቦለዱን መቼት ለመሳል ፤ እንደ አስፈላጊነቱም ገጠራዊ ወይም የከተማን ለዛ ለማላበስ ፤ በትውፊት አማካይነት የልቦለዱን ጭብጥ በግልጽ ለማመላከት፤ ግጭቶቹን አጉልቶ ለማሳየት ፤ አጠቃላይ የማህበረሰቡን እሴት ለተደራሲያን ለማመላከት፤ የገፀ ባህርያት አቀራረጹን የተባ ለማድረግ ወዘተ ትውፊትን በድርሰት ስራውውስጥ እንደተገለገለበትና አቼቤ በተለይም "Arrow of God " በተሰኘው ስራ ውስጥ የተለያዩ የትውፊት ዘርፎችን በመገልገል በዘመኑ ትውፊትን ግልጽ፤ ቀላል፤ ውብና ፍሬያማ በሆነ መንገድ በመጠቀም የአጻፃፍ ቴክኒኩን ያበለፀገ በእንግሊዘኛ የሚፅፍ አፍሪካዊ ደራሲ መሆኑን ያስረዳሉ፡፡ በመቀጠልም በአማርኛ ሥነ-ፅሁፍ ውስጥ በብዛትም ባይሆን ትውፊት በልዩ ልዩ ቅርፁ ገብቶ የሚታይ መሆኑንና ወደፊት ግን በወጉ ተተንትኖ መሰራት እንዳለበት እየጠቆሙ ለማሳያነትም ከአማርኛ ልቦለዶች መሃል የላቀ የቴክኒክ

ብስለትና ብልጽግና ያለውን የዳኛቸው ወርቁን "አደፍርስ" የተሰኘ ልቦለድ ተጠቅመዋል፡፡ በአደፍርስ ውስጥ የትውፊቶች መግባት ያመጣውን ፋይዳ በሁለት መንገድ ያስቀምጡታል አንደኛው ብዙዎቹ ትውፊቶች የገቡት የአምልኮና እምነት ጉዳዮች ምን ያህል ከአምላኪዎቻቸው ህይወት ጋር የተቆራኙ መሆናቸውን ለማሳየት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የልቦለዱን የአጻጻፍ ቴክኒክና ጭብጡን ለማዳበር የገቡ መሆናቸውን ያስቀምጣሉ፡፡

## 2.1.3.1 ፎክሎር ለስነ-ፅሁፍ እድገት የሚያበረክተው አስተዋጽኦ

ፎክሎርን በስነ-ፅሁፍ ውስጥ መጠቀም በርካታ ጠቀሜታዎች ወይም ፋይዳዎች ይኖሩታል ሰለሞን ተሾመ Greenን (1997) ጠቅሶ እንደገለፀው ማንኛውም የፎክሎር ዘርፍ የሚፈጠረው አንዳች አገልግሎት (ጥቅም) ሊሰጥ መሆን ይገባዋል ይላል፡፡ከዚህ በመነሳት ፎክሎር ለስነጽሁፍ የሚሰጠውን ጠቀሜታ በተመለከተ ከዚህ በታች በጥቂቱ እንመለከታለን፡

በተለያዩ ዘመናት የተፃፉ ስነ-ፅሁፎች በዘመኑ የነበረውን ወግና ልማድ የሚያንፀባርቁ በመሆናቸው ሰዎች ይሄንን ባህልና ወግ ለማወቅ ካላቸው ጉጉት የተነሳ ብዙ ፅሁፎችን እንዲያገላብጡና የስነ-ፅሁፍ ተነባቢነት እንዲጨምር ሊያደርገዉ ይችላል፡፡ በተጨማሪም የተለያዩ የፎክሎር ዘሮችን በስነ-ፅሁፍ ስራዎች ውስጥ ማካተት ፅሁፉ ኪናዊ ውበት እንዲኖረዉና ፅሁፉ ከይዘት አንፃር ጉልበት እንዲኖረው ለማድረግም ይረዳል፡፡

አንድ ፀሃፊ በድርሰቱ ውስጥ የሚኖርበትን ማህበረሰብ ወግ፣ባህል፣ታሪክ አጉልቶ ለማሳየት አፈታሪኮችና ምሳሌያዊ አነጋገሮች ፈሊጦችን መጠቀሙ ከፍተኛ ጠቀሜታ ያላቸው በመሆኑ ማህበረሰቡ ባህሌንና እኔነቴን የሚገልፅልኝ የራሴ ስነ-ፅሁፍ አለኝ ብሎ እንዲያስብ ያደርጋል፡፡በተለይም የተለያዩ የፎክሎር ዘሮችን በመጠቀም የማስተማሪያ መፅሃፍ ዉስጥ ለሚዘጋርጁ ለስነ ፅሁፋ ይዘት ያላቸዉ ምንባቦችን ያለ ችግር ለማዘጋጀት ብሎም ምንባቡ ሳቢና ተነባቢ እንዲሆን ያደርገዋል ፡፡

## 2.1.3.2 ስነ-ፅሁፍ ለፎክሎር እድገት የሚያበረክተው አስተዋጽኦ

ፎክሎር በባህሪው በቦታ፣ በጊዜና በመከወኛ አጋጣሚው ተለዋዋጭ በመሆኑ በአንድ አጋጣሚ ያገኘነውን የአንድ ማህበረሰብ የማንነት መገለጫ የሆነ ወግ፣ታሪክና ባህል በሌላ ጊዜ ስናገኘው ተበርዞና ተከልሶ አልያም ከነአካቴው ጠፍቶ ልናገኘው ስለምንችል በተለያዩ

ጊዜያት ወደ ሰው በሚደርሱ የህትመት ስራዎች ውስጥ ማካተቱ ከዚህና መሰል አደጋ ሊታደገው ይችላል ፡፡

የአንድን ማህበረሰብ ባህል፣ ወግና፣ ልማድ ፤ እምነቱን ፤ስነቃሉን ፤የተለያዩ እደ ጥበብ ውጤቶቹን ወዘተ በተለያዩ የፈጠራ ስራዎች አዋዝቶ መጠቀም አንባቢያን ድርሰቱ ከተፃፈበት ማህበረሰብ ማንነት ጋር እንዲተዋወቁ ከማድረጉ በተጨማሪ በምንም አጋጣሚ ወደ ስፍራው ቢመጡ እንግዳ የሆነ ስሜት እንይሰማቸው ብሎም በማህበረሰቡ ዘንድ የሚከለከሉና የሚፈቀዱ ጉዳዮችን ቀድመው በመረዳት ተግባራዊ እንዲያደርጉ ያግዛል ፡፡

በተለይም የአንድ ማህበረሰብ አጠቃላይ ባህል በመሰል *ሥነ-ፅሁፋዊ* ስራዎች ውስጥ መካተቱ ምንአልባትም መጽሃፍቱ በዓለም ቋንቋ ተተርጉመው የሚሰራጩበት አጋጣሚ ቢኖር የዚያ ማህበረሰብ ወግና ባህል በዓለም ደረጃ ከመታወቁ ጋርተያይዞ በርካታ ጎብኚዎች ወደ ስፍራው እንዲመጡ ሊያደርግ ስለሚችል ለባህሉ መጠበቅ ክትትልና ድጋፍ የሚያደርጉ አካላት የሚበራከቱበት ሁኔታም ይኖራል፡፡ የዚህ ባህል መጠበቅ ደግሞ ለአካባቢውም ሆነ ለሃገር ከፍተኛ ገቢን ሊያስገኝ ይችላል፡፡

### 2.1.3.3. የጥናቱ ትወራ

በዚህ ጥናት ውስጥ ተግባራዊ የተደረገው "በይነ-ፅሁፋዊ" *Inter-textuality*[1]ንድፈ ሃሳብ ሲሆን የመተንተኛ ስልቱም ፍከራነው፡፡ የስነ-ፅሁፍ ጥናት የተለያዩ የአጠናን ስልቶች አልፎ በበይነ-ዲሲፕሊናዊ ፈር በሚቀናጅበት በዚህ ወቅት "በይነ-ቴክስታዊ" ሂደትን መከተል ዋናየሂስ ማጠንጠኛ የቴክስቶችን ዘርፈ ብዙነት ማሳያ ሆኗል፡፡ አንድን ቴክስት በነጠላ ፍቺ ከማየት ይልቅ "ህያው" ከሆነው የባህል ትርጓሜ አንፃር እያዋደዱ ማየቱ ተገቢ ይሆናል፡፡ ስለሆነም ይህ ጥናት *Intertextuality* ዘዴን በመጠቀም ታላሚ የሆኑትን ሁለት የሥነ ጽሁፍ ስራዎች ከባህላዊ አስተማስሎዎችና ከሌሎችም ተጓዳኝ ጉዳዮች ጋር በማናበብ የሚያይ ይሆናል፡፡

---

[1] በዚህ ጥናት ውስጥ "በይነጽሁፋዊ" የሚለው ቃል Intertextuality የሚለውን የእንግሊዘኛ ቃል ተክቶ ያገለግላል፡፡ Intertextuality ማለት (Mingle while weaving) ወይም "የተቀየጠና ከተለያዩ ሁኔታዎች አንጻር የሚታይ" ማለት ሲሆን ባዩልኝ አያሌው 2008 ዓም በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት ባቀረበው ጥናት ላይ ይህንኑ ቃል ለፅንሰ ሃሳቡ መጠሪያነት መጠቀሙን ለማየት ተችሏል፡፡

Intertextuality ልክ እንደ Litrary እና Cultural ቲዎሪ ሁሉ መታየት የተጀመረው ከ20ኛው ክፍለ ዘመን በኋላ ሲሆን እንደ Ferdinad(1857-1913) አመለካከት የ Intertextuality ዋና አላማ መሆን ያለበትና አንድ የየስነ-ፅሁፍ ስራን ለመሂስ ትኩረት ማድረግ ያለብን በገጸ ፅሁፉ ላይ ብቻ ነው "Ferdinand de Saussure(1857-1913) by emphasaizing the systematic features of language , he established the relational nature of meaning and text"**ሲል** በተቃራኒው ሌላው ሊትራሪ ቲወሪስትና የሩሲያው ፈላስፋና የ Litrary Critisim ት/ቤት መስራች የሆነው **Bakhtin**(1895-1975) **በበኩሉ** Another litrary theorist who had a major influence on the theory of Intertextuality was the Russian litrary theorist and Philosopher Mikhail Bakhtin (1895-1975) He Emphasaized the relation between an outer and hiswork, the work and its readers, and the relation of all social, historical force that surround them." Bakhtin (Intertextuality) ማለት አንድን የስነ-ፅሁፍ ሥራ ለመሂስ ትኩረት ማድረግ ያለብን ከገፅ ፅሁፉ በተጨማሪ በፀሃፊውና በስራው ፤ በስራውና በአንባቢው መካከል ያለውን ግንኙነት ፤ እንዲሁም ማህበራዊ ፣ ታሪካዊና አካባቢያዊ አውዱን ሁሉ ከግምት ውስጥ ማስገባት ግድ ነው ይላል፡፡

በመቀጠልም የሁለቱን ሃሳብ ይዛ የ (Post Structuralism) ተከታይና ፈረንሳይቷ የነገረ ትዕምርት ተመራማሪ ጁሊያ ክሪስቲቫ (ከ1941-1980) Intertextuality ቲዎሪን ማስተዋወቅ ቻለች፡፡ ክሪስቲቫ Intertextuality የሚለው ቃል የላቲን ቃል መሆኑንና ትርጓሜውም (Mingle while weaving) "የተቀየጠ ወይም ከተለያዩ ሁኔታዎች አንፃር የሚታይ" ማለት ነው ትላለች፡፡

ክሪስቲቫ በጥናቷ በቴክስቶች ውስጥ የሚገኘው ግንኙነት Horizontal እና Vertical መሆኑን በመግለፅ በቴክስት ውስጥ ያለውን ምልልስ የሚፈጥሩት ሶስት አካላት የጽሁፉ ጉዳይ፣ ተደራሲው እና ከቴክስቱ ውጭ ያሉ ሁኔታዎች እንደሆኑ አስረድታለች፡፡

ክሪስቲቫ በማንኛውም ቴክስት ውስጥ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ሌሎች ቴክስቶች ይገኛሉ፣ የትኛውም ቴክስት የተፈጠረው ከሌሎች ቴክስቶች ውህድና ህብር ነው ትላለች፡፡

ክሪስቲቫ በይነ ቴክስታዊነት ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ከምንጭ ጥናት ጋር ተያይዞ እየተነሳ መሆኑን ሆኖም በቴክስቶች ውስጥ የሚታየው መወራረስ ወይም ግንኙነት እንዲሁም

በቋንቋም ሆነ በተረክ ውስጥ የሚከሰተው በይነቴክስታዊነት የቅንብር ለውጥና ቅመራም ጭምር መሆኑን ታስረዳለች፡፡

እንደ ጁሊያ አመለካከት በይነ ቴክስታዊነት በቴክስቶች ላይ በሁለት ምክንያቶች ሊፈጠር ይችላል፡፡ አንደኛው አዲሱ ቴክስት እንዲነበብና ተቀባይነት እንዲያገኝ ለማድረግ ከአንድ በሰፊው ተቀባይነትን ካገኘ ወይም በብዛት ከተነበበ ቴክስት ጋር በማዛመድ የሚፈጠር ሲሆን ይህም ለአዲሱ ቴክስት እውቅና ለማስገኘት ሲባል ይሁነኝ ተብሎ የሚደረግ ነው፡፡

ሁለተኛው በይነቴክስታዊነት የሚፈጠርበት ምክንያት ደግሞ አንዳንድ ጊዜ በአዲሱ ቴክስት ላይ ከዚህ በፊት የነበረ ሌላ ቴክስትን መገልገላችን የግድ ሲሆን ነው፡፡ በዚህ ምክንያት የሚፈጠረው በይነቴክስታዊነት ለአንዳች ፋይዳ ሲባል የግድ ሆኖ ሲገኝ የሚካሄድ ብቻ ነው፡፡ ከእነዚህ ምክንያቶችም ውጭ አንድ ቴክስት ከሌሎች ቴክስቶች ጋር ባጋጣሚ በይነቴክስታዊነት ሊፈጥር ይችላል፡፡ ይህም የሚያመላክተው መፈጠሪያ መንገዶች በርካታና ውስብስብ በመሆናቸው ነው፡፡

የዚህ ጥናትም አንድምታ ለጥናት የተያዙት ሁለት  ልቦለዳዊ ስራዎች በአንድም ሆነ በሌላ መልኩ ከዚህ ቀደም ከተፃፉ የልቦለድ ስራዎች ጋር የሚዛመዱ ሆነዉ ተገኝተዋል፡፡ ይህም የቴክስቶችን መጠራራት ያሳያል፡፡ ለምሳሌ ለጥናት የተመረጠዉ የእንዳለ ጌታ ከበደ በ2006 የታተመው *እምቢታ* ልቦለድ ዉስጥ ዋናዋ ገፀ-ባህሪ የቃቄ ወርድወት እና በ1983 የታተመው የገብረየሱስ ሀይለማሪያም የጫሙት ሸካ በሚል የጉራግኛ ልቦለድ ውስጥ ያለችው ዋናዋ ገፀ ባህሪ ጫሙት ጋር የሚያመሳስላቸው ሚታዊ ገፅታ አሉት፡፡

የቃቄ ወርድወት በዘመኗ በጉራጌ ሴቶች ላይ ይደርስ የነበረውን ጭቆና ለማስቀረትና ከወንዶች እኩል እንሁን የሚል ጥያቄን በመያዝ በታላቁ የእጀካ ሸንጎ ፍርድ የምትሟገትና አንቂት ሳይኖርባት ከባህሉ ዉጭ ያልፈለገችዉን ባል ፈታ የመረጠችዉን አግብታ የምትኖር ጀግና ሴት ነች፡፡ በተመሳሳይ ጫሙት ከስሚ ትርጓሜ እንኳን ብንነሳ ሀይለኛ የሚል ፍቺ ያለው ሲሆን በፍቃዷ ባሏን ፈታ ቤተሰቦቿ ጋር የምትኖር ሴት ነች፡፡ ሁለቱም ሴቶች በባህሉ መሰረት ያልተፈቀደ ተግባር ሲያከናውኑ ይታያሉ፡፡ ለጋብቻ ጥያቄ መልስ የሚሰጡትና የሚወስኑት ሽማግሌዎች ሳይሆኑ ራሳቸው መሆናቸው፤ በራስ መተማመናቸው ከፍ ያለ፤ጀግና ተብለው በማህበረሰቡ ዘንድ የሚከበሩ ወንዶችን

የሚያሸንፉ፣ በባህል አፈንጋጭነታቸው የሚመሳሰሉና ለራሳቸው የሚሰጡት ግምት ከፍ ያለና በሰዎች ዘንድ የሚወደዱ መሆኑ ያመሳስላቸዋል፡፡

በሁለተኛዉ ስራ ዉስጥም በተመሳሳይ የቴክስቶች መጠራራት የሚስተዋል ሲሆን በ2005 ዓ.ም የተፃፈዉ የአንዷለም አባተ *መኤኒት የተሰኘዉ ልቦለድ በ1987 ዓ.ም በፍቅረማርቆስ* ደስታ የታተመዉ ከቡስካዉ በስተጀርባ የተሰኘዉ ስራ ጋር ተዛምዶ ያለዉ መሆኑ ታይቷል፡፡ ሁለቱም ኢትኖግራፊክ የሚባለዉን አፃፃፍ የተከተሉ ሲሆን ደራሲያኑ ወደ ማህበረሰቡ ዘንድ በመሄድ እንደ ባህሉ ኖረዉ ከሚከለከለዉ ተከልክለዉና በሚፈቅደዉ ተመርተዉ የፃፉት ሲሆን በመኤኒት ልቦለድ ዉስጥ ዋናዉ ገፀ ባህሪ አለምሰገድ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪ ሲሆን ለባህል ትልቅ ክብር ያለዉ ሰዉ ነዉ፡፡ ይህንንም ተግባራዊ ለማድረግ ወደ ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ መኤኒት ብሄረሰብ ዘንድ ተጉዞ ከማያዉቀዉ ባህልና ማንነት ጋር ተላምዶ ተጨባጭ ጥናት ለማድረግ ይታትራል ፡፡ በተመሳሳይ የቡስካዉ በስተጀርባ ዋና ገፀ ባህሪ ካርለትም ከእንግሊዝ ሃገር የመጣችና ለአካባቢዉም ሆነ ለባህሉ አዲስ የሆነች እርሷም ለባህል ትልቅ ክብር ያላት የዩኒቨርሲቲ ተማሪ ስትሆን የመጣችበትን ዓላማ ለማሳካት ሴትነቷና የባህልም ሆነ የአኗኗር ልዩነት ሳይገድባት የምትታትር ሴት ነች፡፡

በሌላ መልኩ ሁለቱም ዋና ገፀ ባህርያት ለጥናት ወደ ማህበረሰቡ ዘንድ የሄዱት ስለማህበረሰቡ መልካምነት እና ስለባህሉ አስደናቂነት በተደጋጋሚ በመስማታቸዉ የባህሉ ባለቤቶች ጋር ደርሰዉ የተባለዉን በተግባር ለማረጋገጥ ካላቸዉ ፅኑ ፍላጎት ሲሆን ለጥናት በሚሄዱበት ወቅትም አለምሰገድ ፍራኦልን ካለርትም ካሉ ሆራን አጋዥ አድርገዉ መሄዳቸዉ፣ ካሉ ሆራ ሚንጊ ተብሎ በማህበረሰቡ ተገሎ የኖረ ሰዉ ሲሆን በተመሳሳይ በመኤኒት ብሄረሰብ ዘንድም በተለያዩ ምክንያቶች ከማህበረሰቡ ተገለዉ የሚኖሩ እንዳሉም ለማወቅ መቻሉ የታሪክ ተዛምዶ እንዳላቸዉ ያሳያል፡፡ በአጠቃላይ ለጥናት የተመረጡት ሁለት ስራዎች ከዚህ ቀደም ከተፃፉ ስራዎች ጋር በተለያየ ምክንያት ሲዛመዱና ቴክስቶቹም ሲዋሃዱ በመገኘታቸዉ ለዚህ ጥናት በመተንተኛነት Intertextuality ንድፈ ሃሳብ አገልግሎት ላይ ዉሏል፡፡

ከዚህ በተጨማሪነትም እንደ ጁሊያ ክሪስቲቫና ተከታዮቿ አመለካከት አንድ የስነ-ፅሁፍ ስራ ማለት ራሱን ብቻውን ችሎ ሊጠና የማይችል ቋሚ ያልሆነ ብቻውን ምሉዕ ያልሆነና አንድን የስነ-ፅሁፍ ስራ ለመሄስ በሁለት ቴክስቶች መካከል ያለዉን ግንኙነት ከመፈተሽ

ዉ-ጭም Intertextuality በስነ-ፅሁፍ ሲታይ ከተፃፍት በተጨማሪ ከሌሎች ጥበቦች ጋር ያለው ዲሲፒሊናዊ ግንኙነትም ከግንዛቤ ውስጥ መግባት አለበት "Intertextuality has been adapted by critics of non literary art forms, such as painting, music, architecture, photography or even film. Through the use of Intertextuality employed by other art forms, traits of society or period of history can be captured not only in the written form." ይላሉ።

በአጠቃላይ አንድን የስነ ጽሁፍ ስራ ለመረዳት ደራሲ የሚፅፈው የራሱን ፈጠራ ብቻ ሳይሆን ከተለያዩ መፃህፍት ያነበበውን ፣ የዘመኑን መንፈስ ተንተርሶና በእውኑ አለም የማህበረሰቡን አጠቃላይ ባህል፣ አኗኗር፣ የህይወት ፍልስፍናውን ወዘተ በመፈከር በመሆኑ ለጥናቱ በተመረጡት ስራዎች ውስጥ ደግሞ ተስተላልፏቸው በቃል ፣ በቁስና በድርጊት የሚገለፁ የፎክሎር ዘርፎች ከቴክስቱ ጋር በመላመድ የተገለፁበት አግባብ በመኖሩ ከላይ በነክርስቲቫ እንደተገለፀው ሥነ-ጽሁፍ ተጽፈው ከሚገኙት በተጨማሪ ከስነ-ስዕል ፣ ከሙዚቃ ፣ ከቅርፃ ቅርፅ ፣ ከፎቶግራፍና ከሌሎችም ጥበባት ጋር የተላመደ በመሆኑ በልቦለዶቹ ውስጥ የሚገኙትን እነዚህን ፎክሎራዊ ጉዳዮች በመለየትና ለሥነ-ፅሁፋዊ ስራው የሚሰጡትንም ፋይዳ በመፈተሽ ሥነ-ጽሁፍ ከሌሎች ጥበቦች ጋርመጠናት እንደሚችል ለማመላከት ጥናቱ በዚህ ንድፈ ሃሳብ ተቃኝቷል ፡፡

## 2.2 የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

በዚህ ክፍል የቃኘኋቸው ጥናቶች በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነጸሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ተማሪዎች ሁለተኛና ሶስተኛ ዲግሪ ማሟያ ያቀረቧቸውን የጥናታዊ ጽሑፍ ሥራዎች ሲሆን አምስት ያህል ናቸዉ፡፡

የመጀመሪያው ታደሰ ሺበሺ "ሚቶሎጂያዊ ጥናት እቴሜቴ ሎሚ ሽታ እና ይወስዳል መንገድ ያመጣል መንገድ በተሰኙ የአዳም ረታ መድበሎች" በሚል ርዕስ ለኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ በ (2005) የቀረበ ጥናት ሲሆን

የታደሰ ጥናት፣ በመረጣቸው መድበሎች ውስጥ የተደራጁ ሚቶሎጂያዊ ጉዳዮች ለሥነ ጽሑፋዊ ስራው ያበረከቱትን አስተዋጽኦ መመርመር በአቢይ አላማነት፣የሚታዊ ጉዳዮችን አቀራረብ፣የአዳምን ሚቶ ከያኒነት እና የሚያነሳቸውን ጭብጦች መመርመር ደግሞ በንዑስ አላማነት ይዞ የተነሳ ነው፡፡የምርምር ጥያቄዎችም ከአላማዎች ጋር የተሳሰሩ ሲሆኑ

ለትንተናው የሚያግዘው ንድፈ ሃሳባዊ ዳራም አበጅቷል፡፡ ስለሚት ምንነትና አመጣጥ፣ስለ በይነዲሲፕሊናዊነቱና ስለ ሚቶኪን ሰፊ ማብራሪያ ከሰጠ በኋላ የሚትን ናየስነ-ፅሁፍ ንግንኙነት አስፍሯል፡፡ የታደሰ ትንተና በሦስት አቢይ ጉዳዮች ላይ ያረፈ ነው፡፡ የመጀመሪያው የ"ተቃራኒዎች መቃለጥ" ነው፡፡ አዳም ሰርካዊ የሆነውን የሚት ትልም ማዋቀሪያ፣ የተቃራኒ ስሜቶችን መዋሃድ፣ለሥነ ጽሑፋዊ ሥራዎቹ የትልም ማዋቀሪያነት እንደሚገለገልባቸው አሳይቷል፡፡

በመጨረሻው የትንተናው ክፍል "ሚታዊ ጉዳዮች በልጆች ጨዋታ" የሚል ርዕስ አበጅቶ "እቴሜቴ የሎሚ ሽታ" የሚለው የልጅነት ጨዋታ እቴሜቴ ሎሚ ሽታ የተሰኘ መድበል እንዴት እንዳዋቀረ ተመልክቶበታል፡፡ በማጠቃለያው አዳም ለሥነጽሑፋዊ ስራዎቹ ማደራጃ ሚቶሎጂን፣ ሚታዊ ቋንቋን፣ምናባዊ ደራሲና ምትሃት የአጻጻፍ ብልሃቶችን ለሃሳቡ ማሂጃነት እንደሚገለገልባቸውና ሚታዊ ትዕምርትን ለሥነጽሑፋዊ መዋቅርና ጭብጥ ማበልጸጊያነት እንደሚያውላቸው አሳይቷል፡፡

ሁለተኛው የአገኘሁ አዳነ ሥዕል፣ሠዓሊነት እና ሠዓሊ ገጸባሕርያት በተመረጡ የአማርኛ ዘመናዊ ልብወለዶች ውስጥ በሚል ርዕስ ለኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ በ (2007) የቀረበ ጥናት ሲሆን ተጠኚ ልቦለዶቹም ማሕሌት (1981)፣ግርዶሽ (1981)፣ ከአድማስ ባሻገር (1962) እናአደፍርስ (1962) ናቸው፡፡

ጥናቱም ረጅም ልቦለዶች ውስጥ ሥዕል እና ሠዓሊነት በምን ሁኔታ እንደቀረቡ፤ሠዓሊ ገጸባሕርያት እንዴት እንደተቀረፁ፤ የሥዕል እና ስነ-ፅሁፍ ዲሲፒሊናዊ ተጋቦት በልቦለዶቹ ውስጥ በምን መንገድ እንደተስተማሰለ ለመመርመር የሞከረ ነው፡፡የስነ-ፅሁፋዊ ጥናት አስፈላጊነቱም ሥዕል፣ሠዓሊነት እና ሠዓሊ ገጸባሕርያት በልብወለዶቹ ውስጥ በጭብጥነት በተደጋጋሚ የታዩ በመሆናቸው መሆኑን ይገልፃል፡፡

አገኘሁ በቆየው የስነ-ፅሁፍ ልማድ፣ሥዕልን" በአጃቢነት" በተለያዩ ኪናዊ ፋይዳዎች መገልገል የተለመደ ነው በማለት ቀደምት ሥነ ጽሑፋዊ ኪኖች"...ታሪክን መልሶ ለመተረክ ፤ገጸባሕርያትን ከአካባቢው ጋር ለማቀራረብ ፤መቼቶችን ተጨባጭ ለማድረግ ፤ የታሪኩን አጠቃላይ ድባብ ለመቅረጽ፤ ወዘተ በሥዕል መታገዙን ይገልፃል፡፡

"ሥዕል፣ ሠዓሊነት እና ሠዓሊ ገጸ ባሕርያት በተመረጡ ዘመናዊ የአማርኛ ልቦለዶች ውስጥ" በሚለው በዚህ ጥናት ሥዕልን የተመለከቱ ጽንሰ ሃሳቦች ፤ነገረ-ኪንና የኪነ ጥበባት

ንድፈ ሃሳቦች ፤በልቦለዶቹ አውድ ውስጥ የዕይታዊ ቴክስቶች (visual texts) ፋይዳና ሚና እንዲሁም የሥዕልና የስነ-ፅሁፍ የወል ተጋቦት ተመርምረውበታል፡፡

የታደሰና የአገኘሁ ጥናቶች ከዚህ ጥናት ጋር የሚወዳጁት የሶስታችንም ልዩ ትኩረት የሆነው ከተለምዷዊው የልቦለድ አላባውያን ተገቢነትና ኢተገቢነትን ከመመርመር በዘለለ የስነ ፅሁፍን ፈርጀ ብዙ የጥናት መስክነት(በይነ ዲሲፒሊናዊነት) በማሳየት ሥነ ጽሁፍ በይነ ዲሲፒሊናዊ ንባብ እንደመሆኑ ከሌሎች ዘርፎች ጋርም መጠናት እንደሚችል መጠቆምላይ መሆኑ ሲሆን ከልቦለድ ስራዎቹ ምርጫ መለያየት፣ ስነ-ፅሁፍን ያዛመድንበት መንገድ (ከሚቶሎጂ፣ ከሥዕልና ከፎክሎር) ጋር መሆኑ ብሎም በአላማ ይዘነው የተነሳነው ሃሳብ እና የተጠቀምነው ንድፈ ሃሳባዊ ቅኝት ለየቅል በመሆኑ ጥናታችንን ያለያየዋል፡፡

ሶስተኛውና ከዚህ ርዕሰ ጉዳይ ጋር ተቀራራቢ የሆነው የአዳነች አበራ "የፎክሎር ቅርፅና ፋይዳ በተመረጡ የታሪክ መፃህፍትና ዜና መዋሎች ውስጥ" በሚል ርዕስ ለኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያበ (2001) የቀረበጥናት ሲሆን ጥናቱ ፎክሎር በተመረጡ የታሪክ መፃህፍትና ዜና መዋዕሎች ውስጥ በምን ቅርፅ እንደገባ በማሳየት ፋይዳውን መተንተን የሚል አላማ ሲኖረው በንዑስነትም የፎክሎር ቅርፆች በምን ሁኔታ ሊገቡ እንደቻሉ ማለትም ደራሲው ሆን ብሎ የፃፋቸው ናቸው ወይስ እንደክስተት የዘገበው የሚለውን ይመረምራል፡፡ በተጨማሪም በታሪክ መፃህፍቱና በዜና መዋዕሉ ውስጥ ያለውን አንድነትና ልዩነት በንፅፅር ይመለከታል ፡፡

የአዳነች ጥናት የሚነግረንየአማርኛ ስነ-ፅሁፍ ካበበበት የዘመናዊነትና የማዕከላዊነት ፅንሰ ሃሳብ ተግባራዊ መሆን ጀመረበት ከሚባለው ከአጼ ቴዎድሮስ ዘመን እስከ አጼ ሃይለ ስላሴ ዘመን ፍጻሜ ድረስ ያለውን ታሪክ የሚወክሉ የታሪክ መፃህፍትና ዜና መዋዕሎች ላይ ማተኮሩንነው፡፡ለጥናቱ ተገቢ ብላ የመረጠቻቸውመፅሀፍትን በአላማ ተኮር ንሞና መመረጣቸውንና የተነሳችበትንም አላማ ለማሳካት አምስት የታሪክ መፃህፍትንና ሁለት ዜና መዋሎችን መርጣለች፡፡ በተመረጡት የታሪክ መፃህፍትና ዜና መዋዕሎች ውስጥ አራቱንም የፎክሎር ዘውጎች ማግኘት እንደቻለችና የአራቱንም ፋይዳ ተመልክታለች ፡፡

አዳነች በንዑሳን አላማዎቿ ላይ ባስቀመጠችው የታሪክ መፃህፍትና ዜና መዋዕሎች ውስጥ ጎልተው የሚታዩትን ፎክሎራዊ ጉዳዮች በመለየት፣ ፋይዳቸውን መመርመር እና ፎክሎርን ከሌሎች ዘርፎች ጋርያለውን ትስስር እስከምን ድረስ እንደሆነ ማሳየት እንዲሁም ከላይ

የታደሰና የአገኘሁጥናቶች ከዚህ ጥናት ጋር ያላቸውን ተዛምዶ በታየበት ልክ በዚህ ጥናትና በአዳነች ጥናት መሃል ያለው ተመሳስሎ ሲሆን ይህ ጥናት ሥነ-ፅሁፍንና ፎክሎርን ማዛመዱ የአዳነች ጥናት ደግሞ የታሪክ መፃህፍትና ዜና መዋዕሎችን ከፎክሎር ጋርማዛመዱ እንዲሁም አዳነች የተጠቀመችው ምንም አይነት ንድፈ ሃሳብ ያለመኖሩና በዚህ ግን የ Intertexuality ንድፈ ሃሳብ በመተንተኛነት አገልግሎት ላይ የሚዉል መሆኑ ልዩነታችን ነው፡፡

አራተኛው ስራ የወሰን ባዩ "በኢትዮጵያ ቴአትር የተነሱ ፎክሎራዊ ጉዳዮች ፋይዳ በተመረጡ ተውኔቶች ማሳያነት" በሚል ርዕስ ለኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ለፒ. ኤች.ዲ.ማሚያ (በ2010) የቀረበ ጥናት ሲሆን የጥናቱ ዋና ዓላማ በኢትዮጵያ ቴአትር ውስጥ የተነሱ ፎክሎራዊ ጉዳዮችን ፋይዳ በተመረጡ ተውኔቶች አስረጂነት ማሳየትነው፡፡ የፎክሎራዊ ጉዳዮችን ይዘት መግለፅ ፤በአንዳንድ ተውኔቶች ውስጥ የተነሱት ፎክሎራዊ ጉዳዮች ከዘመን አንፃር የሚገልፁትን መልዕክት ማወቅ ፤ በተውኔቶቹ ውስጥ የቀረቡት ስነ ቃላዊ ጉዳዮች ከቀረበው ተውኔት ጭብጥ ጋር አንዳች መስተጋብር እንደፈጠሩ ተንትኖ ማሳየት ደግሞ ለጥናቱ በንኡስነት የቀረቡ አላማዎች ናቸው፡፡

ወሰን በጥናቱ የፎክሎርን ፋይዳ በተሻለ መልኩ ሊያሳዩ ይችላሉ ያላቸውንና በአጥኚው የታመነባቸውን ሰባት ያህል ተውኔቶች እንደመረጠና መረጃዎችን በሚገባ ለማግኘትና ለማደራጀት እንዲረዳው ከተውኔቶቹ በተጨማሪ ሁለት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችን ማለትም ሰነድ ዳሰሳና ቃለመጠይቅ እንዳደረገ ይገልጻል፡፡በዚህ ጥናት ግን መረጃ የሚሰበሰበው ለጥናት ከተመረጡት ሁለት ሥነ-ፅሁፋዊ ስራዎች ብቻ ነው፡፡ ይህ ደግሞ የጥናቶቹ ልዩነት ነው፡፡

በወሰን ጥናት ውስጥ ከዛሬ 150 ዓመት በፊት ቃቂ ወርድወት የተባለች ሴት በጉራጌ ባህልና ታሪክ ውስጥ ተጽእኖ መፍጠሯንና አዎንታዊ አስተዋጽኦ ማበርከቷን መጥቀሱ በዘመኑ የነበሩ አንዳንድ ባህላዊ ጉዳዮች ለምሳሌ ምርቃት፣እንቂት፣ ጀፎረና እጀካ የተሰኙ ፎክሎራዊ ጉዳዮችን መዳሰሳቸው ለጥናት ከያዝኩት ስራ ውስጥ እምቢታ ከተሰኘው ታሪካዊ ልቦለድ ጋርተመሳስሎ መኖሩ በሁለታችን ስራዎች መሃል ያለው አንድነት ሲሆን ለጥናት የተያዘው ርዕሰ ጉዳይን በተመለከተ ከስነ-ፅሁፍ ዘርፎች ውስጥ በልቦለድም በተውኔት መልክም በመዘጋጀት አሁን ላይ ያለበትን ደረጃ ለማወቅ አስችሏል፡፡

የወሰን ጥናት በተመረጡት ሰባት ተውኔቶቹ ውስጥ የተነሱትን ስነ ቃላዊና ሃገረሰባዊ ጉዳችን በማጥናት ላይ ብቻ የተገደበ ሲሆን ይህ ጥናት ከነዚህ በተጨማሪ ቁሳዊ ባህሎችን በስፋት የሚያይ መሆኑ ልዩነታችን ሲሆን በተጨማሪም የጥናቱ ትኩረት ፍክሎራዊ ጉዳዮቹ ለተውኔቱ የሚያበረክቱትን አስተዋጽኦ ማመልከት ሳይሆን የፎክሎራዊ ጉዳዮቹ ለቀረቡበት ማህበረሰብ የሚሰጡትን ፍይዳማሳየት ላይ መሆኑ ይህ ጥናት ግን ፎክሎራዊ ጉዳዮቹ ለሥነ-ፅሁፍ ስራው ያበረከቱትን አስተዋፅኦ መፈተሽ መሆኑና በወሰን ጥናት ውስጥ ቅድሚያ ፎክሎራዊ ጉዳዮቹን የመለየት ስራም ያልተሰራ መሆኑ የሚያለያዩን መሰረታዊ ጉዳዮች ናቸው፡፡

- የመጨረሻውና ለተዛማጅነት የቀረበው ጥናት የሊዲያ ተካ "ፎክሎር በጫሙት ሸካ እና በተኬነት- አጃነት አንኪ የጉራጊኛ ልቦለዶች ከማንነት ፅንሰ ሃሳብ አንፃር"፡፡ በሚል ርዕስ ለኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ በ (2005) የቀረበጥናት ሲሆን የሊዲያ ጥናት ዋና ዓላማ በጫሙት ሸካ እና በተኬነት-አጃነት አንኪ የጉራጊኛ ልቦለዶች ውስጥ ፎክሎር የማህበረሰቡን ማንነት(Identity) ለመፍጠር በምን መልኩ አገልግሎት ላይ እንደዋለ ማሳየት ሲሆን የልቦለዶቹን ዘውጎች መለየት፤ የፎክሎር ዘውጎቹ በቀረቡበት አውድ ትርጉም መስጠትና የልቦለዱን ጭብጥ ከፎክሎራዊ ዘውጎች ትርጓሜ ጋርያለውን ተዛምዶ ማሳየትን በንዑስነት አላማ አድርጋ ይዛቸዋለች፡፡

ሊዲያ ለጥናቷ የተገለገለችው የሥነ-ማህበራዊ አቀራረብን (Sociological Approach) ሲሆን የጥናቷ ዋና ትኩረት ሥነ-ጽሁፍ የተበጀበትን ማህበራዊ መዋቅር መመርመር መሆኑን ትገልፃለች፡፡

በአጠቃላይ የሊዲያ ስራ በሁለቱም ልቦለዶች ውስጥ የሚገኙ ፎክሎራዊ ጉዳዮችን ለይቶ በማውጣት የማህበረሰቡን ማንነት በምን መልኩ ፈጥረዋል የሚለው ላይ የሚያጠነጥን ነው፡ ፡ ይህን ጥናት ምንም እንኳ ከሊዲያ ጥናት ጋር የሚያመሳስላቸው በሁለቱም ስራዎች ውስጥ የሚገኙ ፎክሎራዊ ጉዳዮችን በየምድባቸው ለይቶ ማውጣት ቢሆንም ዋነኛ ትኩረቱ ፎክሎራዊ ጉዳዮቹ ለሥነ-ፅሁፍ ስራው ያበረከቱትን አስተዋጽኦ መፈተሽ መሆኑና የተጠቀምነውም ትወራ ልዩነታችን ነው፡፡ ሌላው የጥናታችን አካሂድን በተመለከተ ሁለታችንም Dundes ፎክሎርበሥነ-ጽሁፍ ውስጥ ሲጠና የመለየትና የመተርጎም ሁለት ደረጃዎችን ሊከተል ይገባዋል በማለት ያስቀመጠውን መርህ የሚከተል መሆኑ

ተመሳስሏችን ሲሆን እኔ ለጥናት ከመረጥኳቸው ስነ-ፅሁፋዊ ስራዎች ውስጥ አንዱ የጉራጌ ማህበረሰብ ላይ የተሰራ በመሆኑና የሊዲያም ጥናት ሁለቱም በጉራጊኛ ልቦለዶች ላይ የተሰራ በመሆኑ የባህል ተመሳስሎ ይታይበታል፡፡ በተጨማሪም ከሊዲያ ስራዎች ዉስጥ በጫሙት ሸካ እና በዚህ ጥናት ከተመረጡት ደግሞ በእምቢታ ልቦለድ መካከል የታሪክ ተዛምዶ ወይም የቴክስቶች መጠራራት በመኖሩ Intertexuality ንድፈ ሃሳብ ተግባራዊ ይሆናል፡፡ እንደ አጠቃላይ የሊዲያ ስራዎች ሁለቱም በጉራጊኛ ቋንቋ የተፃፉ መሆናቸውና እርሷም የማህበረሰቡ ተወላጅ እንደመሆኗ እያንዳንዱን ትዕምርት ለመተርጎምም ሆነ ባህሉን በቀላሉ ለመረዳት የጠቀማት መሆኑ እንደ ጥሩ ጎን ሊወሰድ የሚገባው ጉዳይ ሆኖ አግኝቼዋለሁ፡፡

# ምዕራፍ ሦስት

## 3.1 የጥናቱ ዘዴና ንድፍ

ይህ ጥናት የተጠቀመው የምርምር አይነት አይነታዊ ዘዴን ሲሆን ጥናቱ የተከተለው አካሄድ ደግሞ ልየታ (Identification) ፤መፈከር (Interpretation) ዘዴዎችን ነው፡፡ Dundes(1990፣32)፡፡ እንደሚሉት አንድ አጥኚ ፎክሎሮችን ከስነ-ፅሁፍ ስራዎች ውስጥ ለማጥናት መከተል ያለበት ዘዴ በቅድሚያ መለየት፤ቀጥሎ መፈከር የሚለውን መርህ የተከተለ ነው፡፡ በቅድሚያ ለጥናቱ በተመረጡት ሁለት ስራዎች ውስጥ ከልቦለዶቹ ጅማሬ እስከ ፍፃሜ ድረስ የተነሱ ፎክሎራዊ ጉዳዮችን የመለየት ስራ የተሰራ ሲሆን በመቀጠልም ትዕምርታዊ ፍቺ ያላቸውን የልቦለዶቹን አውድ መሰረት በማድረግ የመፈከር ስራ ተሰርቷል፡፡ ተያይዞም ፎክሎራዊ ጉዳዮቹ ለስነ-ፅሁፍ ስራው (ለልቦለዶቹ መሳካት) ያበረከቱት ፋይዳን በተመለከተ ትንታኔ ተሰጥቶባቸዋል፡፡

## 3.2 የመረጃ ምንጮች

ጥናቱ የተሳካ ይሆን ዘንድ ቀዳማይ እና ካልዓይ የመረጃ ምንጮች ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡ ቀዳማይ የመረጃ ምንጭ ሆነው ያገለገሉት በ(2005) አዲስ አበባ፤ኤች ዋይ ኢንተርናሽናል ፕሪንቲንግ የታተመዉ የአንዷለም አባተ (የአጸደ ልጅ) መኤ፤ት የተሰኘዉ ልቦለድ አንዱ ሲሆን ሁለተኛዉ በ(2006) አዲስ አበባ፤ አታፍዘር አሳታሚዎች ድርጅት የታተመዉ የእንዳለ ጌታ ከበደ እምቢታ የተሰኘ ታሪካዊ ልቦለድ ነዉ፡፡ ካልዓይ የመረጃ ምንጭ ሆነው ያገለገሉት ደግሞ የጥናቱ ቀጥተኛ ተተኳሪ ያልሆኑ ነገር ግን ለጥናቱ መሳካት የመረጃ ድጋፍ የሰጡኝ የስነ-ፅሁፍና የፎክሎር ንድፈ ሃሳቦች ናቸው ፡፡

## 3.3 የንሞና አመራረጥ ዘዴ

ጥናቱ አላማ ተኮር የንሞና አመራረጥ ዘዴን የተከተለ ሲሆን ለጥናት በተመረጡት ሁለት ስራዎች ዉስጥ የሚገኙ ፎክሎራዊ ጉዳዮች ብቻ እየተመዘዙ ለትንተና ቀርበዉበታል፡፡ ተጨማሪም በጥናቱ የተለያዩ መስፈርቶችን ከግምት ውስጥ ለማስገባት ተሞክሯል፡፡ ከነዚህ መካከልም ከዘመን፣ ከስነ-ፅሁፍ ስራዎች ምርጫ እና ከፀሃፊያን አንፃር የሚነሱ ጉዳዮች ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

ከዘመን አንፃር፡- ፎክሎር በአንድ ዘመን/ ወቅት የነበረን ማህበረሰብ ባህላዊ፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ሌሎች መሰል ጉዳዮች ወደ ኋላ መለስ ብለን የምናጠናበት የእውቀት አካል መሆኑን (Benamos፣ 1995፣ Dorson፣ 1963) ይገልፃሉ፡፡ በተቀራራቢ ዘመናት የተጻፉ የስነ-ፅሁፍ ስራዎችን ሰብስቦ ከፎክሎር አንፃር የተነሱ ጉዳዮችን ማጥናት ከዚህ አኳያ የሚኖረው ፋይዳ ከፍተኛ ይሆናል፡፡ (ቴዎድሮስ፤ 2001፣130) ዮናስ አድማሱን ገልፆ የአማርኛ የስነ-ፅሁፍ ጥናት ትኩረት የአማርኛ ሥነ -ፅሁፍ ታሪክ (Litrary history) እመፃፍ ላይ ማሳረፍ እንዳለበት እያሳሰቡ ይህን "ታላቅና ፈታኝ" ተግባር ለማከናወን እንዲቻል በቅድሚያ የስነ-ፅሁፍ ባለሙያዎችን በተቀራራቢ ዘመን የተከየኑ የስነ-ፅሁፍ ስራዎችን ወስደው በኪናዊ መስፈርቶች እየመዘኑ ስራዎቹን ሊያስተሳስር የሚችል ፈር መንደፍና መቀመርን ሁነኛ ተግባራቸው እንዲያደርጉ ይመክራሉ ይለናል፡፡ ከዚህ በመነሳትም ለጥናቱ የተመረጡት ሁለቱም ስራዎች የተቀራራቢ ዘመን ማለትም (የ2005) እና (2006) መሆናቸው በቅርብ ዘመን እየተፃፉ ያሉ የሥነ-ፅሁፍ ስራዎች ፎክሎራዊ ጉዳዮችን ከስነ-ፅሁፍ ስራዎቻቸው ጋር እያዋደዱ መፃፍ መጀመራቸው በር ከፋች መሆኑን ማመልከታቸው አንዱ አስተሳሳሪ ገመድ ሲሆን ከስነ-ፅሁፍ ስራዎች ምርጫ አንፃር ደግሞ ሁለቱም ኢትኖግራፊክ የሚባለውን የአፃፃፍ ስልት የተከተሉና በስራዎቻቸው ውስጥ ፎክሎራዊ ጉዳዮች በስፋት የተነሱባቸው፤ልቦለዶቹ የተፃፉበትን ማህበረሰቦች ወግ፣ልማድ ፣ ማንነት ፣ አጠቃላይ ባህላዊ አመለካከትና ክንውናቸውን ስፍራው ድረስ በመሄድ የባህሉን ባለቤቶች መስለውና እንደ ማህበረሰቡ ኖረው የፃፏቸው ስራዎች መሆን ሁለቱን ስራዎች አስተሳሳሪ ሌላኛው ገመድ ይሆናል ፡፡ከፀሃፊያን አንፃር መረጣው ሁለቱም ፀሃፊያን የስነጽሁፍ እና የፎክሎር ሳይንስ ትምህርቶችን በዩኒቨርሲቲ ደረጃ ያጠኑና የዘርፉም ባለሙያ ከመሆናቸው አኳያ ስራዎቻቸው ለዚህ ጥናት ቢመረጡ የጥናቱን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ይረዳል በሚል የጋራ ምክንያት ተጠኚዎቹ ስራዎች ለወል ጥናትነት ለመመረጥ ችለዋል፡፡

## 3.4 የመረጃ አሰባሰብ ዘዴዎች

በዚህ ጥናት መረጃዎች የተሰበሰቡት በሰነድ ፍተሻ ሲሆን Goldstien የሰነድ ዳሰሳ ሊሰራ ከታሰበበት ግዜ ጀምሮ እስከ ጥናቱ ፍጻሜ ድረስ ባሉት ተግባራት ሁሉ የሚከወን የጥናትና ምርምር ሂደትና ተግባር መሆኑን ይገልጻሉ Goldestein (1964፣110)። በመሆኑም በዚህ ጥናት የሰነድ ዳሰሳ ተግባራዊ የተደረገበት ሂደትም ይህን የተከተለ ሲሆን በቅድሚያ

የፎክሎርንና የስነ-ፅሁፍን የጋራ ባህሪያት የሚያመላክቱና አንዱ ከሌላኛው ጋር የሚኖረውን ትስስር የሚያሳዩ የተለያዩ ንባቦችን በማድረግ ፤ በመቀጠልም ሁለቱንም ልቦለዳዊ ስራዎች በሚገባ ደጋግሞ በማንበብና ፍተሻ በማድረግ መረጃዎች ሊሰበሰቡ ችለዋል፡፡

# ምዕራፍ አራት

በዚህ ምዕራፍ የጥናቱ ትንታኔ የሚቀርብበት ሲሆን ለጥናትበተመረጡት መኤኒትና እምቢታ ታሪካዊ ልቦለዶች ውስጥ የሚገኙ አጠቃላይ ፎክሎራዊ ጉዳዮችን በየምድባቸው ለቅሞ የማውጣትና የመለየት ስራ የተሰራ ሲሆን ፎክሎራዊ ጉዳዮች ሆነዉ ትዕምርታዊነት ያላቸዉ ደግሞ የቀረቡበትን አውድመሰረት በማድረግ ተተርጉመዉ ቀርበዋል፡፡ተያይዞም ፎክሎራዊ ጉዳዮቹ ለሥነ-ፅሁፍ ስራው ያበረከቱትን ፋይዳ በተመለከተ ትንታኔ ተሰጥቶባቸዋል፡፡ በቅድሚያ ትንታኔውን ለመረዳት ያስችል ዘንድ የሁለቱንም ስራዎች አፅህሮተ ታሪክ አጠር ተደርጎ ቀርቧል፡፡

## 4.1 የእምቢታ እና የመኤኒት ልቦለዶች አጽህሮተ ታሪክ

### 4.1.1 የእምቢታ ታሪካዊ ልቦለድ አጽህሮተ ታሪክ

ልቦለዱ የዛሬ አንድ መቶ ሃምሳ ሁለት ዓመት አካባቢ (በ1850ዎቹ) ማለትም በአፄ ቴዎድሮስ የንግስና ዘመን በጉራጌ ብሄረሰብ መካከል የሴቶች በደል ቀርቁሯት የተነሳች እንስት ታሪክን የሚተርክ ሲሆን ይህችም እንስት "የቃቄ ውርድወት" ትባላለች፡፡ የቃቄ ውርድወት በቀድሞው የጉራጌ ማህበረሰብ የስም አጠራር ከታዋቂ (የሚከበር) አባት የተወለደ ልጅ የአባቱ ስም ቀድሞ የልጁን አስከትሎ የመጥራት ባህል መሰረት የምትጠራ እጅግ ሃብታም ከሆኑ በጉራጌ፣ በምሐርና አክሊል ወረዳ፣ ቆረር ቀበሌ፣ዞርመኘ ተብሎ በሚጠራው መንደር በምሐር ቤተ-ጉራጌ አንቱ ከተባሉ ባላባትና የኦርቶዶክስ እምነት ተከታይ ከሆኑት ዳሞ ቃቄ ወራቦ እና በጥብቅ የእስልምና እምነት ተከታይነታቸው ከሚታወቁት የወለኔ ቤተ-ጉራጌ ተወላጅ ከሆኑት አጅየት አሚና ትወለዳለች፡፡

ወርድወትን የሚያውቁ ሁሉ "ተወዳዳሪ የማይገኝላት የውበት ዳርቻ እሷ ብቅ ስትል አካባቢው የሚደምቅ የቆንጆዎች ቁንጮ ከሁሉም በላይ ጀግንነትን በጣም የምትወድ፤ዝናን በእጅጉ የምትናፍቅ ናት" ይላሉ፡፡ ይህቺ ውብ ልጃገረድ ለታዋቂው የእዣ ጀግና ለአጋዝ (አበጋዝ) ፋርችዬ ላምቢዬ ትዳራለች፡፡ ምንም እንኳ ወርድወት ያገባችው ወንድ ማንም የምትመኘው አይነት ጀግና ቢሆንምበትዳሯ ደስተኛ ሳትሆን ትቀራለች፡፡ ለዚህም ምክንያቷ በባህላቸው መሰረት ለሴት ልጅ የሚሰጠው ክብርና ቦታ ከወንዶች አንፃር አናሳ ሆኖ ሲፈፀም በማየቷ ነበር፡፡ወርድወት ግን እንደሌሎች ሴቶች ይህን በደል እያየች ዝም

ሳትል ትቀራለች፡፡ የአካባቢውን ሴቶች በማሰባሰብ  በማህበረሰቡ ዘንድ ሴት ልጅ እንደ ወንድ በጀፎረ (ባህላዊ የእርቅና የዳኝነት ስርዓቶችና ሸምግልናዎች የሚካሄዱበት ስፍራ) ልትወያይ ይቅርና በስብሰባው ላይ መቆሟ እንኳን የተወገዘ በሆነበት  በተደጋጋሚ ጥያቄዎቻቸው እንዲሰሙ ታደርጋለች፡፡

እነቃቄ ወርድወት ያነሷቸው ዋና ዋና የመብት ጥያቄዎች አንድ አባ ወራ አንድ ሚስት ትብቃው ፤በሴቶች ላይ የተጣለው እርግማን (እንቂት) ይነሳልን ፤ሴት ልጅ እንደ ወንድ ልጅ የአባቷን መሬት ትውረስ ፤ ሴት ልጅ እንደ ወንድ ሁሉ የመረጠችውን ታግባ፤ ሴት ልጅ ልክ እንደ ወንዶች ሁሉ በአደባባይ በሚደረጉ ስብሰባዎች ላይ ተገናኝተን የማህበረሰቡ ጉዳይ ላይ አስተያየት የመስጠት መብት ይኑረን ወዘተ የሚሉ ነበሩ ፡፡

የነ ወርድወት ጥያቄ ደረጃ በደረጃ እየተሻገረ የእጀካ ሸንጎ የሚሰኝ ምክርና ውሳኔ ሰጪ ባህላዊ ምክር ቤት ይደርሳል፡፡ ወርድወት በጉራጌዎች ዘንድ ባህሉን እንደጣሰ አፈንጋጭ ሴት ትታያለች፡፡ ጥያቄዋ ያስደነገጣቸውና በበሳል አባቶች የሚመራው መላና ፍትህ በእጁ ነው የሚባልለት ታላቁ የእጀካ ሸንጎ ይኼ ፈተና ሲገጥመው ከፍተኛ አድናቆትም፣ የአደጋ ስጋትም ስላደረበት ትልቅ ጥንቃቄና ምክር ያደርጋል፡፡ በኋላም ምሁር ወዳሉት ወደ አባቷ ወደ ዳሞ ቃቄ የአገር ሽማግሌዎችና የሃይማኖት አባቶች የአደራ ትልቅ መልእክት ይልካል ነገር ግን ውርድወት ከዚህ አመፅ እንድትወጣ ይመክሩና ይማፀኑ ዘንድ የተደረገው ጥረት በወርድወት እንቢታ ይከሽፋል፡፡ በመጨረሻም ወርድወት የሰበሰበቻቸውን ሴቶች በባሎቻቸው በኩል አስፈራርተውና አባብለው በጥያቄዎቻቸው እንዳይገፉበትና ከወርድወት ጋር እንዳይተባበሩ ካደረጉ በኋላ አጋዝ ፋርችየን ሸንጎው በዝግ ስብሰባ ጠርቶ "ይሄን የጉራጌ ሴቶች አመፅ ለማስቆም እንችል ዘንድ ለወርድወት እንቂት ማንሳት ግድ ሆኖ አግኝተነዋልና እባክህ የኛን የሽማግሌዎችን ቃል ሰምተህ እንቂቱን አንሳላትና እንመርቅህ" ይሉትና ተነስተው ይቆማሉ፡፡ ጀግናው የጀግናው የዳርሳሞ ልጅ አጋዥ አባቱ ለሸዋ ንጉስ አልገብርም ብለው በተደጋጋሚ ከሚኒልክ ጦር ጋር ፍልሚያ በማድረግ ሰራዊቱን የደመሰሱና ከንጉሱም ጦርነት ይብቃን እርቅን እናውርድ ተብለው የተለመኑ በኋላም አንኮበር ሄደው ጃንሆይ ፊት ቀርበው በፊት ከነበራቸው ስልጣን የበለጠ ስልጣን ተሰጥቷቸው የዳኝነት ዙፋን እንደወረሱ የሚተረክላቸው የዴርሳሞ ልጅ አጋዥ እጅግ ይጨነቃል፡፡ በአንድ በኩል ወርድወትን ማጣቱና በሴት መደፈሩ ክብሩን የሚነኩበት መሆኑ እያንገበገበው በሌላ በኩል ደግሞ ድፍን ሃገሩ የሚንቀጠቀጥላቸው የሃገር

ሽማግሌዎችን ቃል መግፋቱ እንደሚያስረግመው ያውቃል፡፡ በመጨረሻም ጀግናው ፈርች የለአገር ሽማግሌዎች ይሸነፋል፡፡ "እሺ አባቶቼ፣ ከቃላችሁ አልወጣም" ይላል፡፡ምርቃትም ይጎርፍለታል፡፡

ሽማግሌዎቹም ወርድወትን "ወስነናል እንቂት አይኑርብሽ፡፡ የፈቀድሽውን አግቢ! በፈቀድሽ ጊዜ ፍቺ! መርቀናል፡፡ ነገር ግን በሌላ ሴቶች ኑሮ አትግቢ፡፡" በማለት ቃል ያስገቧታል፡፡ ምንም እንኳ ወርድወት ነፃነቷን ያገኘችና እንዳሻት ማግባትና መፍታት የምትችል ሆኖ የተፈቀደላት ቢሆንም ስትመራው የነበረውና ተቀጣጥሎ ጫፍ የደረሰው የተበደለ ፍትህ ጠያቂ ሴቶች ትግል በወንዶች ሴራና በሴቶቹም መፍረክረክ ምክንያት እንዲህ መሆኑወርድወትን በጣም ያሳዝናታል ፡፡

በሴቶች ላይ የሚፈፀምን በደልለማስቀረት ባስተባበረችው ያታዊ ትግል ያለመችው ግብ ያልመታላት ወርድወት ስሜትዋ ደብዝዞባት ወደአባትዋ ዳሞ ቃቄ ቤት ትመለሳለች፡፡ ቤተሰቦቿም እሷን ደስ ለማሰኘትብዙ ይጥራሉ፡፡ብቸኝነትና ትካዜ ታበዛለች፡፡ ብዙ ሰዎች ለትዳር ጥያቄ ሽማግሌ ቢልኩም የትዳርን ዓለም አይንህን ላፈር ብላ ትቆያለች፡፡ በመጨረሻም የተጣለባትን ባህላዊ ገደብ አሽቀንጥራ በመጣል ከማህበረሰቡ ህግ ትሸፍታለች፡፡ ዝናዋ በመላው የጉራጌ ምድር ያስተጋባል፡፡ በኋላም የመረጠችውን የቸሃውን ጀግና የአሴህ አርብ ፉጋ (የጌረሞ ፉጋ)ን አግብታ መኖር ትጀምራለች ፡፡

### 4.1.2 የመኤኒት ልቦለድ አጽህሮተ ታሪክ

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሁለተኛ ዲግሪ ተማሪ የሆነው አለምሰገድ እጅግ ከሚያፈቅራት ጓደኛው ፍራኦል ጋርየመመረቂያ ጽሁፉን ለመስራት ከአዲስ አበባ ወደ ደቡብ ምእራብ ኢትዮጵያ የመኤኒት ብሄረሰብ ዘንድ ይጓዛሉ፡፡

በመጀመሪያ ሚዛን ተፈሪ ከዚያም ወደ መኤኒት ሻሻ በኋላም ወደ ጎልዲያ እጅግ አሰልቺና አድካሚ ጉዞ አድርገው ጨበራ ይደርሳሉ፡፡ ፍራኦል በየመንገዱና ሃገሩ የሚቀርብላት ምግብና የምትተኛበት መኝታና ክፍል ከአድካሚው የእግር ጉዞ ጋርተዳምሮ ከምታውቀው እና ከኖረችበት ህይወት ጋርአልጣጣም ብሎ ቢያስቸግራትም አለምሰገድ ከጎኗ በመሆኑ ትቋቋመዋለች፡፡

አለምሰገድ ባህል መከበር አለበት ብሎ የሚያምን አይነት ሰውሲሆን በትውልድ ውስጥ አርአያ መሆንን ሲናፍቅ አድጓል፡፡በልጅነቱም በትህትናው የታወቀ የመንደሩ ሰው ሁሉ የመረቀው ብልህና አስተዋይ መሆኑን የሚያውቁት ሁሉ ይመሰክሩለታል፡፡ ፍራኦል በተደጋጋሚ ከጋብቻቸው በፊት ወሲብ መፈፀም ፈልጋ ብትወተውተውም ማድረግ እንደሌለባቸው አጥብቆ ይከለክላታል፡፡ ጨበራ ከመጡ ከብዙ ጊዜ  በኋላ አንድ ቀን በስህተት በፈጸሙት ግንኙነት ራሱን እንደ ሃጢያተኛ በመቁጠር ፈጣሪውን ምህረት ይጠይቃል፡፡ ፍራኦልን “ምንህ ናት?” ተብሎ ሲጠየቅ ፍቅረኛዬ ካልኩ በባህላቸው መሰረት ላይወደድና ከባህሉ ጋርሊጣረስ ይችላል ብሎ “ታናሽ እህቴ ናት” ብሎ መልስ ይሰጣል ፡፡

መኤኒቶች በእያንዳንዱ ድርጊታቸውውስጥ የራሳቸውን እሴት፤ባህል፤ልማድ፤እምነት፤ እውቀትናፍልስፍና የሚያንጸባርቁበት ሁኔታ እጅግ ያስገረመው አለምሰገድ ፍራኦልን ቸል ብሎትኩረቱን ጥናቱ ላይ ያደርጋል፡፡ፍራኦል ከአለምሰገድ ተነጥላ ወደጓሮ ለሽንት በወጣችበት ሰዓት አንድ ወጣት አስገድዶ ይደፍራታል፡፡ የፍራኦል መደፈር ሁሉንም ያስቆጣል፡፡ በተለይ  እንደልጆቻቸው የተቀበሏቸውን አቶ ኬላጊንና ወገኖቻቸውን እጅግ ያሳዝናል፡ፍራኦል ከሁለት ቀን በኋላ ቅስሟ ተሰብሮና ተስፋ ቆርጣ በሰመመን ትነቃለች፡፡ አለምሰገድም እሱን ብላ መጥታ ለዚህ ስቃይ በመዳረጓ በፀፀት ስሜት ይንገበገባል፡፡ በኋላም በመኤኒት ባህል መሰረት ሽማግሌ ተልኮ የደፈራት ጎረምሳ አንዲት ቁብ በግ ይዞ በመምጣት በሽማግሌዎቹ ፊት ይቀርባል፡፡ በጓም በባህሉ መሰረት ትታረዳለች፡፡ የበጉም አንጀት በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ ወጥቶ በእድሜ የገፉና በማህበረሰቡ ተደማጭነት ያላቸው ሰዎች ማንበብ ይጀምራሉ፡፡ውጤቱም ይገለፃል፡፡  በመጨረሻም የደፈራት ወንድ ከጉልበቷ ጀምሮ ወደታች በደም ያጥባትና እርቁ ይፈፀማል፡፡

ይህ ወጣት ግን ፍራኦልን ጠልፎ የግሉ ለማድረግ የነበረው ፅኑ ፍላጎት ነበረዉና በሌላ ጊዜ ጓደኞቹን አሰባስቦ ጦር በመያዝ ለጠለፋ ይከተላቸዋል፡፡ በዚህ ጊዜ ፍራኦል ቀድማ ታየውና ትጮሃለች፡፡ አለምሰገድና የአዛውንቱ ኬላጊ ልጅ ድብድብ ይጀምራሉ፡፡ በኋላም ከተባባሪዎቹ መሃል አንዱ ወጣት ይሞታል፡፡ግጭቱ ይባባሳል የተገዳይ ወገኞች ለበቀል ይነሳሳሉ፡፡ የገዳይ ጎሳዎች በፍጥነት ሽማግሌዎችንይልካሉ፡፡ በመኤኒት ባህል መሰረት እርቅ ለማውረድ የይቅርታ መጠየቂያና የመቅበሪያ ከብት ይሰጣል፡፡ ከባዱ ጉዳይ ደግሞ የገዳይእህት በአሻነት መከፈል አለባት፡፡ ፍራኦልና አለምሰገድ እህትና ወንድም ነን በማለታቸው ማህበረሰቡም የሚያውቀው ይሄን በመሆኑ አሁን ተነስተው ፍቅረኛሞች ነን

ቢሉ ቢያለቅሱ ቢለምኑ የሚያምናቸው ይጠፋል፡፡ ፍራኦል በአሻነት(ለሚች ወንድም መተኪያ) መከፈል እንዳለባት ይወሰናል፡፡ በአሻነትም ትከፈላለች፡፡ ፍራኦልን በአሻ የወረሰው ወጣትም ወደ ማይገኝበት ስፍራ ይዟት ይሸሻል፡፡

አለምሰገድም ከአዛውንቱ ኬላገ ልጅ ጋር በመሆን ጉዳዩን ለህግ ለማሳወቅ ተመልሶ ወደ ጎልድያ ይሄዳል፡፡ የፍራኦል ታላቅ እህት ቁጡዋና ገንዘብ ወዳጇ ሃዊም እህቷን ለመፈለግ መጥታ ነበርና አለምሰገድ ጋር ይገናኛሉ፡፡ በኋላም የፖሊስ አካል ይዘው ወደ አዛውንቱ ሰፈር ያቀናሉ፡፡ ፍራኦልን አየሁ የሚል ይጠፋል፡፡ ተስፋ ይቆርጣሉ፡፡ ሃዊ ወደ አዲስ አበባ ተመልሳ አለምሰገድን ትከሰዋለች፡፡ አለምሰገድም ይታሰራል፡፡ ከአንድ ሳምንት በኋላ በዋስ ይለቀቃል፡፡ ይሁን እንጂ እንደቀድሞው አልሆን ይላል አይበላ፣ሰውነቱን አይታጠብ፣ ከሰው አያወራ የሚያስበው ራሱን ስለማጥፋት ብቻ ይሆናል ጓደኞቹ ይጨነቃሉ፡፣ በኋላም ፖሊስ ክትትሉን አላቋመም ነበርና ከመኤኒቶች መንደር ስልክ ተደውሎ ፍራኦል እንደተገኘች ይነገረዋል፡፡

ፍራኦል ሳታስበው ከትምህርቷም፣ ከቤተሰቦቿም ርቃ በመኤኒት ሰማይ ስር ብዙ መከራ ይደርስባታል፡፡ትደፈራለች፣ ትጠለፋለች፣ በአሻ ተከፍላም ሁለተኛ ሚስት የመሆን መጥፎና አስደንጋጭ አጋጣሚዎችንም ታያለች፡፡ በኋላም ወደ ትውልድ ቀዬዋ ወደ አዲስ አበባ ትመለሳለች፡፡ ይሁንና አለምሰገድን ተይው በሚሉና በሆዷ በያዘችው ፅንስ ይውጣ አይውጣ ንትርክ ከቤተሰቦቿ ጋር ተስማምታ መኖር ሳትችል ትቀራለች፡፡ በመጨረሻም ጓዟን ጠቅልላ አለምሰገድ ጋር በትዳር በአንድ ቤት መኖር ትጀምራለች፡፡ ወንድ ልጅም ይወልዳሉ፡፡ የልጃቸውንም ስም "መኤኒት" ይሉታል ትርጓሜውም "ሰው" ማለት ነው፡፡

## 4.2 የፎክሎራዊ ጉዳዮች ፋይዳ ትንተና *በመኤኒትና እምቢታ ታሪካዊ ልቦለዶች*

በፎክሎር ዘርፎች እና በየዘርፎቹም ውስጥ የሚገኙት አያሌ ዘውጎች ለአንድ መሰረታዊ ፋይዳ እስካልሰሩ ድረስ ቀጣይነት ላይኖራቸው ይችላል፡፡ ከዚህ አንፃር በሁለቱም ስራዎች ውስጥ የተነሱትን ፎክሎራዊ ጉዳዮች መነሻ በማድረግ ደራሲያን እነዚህን ፎክሎራዊ ጉዳዮች መጠቀማቸው ለስራው ያስገኘላቸውን የተለያዩ ፋይዳዎች መመርመር አስፈላጊ ይሆናል፡፡

ለጥናት በተመረጡት ሁለት ስራዎች ውስጥ በርካታ ፎክሎራዊ ጉዳዮች የተዳሰሱ ሲሆን በዋናነት ሃገረሰባዊ ልማዶች፣ስነቃሎችና ቁሳዊ ባህሎች ተነስተዋል፡፡ በመሆኑም በቅድሚያ

በልቦለዶቹ ውስጥ የሚገኙትን ፎክሎራዊ ጉዳዮች የመለየት ከልየታውውስጥ ትዕምርታዊነት ያላቸውን ከልቦለዶቹ አውድ ተነስቶ መፈከር በመጨረሻም ፎክሎራዊ ጉዳዮቹ ለልቦለዶቹ ያበረከቱትን ፋይዳ ለመተንተን ተሞክሯል፡፡

### 4.2.1 ሥነ-ቃል

ከሥነ-ቃል ምድቦች መካከል ምርቃት ፣ እርግማን ፣ መሃላ፣ ምሳሌያዊና ፈሊጣዊ አነጋገሮች በሁለቱም ስራዎች ውስጥ የሚገኙ ሲሆን *በእምቢታ* ታሪካዊ ልቦለድ ውስጥ የውዳሴ ቃል ግጥሞች *በመኤኒት* ልቦለድ ውስጥ ደግሞ ፉከራዎች ይገኙበታል፡፡

#### 4.2.1.1 እርግማንና መሃላ

የስነቃል ዘርፍ የሆነው እርግማን *በመኤኒት* ልቦለድ ውስጥ የሚገኝ ሲሆን በመኤኒቶች ዘንድ ሁለት የተካካዱ ሰዎችን ለመዳኘት የሚሄዱት የጎሳ መሪ ወይም ቃልቻ ጋር መሆኑንና ቃልቻዎቹ ፀበኞቹ ፊት በመቅረብና በማስማል በዳይ እንዲክስ ተበዳይ እንዲካስ የሚያደርጉበት ሁኔታ እንዳለ በዚህ መልኩ መተማመን ላይ ካልደረሱ በመረጋገም እንዲዘጋ መደረጉ በልቦለዱ ውስጥ የተጠቀሰ ሲሆን እነዚህ ከፎክሎር ዘርፎች መካከል የስነ-ቃል ምድብ የሆኑትን እርግማንና መሃላ በልቦለዱ ታሪክ ውስጥ የተፈጠረን ግጭት ከማክረር ረገድ ከፍተኛ ሚናን ሲጫወቱ እንመለከታለን፡፡ ቀጣዩን ከልቦለዱ የተቀነጨበ ፅሁፍ ለአብነት ያህል መመልከት ይቻላል፡፡

> ገንዘብ አበድሬው ከዳኝ ስላለ ነው እዚህ ድረስ ያስጠራንህ፤ስትበዳደሩ ደግሞ ያየ ሰው የለም፡፡ ሆኖም ወስደህበት ከሆነ ባይሆን ወደፊት ሰርተህ ትከፍላለህ ወይም ተበድረህ ትሰጠዋለህ፡፡ "ቃልቻው ሲናገሩ ምንም ለውጥ አይታይባቸውም፡፡ አንዴ የሆነውን ተናግሬያለሁ፡፡ ሰውየው ምንም ገንዘብ ሳይሰጠኝ ነው የሚከሰኝ ከካደ የእርስዎን እጅ ይምታና ይማልልኝ፤እኔም የእርስዎን ደጅ ጠርጌ እሄዳለሁ፡፡"እንግዲህ እንዲረግምህ ልንፈቅድለት ነው" አሉና ተከሳሹን ትኩር ብለው አዩትተከሳሹ የቃልቻው አይኖች በጥልቀት እየመረመሩት እንደሆነ አውቋል፡፡ ምራቁን በትልቁ ዋጥ አድርጎ ቀና አለና ከቃልቻውጋርተያዩ፡፡ መተያየቱ ሳይረግብ…ያላደረኩት ነገር በእኔም ሆነ በዘሬ ላይ አይደርስምና ይርገም፡፡እርግማኑ ግንበራሱና በዘሩ ላይ መከራውን እንደሚያፈላበት አውቃለሁ" አለ፡፡ ቃልቻው ወደ ግራ ዘወር ሲሉ ረዳታቸው ፈጠን ብሎ የተቆረጠና ጭብጥ የሚሞላ ግራዋና ካስካሳ (ናጫ) ይዞ ተመለሰ፡፡በዚያው ሰዓት ሌላ ረዳት የሚመስል ልጅ እግር ወጣት ደግሞ በቋንቋቸው"ሾርቃ" የሚባለውን ተለቅ ያለ ግማሽ ቅልየተሞላውሃ ይዞ ከከሳሽና ተከሳሽ ፊት አስቀመጡት፡፡ዓለምሰገድ የሁለቱ ነገሮች ፍቺ ስላልገባው አስተርጓሚውን በሹክሹክታ ማናገር ጀመረ፡፡

> "ምንድነው የመጣው?" ቅጠሎቹን እያሳየ ጠየቀ፡፡ የመጡት ሁለቱ ካስካሳና ግራዋ የተሰኙ ቅጠሎች ግቢ ለመተረጊያነት ነው፡፡ የተመረጡትም ሁለቱም እቃ ሲያጥቡ የሚያጠሩ በመሆናቸው ነው፡፡ በሾርቃ ያለውውሃ ነው፡፡ ሁለቱም ለእርግማን ስርዓት ማካሄጃ የሚውሉ ናቸው፡፡ ከሳሽ የቀረበለትን የሾርቃ ውሃ በሁለት እጆቹ ከፍ አድርጎ እንደያዘ በአካባቢው ያሉትን ሰዎች ተመለከተ እንደገና አይኖቹን ውሃው ላይ አድርጎ "እኔ እውነት ተናግሬ ይሄ ሰውዬ ስለካደ እዚህ ሾርቃ እንዳለውውሃ ሕይወቱ ይደፋ"ብሎ ውሃውን ወዲያና ወዲህ ነቅንቆ ወደ ውጭ አውጥቶ አርቆ ደፋው፡፡ ተከሳሽ በፍጥነት ተቆርጦ የመጣውን ግራዋ በቀኝ እጁ አፈፍ አድርጎ ትዕዛዝ መጠባበቅ ጀመረ፡፡ የተሰጠውን ቦታ ለመጥረግም ወጣ፡፡ "እውነት ተናግሬ ከሆነ የርሱ ዘር እንዲህ ይጠረግ፤እኔ ውሸት ተናግሬ እንደሆነ የኔ ዘር እንዲህ ይጠረግ ብሎ ጮህ ብሎ ተናግሮ የተጠቆመውን ቦታ በግራዋና ናጫው መጥረግ ቀጠለ...(መኤኒት2005፤129-130)፡፡

ከላይ ከቀረበው ሃሳብ እንደምንረዳው *በመኤኒት* ማህበረሰብ ዘንድ ሁለት የተካካዱ ሰዎች ለመዳኘት የሚሄዱት የጎሳ መሪ ወይም ቃልቻ ጋር መሆኑን ነው፡፡ በቃልቻዉ ፊት ቀርበዉ መተማመን ላይ ካልደረሱ በመረጋገም እንዲዘጋ ይደረጋሉ፡፡ ተራጋሚዉ ሰዉ እዉነትም የተካደ ከሆነ በተረጋሚዉ እስከ ሰባት የሚደርሱ ቤተዘመድ ላይ እርግማኑ ይደርሳል ተብሎ ስለሚታመን ግጭቱ እየተባባሰ (እየጠዘ) በሁለቱ መካከል ያለው የሻከረ ጉዳይ ይበልጥ እየጠነከረ እንዲሄድ ያደርገዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የእርግማኑን ስርዓት አስፈፃሚው ቃልቻም ግጭቱ እንዲባባስ የራሳቸው ሚና ሲኖራቸው ለማስፈፀሚያ የሚውሉት የተለያዩ ቅጠሎች ደግሞ ለማህበረሰቡ አንዳች ትዕምርታዊ ፋይዳ ያላቸው ሲሆን ቅጠሎቹ ከሌላው ተለይተው የተመረጡት ምክንያት ሁለቱም እቃ ሲያጥቡ የሚያጠሩና በማህበረሰቡ ዘንድ ከፍተኛ ግልጋሎትን የሚሰጡ በመሆናቸው ሲሆን ግጭቱን ለማክረርም አስተዋጥኦ አድርገዋል፡፡ በአጠቃላይ ከላይ እንደምንረዳው ከፎክሎር ዘርፎች ውስጥ የስነቃል ምድብ የሆኑ እርግማን እና መሃላ የልቦለዱን ግጭት በማክረር ረገድ ከፍተኛ ሚና ተጫውተዋል፡፡

በተመሳሳይ *እምቢታ* በተሰኘ ታሪካዊ ልቦለድ ውስጥ ከተነሱት አንኳር ጉዳዮችአንዱ አንቂት ሲሆን፤አንቂት ማለት ጥሬ ትርጉሙ የሴት ልጅ እርግማን ማለትመሆኑ፡፡አንቂት የጉራጌ ማህበረሰብ የቆየ ፍልስፍናና እምነት የሚንጸባረቅበት ጥልቅ ሃሳብ የያዘ ጉዳይ መሆኑንና ወንዶች ሴቶችን ፊትቼሻለሁ እስካላሉ ድረስ ሌላ ባል እንዳያገቡ የሚከለክልና የሚያስር ህግም እንደሆነ የቃቄ ወርድወትና አጋሮቿ በተደጋጋሚ የእጅካን ሸንጎ ከሚሞግቱባቸው ዋናና መሰረታዊ ጥያቄዎች ውስጥ አንዱ ይሄው የአንቂት ይነሳልን ጥያቄም እንደሆነ ጭምር በታሪካዊ ልቦለዱ በርካታ ቦታዎች ላይ ተገልጿል፡፡ ይህ

የአንቂት ህግ (በሴቶች ላይ የተጣለ እርግማን) የልቦለዱን ግጭት ከማክረር አኳያ አንዳች ፋይዳ ሲኖረው ይታያል፡፡ ቀጣዩን ከታሪካዊ ልቦለዱ የተቀነጨበ አስረጂ እንመልከት፡፡

> "አንቂት የተፈራ ቃል ነው ቃሉ ብዙ ሚስጥር አዝሏል፡፡ አይጠየቅም አይሻሻልም አንቂትን የተዳፈሩ የደረሰባቸውን አይተናል፡፡ይህንን የጋብቻ ውል ሃገሬው እንዲተዳደርበት ያመጡ ሽማግሌዎች ውሉን ተግባራዊ በማያደርጉ ተወላጆች ላይ የእርግማን ዶፍ አዝንበዋል፡፡ እርግማኑ ደግሞ ይታመናል ያየኳቸው ሴቶች አሉ እከሌ ቤት አነእከሌ ጎሳዎች ቤት እንዳትገቡ ተብሎ ሴቶቹ ግን ባሎቻቸውን ለማናደድ አትጋቡ ከተባሉት ቤቶች ጋር ተጋብተው ህሊናቸውን የሳቱ ፤በወንዝ የተወሰዱ ፤መሃን የሆኑና በመብረቅ የተመቱ…(እምቢታ2006፣ 38)

ወርድወትን ከባህሉ እንድታፈነግጥና ከማህበረሰቡም ጋር እንድትጋጭ ያደረጋት ዋነኛ ርዕሰ ጉዳይ ይሄው በሴት ልጅ ላይ የተጣለ እርግማን ነው፡፡ ከላይ ከቀረበው ሃሳብ እንደምንረዳው ደግሞ ማህበረሰቡ በዚህ ህግ አምኖና ፈርቶ እንደሚተዳደር ሲሆን ወርድወት አሻፈረኝ እኛ ሴቶች በዚህ ህግ አንገዛም ይሻሻልልን በምትልበት ወቅት ባህሏን እንደ ጣሰች መቆጠሯ ግጭት ውስጥ እንድትገባ አድርጓታል፡፡ በመሆኑም የስነ ቃል ምድብ የሆነው እርግማን በእምቢታ ታሪካዊ ልቦለድ ዉስጥ ግጭት እንዲፈጠር ከማድረግ አንፃር ከፍተኛ ሚናን ተጫውቷል፡፡

### 4.2.1.2 ምርቃት

ምርቃትን በተመለከተ *በእምቢታ* ታሪካዊ ልቦለድ ውስጥ ከጉራጌ ብሄረሰብ ጋር እጅግ የተሳሰረ እንደሆነና ምርቃቱም የሚካሄደው በሽማግሌዎች ሲሆን እነዚህ ግለሰቦች በማህበረሰቡ ዘንድ ትልቅ ቦታ የሚሰጣቸውና አድራጊ ፈጣሪ እንደሆኑ፤አንዳች የማስፈጸም ሃይል ከፈጣሪ የተቸራቸው ናቸው ብሎ በማሰብ በነሱ ታዞ አልፈፅምም ያለ አካል አደጋ ይደርስበታል ተብሎም የሚታመንበት ሁኔታ እንዳለና በአጠቃላይ በጉራጌ ባህል መሰረት በምርቃት ያልተጀመረ ጋብቻም ሆነ እርቅ አይፀድቅም ተብሎ የሚታመን መሆኑበዚህ ታሪካዊ ልቦለድ ውስጥ ከጅማሬው እስከ ፍፃሜው ድረስ በተለያዩ ገፆች ላይ ተጠቅሷል፡፡ ለማሳያት ቀጣዩን ከልቦለዱ የተቀነጨበ ምርቃት እንመልከት፡፡

> ወርድወት ሃሳቧን መግለፅ የጀመረችው አንድ ጉዳይ ሊጀምር ሲል የትም ሲደረግ እንዳየችው በምርቃት ነው፡፡ ከተቀመጥንበት በርጩማ እንድንነሳ በምልክት አዘዘችን ፡፡ ቤቱ ቅቤ ቅቤ ይላል፡፡

“እውነት ያናግረን!”አለች ወርድወት፡፡

“አሜን!

“የሽማግሌዎች እድሜ ይርዘም!”

“አሜን!”

“ልጆች አድገው ለቁም ነገር ይብቁ!”

“አሜን!”

“አዝመራችን ፍሬ አይጣ!”

“አሜን!”

“በረቶቻችን በከብት ይሞላ…ጤና እንሁን…መዋደድ መተባበር አይለየን!”

“አሜን!”

“ከኔ የጎደለው ፈጣሪ ይሙላበት!”

አሜን ሙሉ ይሁን(እምቢታ፤ 62)፡፡

ምንም እንኳ ወርድወት ተኮትኩታና ታንፃ ካደገችበት ረጂም እድሜን ካስቆጠሩ የጉራጌ ማህበረሰብ ወግና ባህል ያፈነገጠች ተደርጋ የተቆጠረች ቢሆንና ማህበረሰቡ ከሴት ልጆቻቸውና ሚስቶቻቸው ጋር እንዳትቀላቀል ያገለላት ቢሆንም እርሷ ግን ከባህሉ መካከል የምትወደውና የምትተገብረው እንዳላት ለማሳየትና በዚያ በከረረ ፀብ ውስጥ ሆናና በመሃላቸው የነበረው አለመግባባት እንዳለ ሆኖ ሽማግሌዎቹን እንደምታከብርና የሁሉም ባህል ተቃዋሚ አለመሆኗን ለማመልከት እንደማንኛውም የማህበረሰቡ አባል የሆነ ሰው ብሶቷን ለሸንጎው ከማስረዳቷ በፊት በምርቃት ስትጀምረው ይታያል፡፡ ይህ ደግሞ ተደፈርን በማለት በከፍተኛ ንዴትና ቁጣ ውስጥ የነበሩትን የእጆካ ሽማግሌዎች እንዲረግቡ አድርጓቸዋል፡፡

*በእምቢታ ታሪካዊ ልቦለድ ውስጥ በጉራጌ ማህበረሰብና በማዕከላዊው መንግሥት መካከል፣ በጉራጌ ማህበረሰብና በሌሎች የአካባቢው ማህበረሰቦች መካከል ፍቅርም፣ ጠብም፣ ጦርነትም፣ ዕርቅም ነበር፡፡ እነዚህ ግንኙነቶች በማህበረሰቡ ውስጥ የሚፈጥሩትን አሉታዊና አዎንታዊ ጉዳዮች ግን አንድን ታላቅ ማህበረሰብ በመፍጠር ሂደት ውስጥ የተከናወኑ የሂደቱ መገለጫዎች እንጂ የቂም መቋጠሪያዎች ሆነው አናገኛቸውም፡፡ በአንድ ቤተሰብ*

ውስጥ በሚገኙ ልጆች መካከል የሚኖር መጣላትና መዋደድ የልጆቹ የዕድገታቸው ሂደት አካል እንደሚሆነው ማለት ነው፡፡

በተጨማሪም የዚሁ ታሪካዊ ልቦለድ ደራሲ ፎክሎራዊ ጉዳዮችን በማንሳት የልቦለዱን ግጭት እንዳከረረ ሁሉ እንደዚያ የከረሩ ግጭቶችን በፎክሎራዊ ጉዳዮች መልሰው እንዲበርዱ ሲያደርግም ይስተዋላል፡፡ ደራሲዉ እንደዚያ ጫፍ የወጣን ግጭት መልሶ በፎክራዊ ጉዳይ ማርገቡ አንባቢያን ፋታ እንዲያገኙና በታሪኩ ሂደት ከአሁን አሁን ምን ተፈጠረ የሚሉልብ ሰቀላዎች እንዲረግቡ ለማድረግ ተጠቅሞበታል፡፡ ከነዚህም ውስጥ ጥቂቶቹን እንመልከት፡፡

> በሬው ቀረበ አጋዝ ዳርሳሞ ኬሮ በወጉና በልማዱ መሰረት እጃቸውን በሬው ጫንቃ ላይ አሳርፈው መመረቅ ጀመሩ፡፡
>
> “ዳሞ እድሜህ ይርዘም፤ በልጆችህ ተደሰት፤ ዘርህ እንደ አሸዋ ይብዛ፡፡ “አሜን!”…
>
> አጋዝም “ወርድወት” አሉ ፈገግ ኮራ ብለው፡፡
>
> “ዮ!”
>
> አንቺንም ከውስጤ ነው የምመርቅሽ ….“ወርድወት ብገርልን!”
>
> “አሜን!”
>
> “በመንገድሽ ቆሞ ሊያሰናክልሽ የሚፈልገውን ማርያም እግሩን ቄጠማ
>
> ዓይኑን ጨለማ ታድርገው!”
>
> “አሜን!”
>
> “ወርድወት ሰው ሁሉ እኩል ከእንቅልፉ አይነቃም፡፡ ነቅተሽ ቀስቅሰሺናልና
>
> ልብሽ እንደ ፀሃይ የጠራ ይሁን፡፡
>
> “አሜን!”
>
> “…በእኔ የጎደለውን ማርያም ትሙላበት!” (እምቢታ200-201)፡፡

ምርቃትና የጉራጌ ማህበረሰብ እጅግ የተሳሰሩ እንደሆኑ ከታሪካዊ ልቦለዱ መረዳት ይቻላል፡፡ እያንዳንዱ ጉዳይ ከመፈፀሙ በፊት የሚጀመረው በምርቃት ነው፡፡ ወርድወት እንደዚያ ከማህበረሰቡ ወግና ባህል ያፈነገጠች “እብድ”፣ “ባለዛር”፣ “በሽተኛ” ተብላ ስም

እንዳልተሰጣትና ከፍተኛ ግጭት ውስጥ እንዳልገባች ሁሉ፣ እንደዚያ ያመነቻቸው ሴቶች ትተዋት ቀርተው ብቻዋን ታግላ የራሷን ፍች አስፈፅማ የመጀመሪያ ባሏን ፈታ ያለ ማንም አጋዥና ረዳት በራሷ ፈቃድ ሁለተኛውን ባሏን የጌረሞ ፉጋን እንዳላገባች ሁሉ፣ በታሪኩ ማብቂያ ላይ አንዳንዶቹ በሃሳቧ እየተስማሙና ይቅር እያሏትና እየመረቋትም መጥተው ነበር፡፡ ከነዚህ መካከል አንዱ የተበዳዩ ፣ "አልፈልግህም እምቢኝ አንተ የኔ ባል መሆን አትችልም" ብላ ጥላው የሄደችው የወርድወት የቀድሞ ባለቤት የአጋዝ አባት ዳርሳሞ ኬሮ ነበሩ፡፡ ዴርሳሞም በወርድወት ትዳር ደስተኛ እንደሆኑ ወርድወት ልጃቸውን ያዋረደችና የበደለችውን ሁሉ ረስተው በመጨረሻም ሃሳቧን የሚደግፉ እንደሆኑ በምርቃት ገልፀውላታል፡፡ እንደዚያ ከሮና የአንባቢዉን ልብ ቀስፎ በመያዝ ሲያስጨንቅ የነበረዉንም ስሜት ከስነቃል ዘርፍ ውስጥ አንዱ በሆነው በምርቃት ሲረግብ ይታያል፡፡ በመሆኑም ምርቃት በልቦለዱ ታሪክ ውስጥ ተፈጥሮ የነበረን ከፍተኛ የሆነ ግጭት እንዲሁም ከግጭቱ ጋር አብሮ ሲጋጭ፣ከገፀባህርያት ጋር አብሮ ሲታመምና ሲቆስል የነበረዉ የአንባቢን ልብ ለማሳረፍና የንባብ እፎይታን በመስጠት ረገድ ትልቅ ፋይዳ አበርክቷል ማለት ይቻላል፡፡

### 4.2.1.3 ምሳሌያዊና ፈሊጣዊ አነጋገሮች

በእምቢታ ታሪካዊ ልቦለድ ውስጥ ከተነሱ ምሳሌያዊ አነጋገሮች መካከል አብዛኞቹ በሴት ልጅ ላይ የተባሉ ሲሆኑ ሴቶችንም የሚገልፁት በአሉታዊ ጎኑ መሆኑ ለመረዳ ተችሏል፡፡ ቀጣዮቹን ለአብነት እንመልከት

"የሴት ልጅ ልብ እንደ ጃርት ነው እሾህ ያበቅላል" እምቢታ (100)፡፡

"ደረቅ ሴት ውልቅ ውልቅ እንደሚል እንደ በሬ ቀንበር ናት" እምቢታ (197)፡፡

"ሴት ልጅ ብቻ የወለደ አባት አባት ነኝ ቢል አያምርበት" እምቢታ (141)፡፡

"የሴት ልጅ ልብ እንደ ወፍ ነው" (እምቢታ፣166)፡፡

ከላይ ለአስረጂነት የቀረቡት ምሳሌያዊ አነጋገሮች እንደሚገልፁት ማህበረሰቡ ለሴቶች ያለው ቦታ ከወንዶች አንፃር ሲታይ አናሳ እንደሆነና ሴት ልጅ የማትታመን፣ ሴት ልጅ ያሏትን እሺ ከማለት ውጭ በራሷ የምትፈጥረው አንዳችም አቅም እንደሌላትና ይህንን መብት ካገኘች ባህላቸው በሴቶች ሊናድና ሊጣስ እንደሚችል የሚያመላክት ነው፡፡ ይህ አይነቱ ሃሳብ ደግሞ በወንዶች የበላይነትና ፈላጭ ቆራጭነት ፣ ባህሉ ሴቶችን ገድቦ

ለወንዶች በሚፈቅደው ህግ አንተዳደርም አሻፈረኝ ባሉ እንደነ ወርድወትንና መሰሎቿ ሃሳብ እና ፍላጎት ጋርየሚጣረስ በመሆኑ እንዲህ በየ መሃሉ የሚገቡና ሴቶችን በአዎንታዊ ሳይሆን በአሉታዊ መንገድ የሚገልጹ ምሳሌያዊ ንግግሮች በሴቶችና በወንዶች መካከል እንዲሁም ባህሉ ወንዶችን አንግሶ በተቃራኒው ሴቶችን በተለያዩ መንገዶች የሚገድብ በመሆኑ በእነ ወርድወት አይነት ሴቶች እና በባህሉ መካከል ያለውን ግጭት ይበልጥ እንዲባባስና ጫፍ እንዲወጣ አድርጎታል፡፡ በአጠቃላይ በታሪካዊ ልቦለዱ ውስጥ የሚገኙ ምሳሌያዊ አነጋገሮች በታሪኩ በተለያዩ ክፍሎች በመግባት ግጭቱን ከማክረር ረገድ አስተዋፅኦ ሲያበረክቱ ተስተውለዋል፡፡

በተመሳሳይ መልኩ *በመኤኒት* ልቦለድ ውስጥም ምሳሌያዊና ፈሊጣዊ አነጋገሮች የልቦለዱን ግጭት እንዲባባስና ገፀ-ባህርያቱ ወደከፋ ደረጃ እንዲዳረሱ የማድረግ እገዛ ሲያደርጉ ይስተዋላል፡፡ ቀጣዮቹን አስረጂዎች ከልቦለዱ ታሪክ በመውሰድ እንመልከት፡፡

> አትናቦል እጆቿን ከኋላ ጠርቅሞ እንደያዘ እንድትረጋጋ እየጮኸ ተናገረ፡፡ “እኔ ነኝ ተራ አንቺ የማትረቢ? ተራ ማለት ልክ አንቺ ነሽ፡፡ ወርቅ ሲያነጥፉልሽ አመድ ላይ የምትንከባለይ፡፡ የትም ስትንዘላዘይ የበረሃ ጅብ የዘነጠለሽ አህያ አንቺ ነሽ፡፡ ታውቂኛለሽ አይደል እኔ ሃዊ ስንቱን አመድ እያስቃምኩ አተላ እያጠጣሁ እንደኖርኩ፡፡ ባንቺ ነው የተናቅኩት ፤ ቤተሰባችን ፋንድያ ላይ የወደቀው በአንቺ ነው…” (መኤኒት፤272) አፅንኦት የራሴ፡፡

ከላይ የምንረዳው በፍራኦል እና በታላቅ እህቷ በሃዊ መካከል የነበረን ግጭት ሲሆን ፍራኦል በነሃዊ አይን የማይገባውንና ደሃውን አለምሰገድን ብላ ወደማታውቀው ስፍራ በመሄዷ ክብራቸውን ያጡ ፣ የተዋረዱና የተናቁ የመሰላት ሃዊ ፍራኦል ከአለምሰገድ ጋርየጀመረችውን ግንኙነት እንድታቋርጥ ለማድረግ በምትሞክርበት ወቅት በሁለቱ መካከል ከፍተኛ የሆነ ግጭት ይፈጠራል፡፡ ይህ ግጭት እንዲከርና እስከድብድብ ድረስ እንዲደርሱ ያደረጋቸው ደግሞ ሁለቱም ከአንደበቶቻቸው የሚያወጧቸው ፈሊጣዊና ምሳሌያዊ አነጋገሮች እንደሆኑ ከታሪኩ እንዲህ ለመረዳት ተችሏል፡፡ በመሆኑም ደራሲያኑ እነዚህን የስነቃል ምድብ የሆኑ ምሳሌያዊና ፈሊጣዊ አነጋገሮች በልቦለዱ ታሪክ ውስጥ በገፀ ባህሪያት መካከል የተፈጠሩ ግጭቶችን ይበልጥ ለማክረር ጥቅም ላይ አውሏቸዋል፡፡

### 4.2.1.4 ፉከራ

*በመኤኒት* ልቦለድ ውስጥ በርካታ ፎክሎራዊ ጉዳዮች ግጭቱን ለማጦዝ ገብተው እናገኛቸዋለን፡፡ ለምሳሌ በፍራኦልና በእህቷ በሃዊ መካከል ፤ በአትናቦልና በአለምሰገድ እንዲሁም በሃዊና በአለምሰገድ መካከል፤ በፍራኦልና በደፈራት ወጣት መካከል ፤ በአለምሰገድና ፍራኦልን ለመጥለፍ በመጡት ወጣቶች መካከልና በሌሎችም የድርጊቱ አንቀሳቃሽ በሆኑ ገጸባህርያን መካከል ሰው ከሰው ጋርየሚያደርጋርቸው ግጭቶች ሲከሰቱ ይስተዋላል፡፡ የስነቃል ምድብ የሆነው "ፉከራና" የተፈጠረውን ግጭት በማጦዝ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ሲያደርግ ይስተዋላል፡፡ ለማሳያነት ቀጣዩን ከልቦለዱ የተቀነጨበ ፅሁፍ እንመልከት፡፡

> ከሚች ወገኖች ወጣቶች የሆኑት ለበቀል ጦራቸውን መዘው እየፎከሩና እያቅራሩ ሲገሰግሱ ሴቶቹ ደግሞ ከጀርባቸው በመሆን ያበረታቷቸዋል፡፡ "ኤዴ ማሎ ክዬይ ታችካዳይ ትላለች አንዷ፡፡ "ከቤተ ዘመድ ውስጥ አንድ ወንድ ሰው ቢኖር የሚቹን ፈንታ ጠላቱን ይገድል እንደነበር አስረግጣ ለመናገር፡፡ የሴቷን ንግግር የሰማ ወንድ ሁሉ በበቀል ስሜት እንደ ፊጋ በሬ እያጉረመረመ የበቀል ቀንዱን እያሾለ ቀጠለ፡፡ "አኦዬማጭዳይ ባክ ከኦሰክና " አለች ሌላዋ ሴት በጩኸት ከጀርባ ሆና፡፡ ወንድ ከሆናችሁ አትልቀቁ ጨርሷቸው ማለቷ ነበር ለወንዶቹ፡፡ "ሃሹ እንዳቦይ ..... ሃሹ እንዳቦይ፤.... ሃሹ እንዳቦይ" ተጯጯሁ ፎከሩ ሴቶቹ፡፡ "እሰይ ግደሉት ፤...እሰይ ግደሉት፤.... እሰይ ግደሉት" የሴቶቹን መንጫጫትየሰሙት ወንዶቹ አካባቢውን አደበላለቁት (መኤኒት፤174)፡፡

*በመኤኒት* ብሂረሰብ ዘንድ ሰው የገደለ ሰው መግደሉን አምኖ በአፋጣኝ ወደተገዳይ ቤተሰብ ዘንድ ሽማግሌዎችን ካልላከና እርቅ ካልተፈጠረ የሚኖረው እልቂት ቀላል አይደለም፡፡ የተገዳይ ቤተሰቦች የገዳይን ዘር ማንዘር እየፈለጉ ከማጥቃትና ደም ከመመለስ ወደ ኋላ አይሉም፡፡ ከላይ ከልቦለዱ የተረዳነውም ይህን ነው፡፡ በአንድ ሰው መገደል ምክንያት የተጀመረው ግጭት ተባብሶ በርካታ የሰው ህይወት ሊጠፋ መድረሱንና ግጭቱ እጅግ እየተባባሰ እንደሄደ እንረዳለን፡፡ ይህንንም ለማድረግ ከፍተኛ እገዛ ያደረገውበፉከራ ወቅት ሴቶቹ ከወንዶቹ ጀርባ በመሆን በሚቀሰቅሱት ወኔ ነው፡፡ በመሆኑም የስነ ቃል አንድ ምድብ የሆነው ፉከራ የልቦለዱ ግጭት እንዲከርና እንዲጦዝ ምክንያት በመሆን አገልግሏል፡፡

### 4.2.1.5 ቃል ግጥም

በእምቢታ ታሪካዊ ልቦለድ ውስጥ ከፎክሎር ዘውጎች መካከል የሥነ-ቃል ምድብ የሆነው የሙገሳ ቃል ግጥም በታሪካዊ ልቦለዱ የተቀረፁትን ገፀ-ባሕርያት ማንነት ከመግለፅ ረገድ ጉልህ ሚና አበርክቷል፡፡በታሪካዊ ልቦለዱ ውስጥ በርካታ የሙገሳ ቃል ግጥሞች የሚገኙ ሲሆን ቀጣዮቹን ለአብነት ያህል እንመልከት፡-

አሰስ ገሰሱን አግበስብሶ፤

ብርቱዎችን አስጎንብሶ፤

አቻ -መሳይ- እኩያ አጥቶ፤

ግዳይ ጥሎ- ሃዲያን አልፎ፤

ምርኮ አብዝቶ፤ ከብቱን ነድቶ፤

ያን ተራራን-ዘቢዳርን-በልቡ ይዞ፤

ዋቤ ወንዝን በዋና አልፎ፤ፈረሱንም አስጀግኖ፤

ጠላቶቹን አንቀጥቅጦ ፤ዋርካዎቹን ስንጥር አርጎ፤

በየጓሮው አስፈርጥጦ፤ጀግናቸውን አስሸንቶ፤

ይኖራል ሲሏችሁ እመኑ፤

አጋዝ ነውና ማዕረጉ- ክንዱ ለጦር የበረታ፤

ፋርችዬ ነውና ስሙ-ትዕቢተኛን የሚረታ፤

አኸ ነውና ጎሳው፤

ወርድወት ናትና ሚስቱ፤

የቃቄ ልጅ- የሙህር ልጅ -የጀግናይቱ፤

አፌም አይበቃ ለመናገር፤

ስለዚህ ሰው ለመመስከር….”(እምቢታ፤26-27)

ይህ የሙገሳ ቃል ግጥም በጉራጌ ምድር በዘመኑ ታዋቂ የነበረ ጅረ በነስዬ የተባለ ዌየግ ደርዳሪ አጋዝ ፋርችዬ ከቃቄ ወርድወት ጋርጎጆ የቀለሰ ሰሞን የገጠመው የማወደሻ ግጥም ሲሆን ደራሲው በዚህ ቃል ግጥም አማካይነት የበርካታ ገፀ-ባሕርያትን ማንነት እንድንረዳና ከግለሰብም አልፎ የጎሳቸውን በማህበረሰቡ ዘንድ ተፈላጊነትም ጭምር

ጋርእንድንተዋወቅ ያደርገናል፡፡ በዚች አጭር ቃል ግጥም ተጠቅሞ የአጋዘን ፣ የወርድወትን ፣ የቃቄንና የኸዣ ጎሳን ማንነት አሳይቶናል፡፡ ቀጣዩ ደግሞ ለሌላ ጀግና የተገጠመ ቃል ግጥም ነው፡፡

“የጌረሞ ፉጋ፣አይታክቴው ፍጡር፣እንቅልፉን ገዳይ
የጌረሞ ፉጋ፣ የሰባት ቤት ሰማይ ፣ የቸሃው ፀሃይ
የጌረሞ ፉጋ፣ ሸሸትን አያውቄ ፊት ለፊት ቀዳሚ
የጌረሞ ፉጋ ፍምና በረዶን በህልሙ ተርጓሚ” እምቢታ(152)፡፡

ይህንንም ቃል ግጥም የገጠመው ጅረ በነስዬ ሲሆን ስለዚህ የዌየግ ደርዳሪ በታሪካዊ ልቦለዱ ውስጥ እንዲህ ተገልፆለታል፡፡ ”ጅረ በነስዬ ባይመጣ ኖሮ ዘመድ ጥየቃ ስሄድ አሳድሩኝ መሸብኝ ባይል ኖሮ ምሽቱ ያማረና የተዋበ ይሆን ዘንድ “ለዊክየር” ማለትም ለምሽት ሸንጎ የመጡ ሰዎችንና አሳዳሪዎቹን ለማዝናናት ብሎ “ዌየግ” መደርደር ባይጀምር ኖሮ የጌረሞ ፉጋን እንዴት በዚህ ልክ ላውቀው እችል ነበር” (ገፅ፣152)፡፡ ከላይ ከቀረበው የማወደሻ ቃል ግጥም የምንረዳው የገፀ-ባሕሪውን ማንነት ነው፡፡የጌረሞ ፉጋ ጀግና የማይፈራ፣ የማይሸሽና የማይታክት መሆኑን ደራሲው ይህንን ቃል ግጥም በማምጣት የገፀ ባህሪውን ማንነትና ግለሰቡ በማህበረሰቡ ዘንድ ያለውን ቦታና ተቀባይነት ሊያሳየን ችሏል፡

በአጠቃላይ በሁለቱም ስራዎች ተለይተው የቀረቡት የስነቃል ምድቦች አብዛኞቹ የገቡት የልቦለዶቹን ግጭት ለማጠዝ (ለማክረር) ሲሆን አልፎ አልፎም ግጭቱን ለማርገብ አገልግሎት ሲሰጡም ተስተውለዋል፡፡ ግጭት በአንድ የሥነ-ፅሁፍ ስራ ውስጥ የታሪኩን የሂደት አቅጣጫ የሚያሳይ ከመሆኑም በተጨማሪ የፅሁፉ የጀርባ አጥንትም ነው፡፡ ደራሲያን በድርሰት ሥራቸው ውስጥ የሚያቀርቡት የልቦለዱን ታሪክ እየተረከ ከገጽ ወደ ገፅ ከምዕራፍ ወደ ምዕራፍ በድርጊት እያዘገመ ለታሪኩ አንድነትና ውህደት ልብን ሰቅሎ እስከፍፃሜው ድረስ የሚጓዘው በግጭት ነው፡፡ የአንባቢያን ስሜትን ጠርንፎ በመያዝ በገፀባህሪያቱ ድርጊት በሄደበት አቅጣጫሁሉ እያነፈነፈ የመጨረሻ ውጤቱን ለማግኘት በጉጉት የሚከተለው የታሪኩ ሂደት በግጭት ላይ ተሰናስሎ ሲገኝ ነው፡፡ በመሆኑም ደራሲያኑ በሁለቱም ስራዎች ውስጥ እነዚህንና መሰል ፎክሎራዊ ጉዳዮችን መጠቀማቸው የልቦለዱ ግጭት እንዴ እየከረረ በተቃራኒው እየረገበ የአንባቢያንን ልብ በመስቀልና በማርገብ ድርሰቱ ተወዳጅ እንዲሆን ከማስቻሉም በላይ ኪናዊ ውበትም እንዲላበስ አድርጎታል፡፡

### 4.2.2 ሃገረሰባዊ ልማድ

ሃገረሰባዊ ልማዶች ማህበረሰቡ በተደጋጋሚ የሚከውናቸው ድርጊቶች ሲሆኑ በሁለቱም ሥነ-ፅሁፋዊ ስራዎች ውስጥ የሃገረሰባዊ ልማድ ምድብ የሆኑ ሃገረሰባዊ እምነቶች ሰፊውን ቦታ የያዙ ሲሆንክብረ በዓላትና ሃገረሰባዊ ስያሜዎችም ተወስተዋል፡፡

#### 4.2.2.1 ሃገረሰባዊ እምነት

ሃገረሰባዊ እምነትን በተመለከተ ከሌሎች ፎክሎራዊ ዘውጎች በተለየ ሁኔታ በሁለቱም ስራዎች ውስጥ ሰፋ ብለው የተቀመጡ ሲሆን እምነቶቹም በማህበረሰቡ አባላት ዘንድ እውነት ተብለው የተቀበሏቸውና ለሚያምኑበት ጉዳይም የራሳቸው የሆነ ምክንያት ወይም ማብራሪያ የሚያቀርቡባቸው ናቸው፡፡

ወርድወትን አገባለሁ አታገባም በሚሉ በዳሞ ኑሪና በልጃቸው በጌረሞ ፉጋ መሃል የነበረውን ግጭት ስንመለከትም ግጭቱ ሲጦዝ የነበረው በፎክሎራዊ ዘርፍ ውስጥ የሃገረሰባዊ ልማድ ምድብ በሆነው በሃገረሰባዊ እምነት አማካይነት ነው፡፡ ቀጣዩን ቅንጫቢ ፅሁፍ ለአስረጂነት ከልቦለዱ ወስደን እንመልከት

> ልጄ ትልቁ ነገር እሱ አይደለም! ቆጣ አሉ ዳሞ ኑሪ፤እሺ መባልህ አይደለም፡፡ ወርድወት ብቻዋን አይደለችም፡፡ ብቻዋን አይደለምእየተንቀሳቀሰች ያለችው፡፡ ሃሳቦቿ የሷ አይደሉም፡፡ ዛር ወርዶባታል፡፡ ይሄ ነው ብለን የማናውቀው ዛር በሷ ላይ አድሯል፡፡ ትዳራችን እንዳይፈነቀል ብለን እኮ ነው መብቷን የሰጠናት፡፡ ወንዶች ሁለት ሶስት ካገቡ እኛም እናግባ ባንድ ተወስነን መቅረታችን ለምንድነው ብሎ መጠየቅ የጤንነት ነው? አሁን ያዛር ከየት እንደመጣች ያላወቅካት ዓላማዋ ምን እንደሆነ ገብቶኛል፡፡ ሰማህ ልጄ….ይህ በወርድወት ላይ ያደረው ዛር እኛ ወንዶች የቦዝ ተጠሪ መሆናችንን በፍፁም የወደደው አይመስለኝም፡፡ በፊትም ሴት ነበረች የዚህ ተልእኮ መሪ…ቀስ በቀስ እኛ ወንዶች እጅ ገባ፡፡ አሁን ደግሞ ወደነበረበት ይመለስ ብትልስ? ሴት ናት የአምላክ የቅርብ ተጠሪ መሆን የሚገባት ብትልስ?
>
> ብትልስ? በላ መልስልኛ?
>
> ትውሰደዋ!
>
> ትውረሰው? ትውሰደው? የጓሮ ጎመን መሰለህ? የባህር ዛፍ ቅጠል መሰለህ?
>
> ቦዝ ጠብቆ ያቆየውን የአምልኮ መንፈስ ትውሰደው የምትለው? ተቆጡ፡፡

. ምን ጎድሎብህ ነው ወደ ወርድወት ያስመለከተህ፤ ቁልቁል ወርደህ? ታላቅህን? አግባታ የፈታችውን? የአመፃ ዛር የሰፈረባትን?

"አባዬ ወርድወትን ማግባት እፈልጋርለሁ፤ እሷን ብቻ!"

"ቦዝ እሷን እንድትጠላ ካላደረገህ የለማ!በእኔ ላይ አላደረማ!"

"ሽማግሌ ላክና...."

"ቆሜ ነው ሞቼ?" ተቆጡ (እምቢታ፤140-141)፡፡

ከላይ የተመለከትነው በአባትና ልጁ መሃል ያለው አለመግባባት እየከረረ እየከረረ መጥቶ ግጭቱ ሲጦዝ ነው የግጭቱም መባባስ የተገለፀው በፎክሎራዊ ጉዳዮች አማካይነት ነው፡፡ "ቦዝ" ነባር አምልኮ ሲሆን በአብዛኛው ሰባት ቤት ጉራጌ ሙህርን፤እኖርን፤እነሞርን ሳይጨምር ከጥንት ጀምሮ የሚመለክ ነው፡፡ የ"ቦዝ" አምላኪዎች አብዛኞቹ ወንዶች ናቸው፡ ፡ ምክንያቱም ወንዶች የቦዝ መንፈስ ሁሌም በጦርነትም ፤ በድልም ወቅት አብሮን ዘምቶ ያግዘናል እኛ ወንዶች የቦዝ መንፈስ አብሮን ስላለ ጠንካሮች አድርጎናል ብለው ስለሚያምኑበት፡፡ ወንዶች ቦዝን የመብረቅ አምላክ ፤ሃይል ሰጪው፤ ብርታት አመንጪው፤ ባለ ነጎድጓዳማው ድምፅ እያሉም ይጠሩታል፡፡ ሴቶቹ ግን አብዛኞቹ በየዋኋና በማህፀን አለምላሚዋ "በደማሚት" ነው የሚያምኑት፡፡ ዳሞ ኑሪም የቦዝ እምነት ተከታይ ናቸው፡፡ "ቦዝን" በጽኑ የሚያምኑ "የቦዝ" መንፈስ በእኔ ላይ አድሯል የሚሉ አይነት ሰው ናቸው፡፡ ለዚህም ነው ከልጃቸውጋርግጭት ውስጥ የሚገቡት፡፡ ቦዝ ደግሞ የማህበረሰቡ የቆየና አብሯቸው ዘመናትን የተሻገረ ማንነታቸውን የሚያንፀባርቁበት ሃገረሰባዊ እምነታቸው ነው፡፡ እነዚህ አምላኪዎች ደግሞ የቦዝን እምነት የሚቃረን ባዕድ አምልኮ አድርገው ከሚቆጥሩት አንዱ "ዛር" ነው፡፡ አንድ ሰው ከሚያውቁት እና ከተለመደውውጭ ሲሆንባቸውና ከባህላቸው አፈነግጣለሁ ሲል የጤንነት አይደለም ብለው በማሰብ አንዳች ሃይል በውስጡ ይኖራል ብለው ያምናሉ፡፡ ያም ሃይል አምላካቸውን የማይፈልግ በሴቶች ላይ ያደረ መጥፎ መንፈስ ነው በማለትም አጥብቀው ይቃወሙታል፡፡ ዳሞም ወርድወት ብቻዋን ሳትሆን ዛሩ ነው እንዲህ እንድትናገርና ከባህሉ እንድታፈነግጥ ያደረጋት ብለው በማመናቸው ነበር ልጃቸው እንዳገባት በመከልከል ከልጃቸውጋርከፍተኛ ግጭት ውስጥ የገቡት፡፡

"ዛርም" ልክ እንደ "ቦዝ" ሁሉ ከሃገረሰባዊ ልማድ ዘርፍ የሆነ በሃገረሰባዊ እምነት ምድብ የሚገኝ የፎክሎር ዘር ነው፡፡ ስለዚህ ደራሲው እነዚህን ፎክሎራዊ ጉዳዮች ደጋግሞ

ለድርሰቱ መጠቀሙ በገፀ ባህርያት መካከል የሚኖርን የሃሳብ አለመግባባት አክርሮና አጡዞ ማህበረሰቡ ለነዚህ መሰል ልማዳዊ እምነቶች ምን ያህል የተገዛ እንደሆነ እያሳወቀን በተጓዳኝም ግጭቱ የት ደረጃ ላይ እንደደረሰ ለአንባቢያን ለማሳየት ተጠቅሞበታል፡፡

*በመኤኒት* ልቦለድ ውስጥም በተመሳሳይ ሁኔታ በማህበረሰቡ ሕይወት ዘንድ ከፍተኛ ጠቀሜታ ያላቸው የሃገረሰባዊ እምነት ዘርፎች የተጠቀሱ ሲሆን አንደኛው"አንጀት ማንበብ" ነው ይህ ስርዓት ለመኤኒት ሽማግሌዎች ብቻ የተሰጠ የፈጣሪ ፀጋ ተደርጎ የሚወሰድ ሲሆን የተደበቁ እውነቶችን ፈልፍሎ የማውጣትና እርቅንም ለማውረድ የሚጠቀሙበት ነው፡፡ ሌላው በልቦለዱ ውስጥ የታየው እምነት "ገድ" ሲሆን ይህም ጥሩ እድልን የሚያበስር ነው፡፡ ፍራኦልና አለምሰገድ በእንግድነት አዛውንት ኬላገ ቤት ሲገቡ የአዛውንቱ ልጅ ሴት ትወልዳለች አዛውንቱም "እግራችሁ እርጥብ ነው" በማለት የልጅ ልጃቸውን ስም ፍራኦል በማለት ሲሰይሟት በልቦለዱ ላይ ተጠቅሷል፡፡ ከነዚህ በተጨማሪ በዚህ ልቦለድ ውስጥ "ቃምሱት" የሚባል ሬሳ አውጥቶ የሚበላ ጎሳ አለ ብለው የሚያምኑ መሆኑ አንጀት መጓተት፤ በደም መታጠብ፤ ፍየል ወይም በግ ቀጥቅጦ መግደል፤ ደም መራመድ ወዘተ በልቦለዱ ውስጥ የተጠቀሱ እምነቶች ሲሆን እነዚህ ሃገረሰባዊ እምነቶች መነሻቸው የማህበረሰቡ ባህል በመሆኑ የማህበረሰቡ የረጂም ዘመን የህይወት ተሞክሮው እውነት እንደሆኑ የሚያረጋግጥባቸውና ቦታ ሰጥቶ የተቀበላቸው ድርጊቶች ናቸው፡፡*የመኤኒት* ልቦለድ ደራሲ የልቦለዱን የጀርባ አጥንት የሆነውን ግጭት በርካታ ፎክሎራዊ ጉዳዮችን ተጠቅሞ እንዳከረረው ሁሉ ሃገረሰባዊ ልማዶችን ተጠቅሞ እንደዚያ የከረረና ጫፍ የወጣን ግጭት መልሶ ሲያወርደውና ሲያረግበው እንመለከታለን ፡፡

> *በሩ ላይ ወጠጤ በግ አለ፡፡ የሚች ወንድም ሆኖ የቀረበው የአዛውንቱ ኬላገ ሁለተኛ ልጅ በጓን በተሰጠው ረጂም ጦር ለመውጋርት ተዘጋጀ፡፡ ትእይንቱን ለመታደም በተሰበሰቡት መካከል እጁን ወደ ላይ ከፍ በማድረግ "ይህ ጦር እኛን የሚችና የገዳይ ወገኖችን ሳይሆን ይሄንን በግ ይውጋ" ብሎ በበጉ የቀኝ አንገት ላይ ሰካው፡፡ ተንፈራፈረ ወዲያውኑ ሰዎች ቢላዋ አምጥተው አንገቱ ታረደ፡፡ ከበጉ የሚፈሰው ደም በቅል ተቀዳ፡፡ ከዚያ የገዳይ ወገንን የወከለው የአዛውንቱ ሁለተኛ ልጅ እና የሚች ታላቅ ወንድም ፤ የታረደዉን በግ ደም በመራመድ ችግርን፤ መበቃቀልና ለጠብ መፈላለግን ተሻገሩት፡፡ እንደበጉ ሁሉ አንድ ወይፈን ቀረበ፡፡ ወይፈኑንም ሁለት ሰዎች ግራና ቀኝ ጥርቅም አድርገው ያዙት፡፡ ሰውየውም ኢላማውን አስተካክሎ የወይፈኑ ግንባር ላይ ጥቂሩን ድንጋይ አሳረፈው፡፡... በአስታራቂ ሽማግሌዎች የታዘዙት ሰዎች ወይፈኑን ፈጥነው መበላለታቸውን ቀጠሉ፡፡ በጥቂት ጊዜውስጥ የወይፈኑ አንጀት በአንጀት አንባቢዎች ይታይ ጀመር፡፡ አንብበው የሚናገሩት ሰዎች እርቁን*

እውነተኛነት እና ያለቅራኔ መካሄድ ለማረጋርገጥ ምርመራውን ቀጠሉ፡፡ "….የሰላም ነው ጥሩ እርቅ ነው" አሉ ሁለት አንጀቱን አንብበው ትርጉሙን አውቀናል ያሉ ሰዎች፡፡

በሁለቱ መካከል የተሻለ መቀራረብና ዘና የማለት መንፈስ ቀጠለ፡፡ ከሃገር ሽማግሌዎች በእድሜ ጠና ያሉት ታዋቂው ኪርቴጅ የታለበ እና የተጠበሰ ርዝመቱ አንድ ሜትር የሚደርስ የወይፈን አንጀት ይዘው የአዛውንቱ ኬላጊ ሁለተኛ ልጅ ከገዳዩ ወገን፣የሚች ወንድም ደግሞ ከሚች ወገን ተጠራርተው ፊት ለፊት እንዲቀመጡ ተደረገ፡፡ ሁለቱም እጆቻቸውን በጉልበቶቻው ዙሪያ ለጥፈው ተቀመጡ፡፡ ያለምንም የአይን ርግብታ ተፋጥጠው መታየት ጀመሩ፡፡ ትርጉሙ በሁለቱ ወገኖች መካከል የተፈጠረውን በአይን ቁራኛ መተያየትና ለመበቃቀል የመፈላለግ ድርጊት የሚያሳይ እና የተፈጠረውን ሃይለኛ መካረር የሚያመላክት ነው፡፡ ሽማግሌው ቅርቴች የአንጀቱን አንደኛ ጫፍ በሚች ወንድም አፍ ሌላውን ደግሞ በአዛውንቱ ልጅ አፍ ውስጥ አድርገው ነክሰው እንዲወጥሩት አደረጉ፡፡ ሁለቱም ተወካዮች አይኖቻቸው ፈጠው በአፋቸው ያለውን አንጀት ወጥረው መተያየት ቀጠሉ፡፡ "በሏ" አሉ ሽማግሌው በቀስታ አንጀቱን የመብላት ስርዓት እንዲፈፀም በማዘዝ፡፡ የሁለቱ አፍ መጠጋጋት ሲጀምር የአገር ሽማግሌው ቅርቼት ረጂም ጦራቸውን ሰድደው የተወጠረውን አንጀት በጠሱት…(መኤኒት፣ከ219-23)፡፡

*በመኤኒት* ብሄረሰብ ዘንድ በበዳይና በተበዳይ መሃል ያለን የተካረረ ጠብ ለመበጠስ ጦር አስፈላጊ ሲሆን አይተናል፡፡ ጦር የሚችና የገዳይ ወገኖች እንዲስማሙ ሰው ሳይሆን በምትካቸው በግ እንዲወጋ ሲደረግበት ተመልክተናል፡፡ በማህበረሰቡ እምነት መሰረት የበግ ደም በቅል ተቀድቶ የገዳይና የተገዳይ ወገኖች ደሙን በመራመድ መበቃቀልንና ለጠብ መፈላለግን ሲሻገሩት ከመፅሃፉ ለመረዳት ችለናል፡፡ የወይፈን አንጀት ወጥቶ በአንጀት አንባቢዎች ተነቦ እርቁ የሰላም እንደሆነ ተነግሮበታል፡፡ ከዚህ ፅሁፍ መረዳት እንደሚቻለዉ አንጀት ትዕምርታዊ ፍቺን ያዘለ ሲሆን የሚወክለዉም መኤኒቶች ልክ እንደ አንጀት ሁሉ የተያያዘ የዘር ሃረግ ያላቸዉና አንደኛዉ ላንደኛዉ ወገኑ እንደሆነ ከመሃል አንዱ ቢጎድል እንደሚጎዱ ለማመልከት የገባ ነዉ፡፡ የበዳይና የተበዳይ ወገን የሆኑ አካላት አንጀቱን ወደ አፋቸዉ በመሳብ የሚጓተቱትም እንዲሁ አንዳች ዓላማ ሲኖረዉ የራስን ገመና ለራስ የአንዱን ጉዳት ሌላዉ የኔ ብሎ አምኖ እንዲቀበለዉ ለማድረግ ነዉ፡፡ በአጠቃላይ ከላይ የተዘረዘሩት በሙሉ ሃገረሰባዊ ልማዶች ሲሆኑ በገዳይና በሚች ወገኖች መሃል የነበረን የተካረረ ጠብ በማርገብና በምትኩ እርቅን በመፍጠር አገልግለዋል፡፡

ህልም ከፎክሎር ዘርፎች ውስጥ በሃገረሰባዊ ልማድ ስር የሃገረሰባዊ እምነት የሚልኪ ምድብ ነው፡፡ በሰው ልጅ አስተሳሰብ ውስጥ የኖረና የተለያየ ፍቺን የሚይዝ ሲሆን

በባህላዊ አመለካከት አንድ ሰው ሲተኛ ፍላጎቱን እንዲሁም ወደ ፊት ስለሚከሰቱበት ክስተቶች በኢንቁ አእምሮው ክፍል የሚያየው ነው (ዘሪሁን፣1992፣211)፡፡

*በእምቢታ ታሪካዊ ልቦለድውስጥ ዋናዋ ገፀባህሪ ወርድወትና የአጋዝ አገልጋይ አባባ ወርድወት ወደፊት በታሪኩ ውስጥ ሊገጥማት ስለሚችል ድርጊት "ህልም" የሚያዩበት ሁኔታ ሰፍሯል፡፡ ሌላው በዚሁ ስራ ውስጥ የዚሁ ምድብ የሆነ "እንጋርዳ" እናገኛለን ባዶ እንስራ የያዘች ሴት መንገድ ማቋረጥ፡፡ "ሟርትም" በዚሁ ልቦለድ ውስጥ የተጠቀሰ ሲሆን አሟረቱብኝ በማለት አጋዝ አገልጋዩ ጋር ግጭት ውስጥ ሲገባ ተጠቅሷል፡፡ ሌላው የተጠቀሰው ሃገረሰባዊ እምነት "ዛር" ነው ወርድወት የመጀመሪያ ባሏን በእምቢታ ከፈታች በኋላ የተሰጣት ስያሜ ሲሆን ብቻዋን ሆና ይህን አልፈፀመችውም ዛር ሰፍሮባታል ስትባልና ስትገለል በታሪኩ ውስጥ ተጠቅሶ እናገኘዋለን፡፡ በልቦለዶቹ ውስጥ ከተገኙት ሃገረሰባዊ እምነቶች ውስጥ ህልምን የሚመለከቱ ፎክሎራዊ ጉዳዮችን ለማሳያ ያክል ወስደን እንመልከት፡፡*

> "መሄድ አልነበረብህም!"አሉት አባባ ያንዲያ፤ "ነግሬህ ፤ እሺ ብለኸኝ ፤ የማይሆን ነገር አይቻለሁ፤ አንተና እሷን የሚያዋህዳችሁና የሚያጋምዳችሁ ነገር የለም ብዬህ…." አሉት፡፡ ከዚህ በኋላ ምን እንደተፈጠረ ዘበርጋ ነው የተረከልኝ በምን ፍጥነት አጠገቤ እንደደረሰ ፤በምን ፍጥነት እጄ ላይ የነበረውን ጦር እንደነጠቀኝ በምን ፍጥነት ጦሩን አባባ እግር ላይ እንደሰካው አላውቅም፡፡ አጋዝ ፋርችዬ ጦሩን አባባ እግር ላይ ሰካ፡፡ ጦሩን?አጋዝ ምን ሆኗል? በአባባ እግር ላይ እንዴት ጦር ይሰካል? አንዴ እጁን አንዴ እግሩን በጠላት በተወጋጊዜ የሚያክሙትን አባባን በጦር? ሰው መድሃኒቱን ያጠቃል? መዳኛውን ያጠፋል?! አባባ ወደቁ፡፡ ዘፍ ብለው ፤እንደተገነደሰ ዛፍ፤በጀርባቸው ወደቁ፡፡ ዋቅ የት ነው ያለኸው?…በብርቱ ቆስለዋል፡፡
>
> "ምናለ እንደጀመረ በጨረሰኝ" አሉ በመከራ "እውነት መናገር ጦር ያስመዝዛል?" አሉ እንባቸው ፈሰሰ፡፡
>
> አጋዝ ያረገውን የሰሙ ጎረቤቶች በቀያቸው እንዲህ ያለ በደል ተፈፅሞ እንዴት ዝም እንላለን ፤ ችላ ብለንስ እንዴት እንተኛን አሉና አጋዝን አነጋገሩት
>
> "በድለሃቸዋል ጦር ሰብቀህባቸዋል ይቅርታ ጠይቅ!" አሉት አጋዝ ይባስ ተናደደ "የተባባልነውን ስላልሰማችሁ ነው!" አለ፡፡

ሰምተነዋል እኮ ጉዳዩን ባትሄድ ይሻልህ ነበር አትሂድ ብዬህ ነበር ማለት - "ድረድከ ተበርቸበራር-[2] በአንድ ሽማግሌ ላይ ጦር ያሰብቃል? ይህ የጉራጌ ልማድ ነው? ከጀግናስ የሚጠበቅ ነው? ሰው ስለሌላቸው ነው አጋዝ? ነው ወይ?

እሳቸው ናቸው ያሟረቱብኝ፡፡ ወደ ቤቷ ስሄድ ባዶ እንስራ ይዛ ወንዝ የምትወርድ ሴት አላጋጠመችኝም ስለዚህ ሊቀናኝ እንደሚችል ገምቼ ነበር፡፡ እሳቸው ናቸው ያሟረቱብኝ በማለትና በመጮህ መታረቅ እንደማይፈልግ አሳወቀ…(እምቢ.ታ፤130-131)፡፡

ከላይ ካለው ሃሳብ እንደምንረዳው የሃገረሰባዊ እምነት ምድብ የሆነውን ሟርት በመጠቀም ደራሲው የፅሁፉን ግጭት ምን ያህል እንዲከር እንዳደረገበት ነው፡፡ አጋዝ የትዳሩ መፍረስ ምክንያት የሽማግሌው ሟርት ነው ብሎ እንዲያስብ ምን ያህልም ፀቡን አካሮት ዘወትር ከጎኑ በመሆን ለእግሩ መጫሚያ የሚሰሩለትን፤ ከጠላት ተዋግቶ ሲመጣ የተጎዳ ሰውነቱን በባህላዊ መድሃኒት እያከሙ የሚያድኑትን አገልጋዩን አባባን ደራሲው በጦር እንዲወጉ ያደረገው ግጭቱ ምን ያህል እየጦዘ እንደሄደ እንድንረዳ ለማድረግ ነው ይህም የሆነው በፎክሎራዊ ጉዳዮች አማካይነት ነው፡፡ ቀጥለን ህልም በልቦለዱ ውስጥ ግጭትን ከማባባስ በተጨማሪ የታሪኩ የንግር ማስኬጃ ቴክኒክ በመሆን እንዴት አገልግሎት ላይ እንደዋለ በማሳያ እንመለከታለን፡፡

ወርድወት ገመድ ለማውጣት ትታገላለች፤ ገመዱን የምታወጣው ከጭኖቿ ስር ነው ከብልቷ ውስጥ፡፡በዚህ ገመድ ሰባት ማገሮችን ለማሰር ትታገላለች፡፡ ማገሮቹ ተቆርጠው የመጡት ከተለያዩ የጉራጌ ክፍለ ህዝብ ነው፡፡ ክፍለ ህዝቡን ወክለው የሚመጡት አጋዞች፤ ኤሰኺአረቦች እና ሌሎች ናቸው፡፡እነዚህ ስመ ጥር ሰዎች ይዘው የመጡትን ማገር ለማሰር ትታገላለች፤ግን አይሆንላትም፤ ገመዱ ይበጠሳል፡፡ እንደተለመደው ሌላ ገመድ ከጭኖቿ ስር ገብታ ከብልቷ መሃል ታወጣዋለች ፤ ግና ሰባት ማገሮችን በአንድ ገመድ ማሰር ከባድ እንደሆነ ይሰማታል በመጨረሻም ገመድ ያልቅባታል፡፡ ትደነግጣለችም፡፡የተቋጠሩትን ለማሰር የምታደርገው ጥረትም ፈታኝ ይሆንባታል…..ሳይሳካላትም ይቀራል (እምቢ.ታ፤113)፡፡

---

[2]"ድረድከ ተበርቸበራር" ይህ ቃል በታሪካዊ ልቦለዱውስጥ በተደጋጋሚ የሚገኝ ሲሆን ሰዎች ከባህላቸው ውጭ የሆነና ያልተለመደ ሁኔታን ሲያዩ የሚሉት ነው፡፡ ትርጉሙም "አታምጣው ወደመጣበት መልሰው፤ አያድርግብን እንደማለት ነው፡፡

እንግዲህ የታሪኩ አብይ ገፀባህሪ የሆነችው ወርድወት ማህበረሰቡ በሴቶች ላይ የጣለውን እግድ እንዲያነሳና በእግዱም ሴቶች እየተበደሉ እንደሆነ በማስረገጥ የሰባት ቤት ጉራጌ ሴቶችን ብቻ ሳይሆን የአጠቃላይ በዘመኑ የነበሩ ሴቶች በደል ቆርቁሯት ፍትህ ለማግኘት ቆርጣ የተነሳች እንስት እንደሆነች ከታሪኩ ለመረዳት ችለናል፡፡ ይሁንና ይህ የወርድወት ልፋትና ድካም በማህበረሰቡ እምቢተኝነትና በሴቶችም እስከመጨረሻው ድረስ ከጎኗ ያለመሰለፍ ምክንያት ብዙ ብትለፋና ብትታገልም ፍሬ ሳያፈራላት ቀርቶ እናገኛለን፡፡ እርግጥ ነው ወርድወት አንቂት ተነስቶላት ነፃ ነሽ ተብላለች፡፡ እንዳሻትም የመረጠችዉን አግብታ መኖር ችላለች፡፡ ነገር ግን ትግሏ ለሷ ብቻ አልነበረም ጭቆናውም በደሉም በሷ ላይ ብቻ የደረሰ አልነበረምና ለአጠቃላዩ ብትታገልም ምንም እንኳ ወርድወት ያሰበችዉን ማድረግ የቻለችና ለዛሬዉ የሴቶች መብት መከበር የራሷን አሻራ ያቀመጠች ቢሆን እርሷ በፈለገችዉ ሰዓትና ዘመን ግን ሁሉንም ሴቶች ነፃ ማውጣት እንደማትችል ደራሲው ለአንባቢያን በንግር መልክ ታሪኩን ለማስገመት ህልምን እንደ ቴክኒክ እንደተገለገለበት ለማወቅ ተችሏል፡፡

በአንዷለም አባተ *መኤኒት* በተሰኘ ስራ ውስጥም በተመሳሳይ ሃገረሰባዊ እምነትን ተጠቅሞ የልቦለዱን ታሪክ ለመንገር (ለመጠቆም) እንዲሁም አንባቢያን ከወዲሁ ጭብጡን እንዲገምቱ ከማድረግ አኳያ ተገልግሎበታል፡፡ ጉዳዩን ከልቦለዱ በተቀነጨበ ማሳያ ቀጥለን እንመለከተዋለን፡፡

> ለመሆኑ ቅዱስ ዳዊት ልጁን ሶሎሞንን ጠርቶ ምን እንዳለው ታውቂያለሽ?
> “መጽሃፍ ቅዱስ እንደሚተርከው ቅዱስ ዳዊት ልጁን ሶሎሞንን ጠርቶ ልጄ ሆይ ሰው ሁን “ነው ያለው፡፡
> “ሰው ሁን?” ፍራኦል ጥያቄው ከአፏ አመለጣት፡፡
> አዎ “ሰው ሁን” አለው፡፡ ሶሎሞን በዚያ ሰዓት ሰው አልነበረም ነበር? ለዚያውም የእስራኤል ንጉስ ፤እግዚያብሄር እንደልቤ ያለው የዳዊት ልጅ ነበር፡፡ ታዲያ ለምን ልጁን ጠርቶ ሰው ሁን አለው? ሶሎሞን ሰው ለመሆን ምን ነበር የጎደለው አየሽ ርግቤ ሰው መሆን ማለት ምን የሚርቅ ምን የሚረቅቅ ጉዳይ እንደሆነ” (መኤኒት፤28)፡፡

ደራሲው ይህን ሃሳብ ገና ከልቦለዱ መጀመሪያ አካባቢ በንግርነት ነው ያስቀመጠው፡፡ ሃሳቡ የተገለፀው ከፎክሎር ዘሮች አንዱ በሆነው በሃገረሰባዊ እምነት አማካይነት ሲሆን ይህ ፎክሎራዊ ጉዳይ የገባውም ጭብጡን ለመንገር(ለመጠቆም) ነው፡፡ የልቦለዱ ስያሜም ሆነ የማህበረሰቡ መጠሪያ "መኤኒት" የሚል ሲሆን ትርጉሙም "ሰው" ማለት ነው፡፡ አዛውንቱ ኬላጊና እነ ጀግናው ናደው አለምሰገድና ፍራኦል ምንም በማያውቁበት ሃገር ሂደው ይህ ሁሉ መከራና ስቃይ ሲፈራረቅባቸው ምንም አይነት የስጋም ሆነ የሃይማኖት ዝምድና ሳይኖራቸው ፤ በሁለቱ መሃል የሚያስተሳስር የባህልም ሆነ የአኗኗር ርቀት ሳያግዳቸው ከዘመድም በላይ ልክ እንደወለዷቸው ልጆቻቸው ስቃያቸውን አብረው ተሰቃይተው ደስታቸውን አብረው ተደስተው እስከ መጨረሻው ድረስ የደረሱት "ሰው" በመሆናቸው ሲሆን የሰውነት ጥጉና መለኪያው ይህ ነው የሚሉት አለምሰገድና ፍራኦል ወደ ሃገራቸው ሲመለሱም መኤኒቶችን ለማስታወስ የወለዱትን ልጅ በትርጉሙ "ሰው" የሚለውን ስያሜ በመስጠት "መኤኒት" ሲሉት እናያለን፡፡ በመሆኑም ደራሲው በታሪኩ ጅማሮ አለምሰገድ ፍራኦልን "ሰው ሁኚ" እያለ ከመፅሃፍ ቅዱስ ቃል እያጣቀሰ ምክርና ተግሳፅ መስጠቱ የልቦዱን አንድ ጭብጥ ለአንባቢያንጠቆም አድርጎ ለማለፍ ረድቶታል፡፡

ሌላው ለጥናት በተመረጡት ሁለት ስራዎች ውስጥ ደራሲያኑ ባወሱት ማህበረሰብ ዘንድ የዘመኑን መንፈስ የሚገልፁ በርካታ የማህበራዊ እና የባህላዊ ደረጃ ልዩነቶች ከፎክሎር ዘርፎች መሃል በሃገረሰባዊ ልማዶች አማካይነት ሲገለፁ ተስተውለዋል፡፡

*የእምቢታ ታሪካዊ ልቦለድ ደራሲ የፎክሎር አንድ ዘርፍ የሆነውን ሃገረሰባዊ ልማድ በመጠቀም በዘመኑ የነበረውን የማህበራዊ ደረጃ ልዩነት እንዲህ ያሳየናል፡፡*

> ዘበርጋ የአባቱ ልጅ ነው፡፡ አንድ ቀን ቃል በቃል ያለኝን አስታውሳለሁ፡፡ መጀመሪያ ነፃ ውጪ ፤ነፃ ልውጣ ፤ ነፃ እንውጣ! ሰው መስለን እንታይ፡፡ በምንሰራው ቁስ እየተጠቀሙ በምንሰራው ጌጥ እየተዋቡ በምንሰራው ጦር ጠላታቸውን እያጠቁ.....እኛን ግን የማያከብሩ ፤ለሰላምታ እንኳ ከሚጸየፉን ማህበረሰብ ራሳችንን ነፃ እናውጣ፡፡ አንቺም ሰው እንጂ ዕቃ አይደለሽም፡፡ማንም የሚገዛሽ፤ማንም ገንዘብ ያለው የሚወስድሽ አደለሽም!"አለኝ ድምፁን ቀንሶ፡፡ "ቸራዎች" ማለትም ጨዋ ሰዎች ይህን ሲናገር ከሰሙት አካባቢያቸውን ለቅቆ እንዲሄድ የሚያስገድዱት ይመስል፡፡ እንዲህ ሲለኝ ልቤ መታ፡፤ ደነገጥኩ፡፡ አሳዳሪዬን ወርድወትን የሰደበ መሰለኝ፡፡ ደግሞም ከዚህ ቀደም ራሱን እንዲህ የሚገልጽ ሰው አላጋጠመኝም፡፡ የነበረን ነገር ልክ አይደለም ማለት ልክ ነው?!

“ዘበርጋ!”

“እመት!” ስጠራው እመት ነው የሚለኝ እመቤቱ የሆንኩ ይመስል፡፡

ወርድወትን አልወደድካትም?

ላለመውደድ ምን ምክንያት አለኝ? ሁላችንም -አንቺም ሆንሽ እኔ -

ፉጋ ተብለን፤ ባሪያ ተብለን ፤ ቀጥቃጭ- ነፉረ ተብለን ፤ ተንቀን የተገፉን

ሁሉ እሷን በልባችን አርግዘን ሃሳቧን አምጠን መውለድ አለብን፤ነፃ

እንድንወጣ፡፡ ብቻዋን ናት...” (እምቢታ፤111) (አፅንኦት የራሴ)፡፡

ከላይ ካለው ሃሳብ የምንረዳው በዘመኑ ቀጥቃጭ ተብለው የሚገለሉ ፤የተገፉና የተናቁ ግለሰቦች እንደነበሩ ነው፡፡ ማህበረሰቡ እነዚህን ግለሰቦች በባሪያነት መንፈስ ተቀብሎ ከሰው እንዳልተፈጠሩ ሁሉ ያለ ምንም ክፍያ እነሱ በሚሰሯቸው ባህላዊ የእደ ጥበብ ስራዎች እያጌጠና ጠላቱንም እየመከተ ለነሱ ክብር ያለመስጠት በአጠቃላይ ሰው ሆነው ተፈጥረው እንደ ሰው የማይቆጠሩበት ዘመን እንደነበረ ለመረዳት ችለናል፡፡ እነዚህ ክስተቶች ደግሞ ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ባሉ የማህበረሰቡ አካላት  ልቦና ውስጥ የሚፈጥሩት ተፅዕኖ ቀላል የሚባል አይሆንም፡፡ ይህንንም ለማስረዳት ፎክሎራዊ ጉዳዩ ትልቅ ፋይዳ አበርክቷል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በነዚህ በሚናቁት ግለሰቦችና በተከበሩት መካከል እንዲሁም በምሬት ወቅት ሁለቱንም በፈጠረው አምላክና በሰዎቹ መካከል ግጭቶች እንዲፈጠሩ ምክንያት ሆኗል፡፡

*በመኤኒት* ልቦለድ ውስጥም በተመሳሳይ መልኩ እነዚህ ሃገረሰባዊ ልማዶች በዘመናቸው በማህበረሰቡ ዘንድ የፈጠሩትን የደረጃ ልዩነት እንዲህ መመልከት ይቻላል፡፡

> ከመንገዱ ዳር ከፈረሰው ቤት ግድግዳ ስር አይኖቻቸው ብቻ ቁልጭ ቁልጭ የሚል በቁስል የተመቱ ፤ፊታቸው ከአቧራ ጋር የተቀላቀለ፤ ፀጉራቸው ዘይት ያጨማለቀው የሚመስል ግን ከፍተኛ ፍርሃትና ድንጋጤ ከአይኖቻቸው ውስጥ የሚታይ ልጆች ተቀምጠዋል፡፡ ልጆቹ ስለህይወት ግድ ያላቸው አይመስሉም፡፡ በአካባቢያቸው የሚደረገው የአነስተኛ የጉሊት ልውውጥም ይሁን ወጪና ወራጁ ቁባቸው አልነበረም፡፡ እነሱ የሚሆነውን ሁሉ አያዩትም፡፡ ማህበረሰቡም እነሱን አያይም፡፡ ከህይወት ባህር ተወርውረው የተጣሉ አሶች ናቸው፡፡ ከማህበረሰቡ የተገለሉ ፍጡራን ናቸው፡፡ እነሱ የሚጥል በሽታ ስላለባቸውና *በመኤኒት* ብሄረሰብ እምነት ደግሞ ይሄ በሽታ የክፉና የእርግማን ምልክት በመሆኑ የተጣሉ ልጆች ናቸው (መኤኒት፤81-82)(አፅንኦት የራሴ)፡፡

በመኤኒት ማህበረሰብ ዘንድ በተለያዩ ምክንያቶች ሁለት አይነት የተገለሉና የተገፉ ሰዎች እንዳሉ በመፅሃፉ ውስጥ ሰፍሮ እናገኘዋለን አንደኛዎቹ ከላይ እንደተረዳነው ጤና በማጣታቸው ብቻ ከማህበረሰቡ ተገለው የሚኖሩና አይደለም ማህበረሰቡ የወለዷቸው እናቶች እንኳ የኔ የማይሏቸው፤ከቤት አውጥተው ራቅ ወዳለ ስፍራ እንዲጥሏቸው የሚደረግበትና ስለነሱ ማውራት በራሱ እንደ ሃጢያት የሚወሰድበት ሁኔታ መኖሩን ነው፡፡ በሌላ መልኩ ደግሞ ጤነኛም ሆነው በሚሰሩት ስራ ብቻ ከማህበረሰቡ ተገለው የሚኖሩ ጎሳዎች እንዳሉም ቀጥሎ ከቀረበው ፅሁፍ እንዲህ እንረዳለን፡፡

> በግብርና ነው የምትተዳደሩት እንዴ?አለ አለም ሰገድ ልቡ ሌላ እያሰበ ፡፡
>
> "አዎ እናርሳለን ፤ከዚያ ውጭም ሞያተኞች ነን፡፡"
>
> ምን ምን ትሰራላችሁ? የአለምሰገድ አይኖች እሳት ማንደጃው ጋር ተወረወሩ፡፡ እደጥበብ እንሰራለን፡፡ ***በእኛ አካባቢ የኛ ያልሆኑ አንዳንድ ሰዎች ቢንቁንም ቢያዋላሉንም መተዳደሪያችን አልተውንም፡፡*** ፈገግ አለ ሰውየው፡፡ የአዛውንቱ ልጅም በመኤኒት ብሄረሰብ ውስጥ የተለዩ ጎሳዎች መኖራቸውንና እነዚህም ልዩ ጎሳዎችም ***ዝቅ ተደርገው ሲቆጠሩ "ፋቂዎች ፣ ቀጥቃጮች"*** እየተባሉ ***ይጠሉና ይናቁ እንደነበረና*** ሌላው ማህበረሰብ ከነሱ ጋር እንደማይጋባም ጭምር ተረከለት (መኤኒት፤194)(አፅንኦት የራሴ)፡፡

ምንም እኳን አሁን አሁን ይህ አይነቱ ተግባር የማህበረሰቡ ግንዛቤ በሰፋ ቁጥር እየቀነሰ እንደመጣ የሚነገር ቢሆንም በዘመኑ ግን ማህበረሰቡ ሲወርድ ሲዋረድ ያመጣው ልማድና አመለካከት የደረጃ ልዩነት መፍጠሩ ዝቅ ተደርገው በሚታዩ ጎሳዎች ላይ የሚያስከትለው ሥነልቦናዊ ጉዳት ቀላል የሚባል አይሆንም፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ደራሲያኑ እነዚህን ልማዶች በስራዎቻቸውውስጥ ማካተታቸው ልማዶቹ "የእኛ" እና "የእኛ" ያልሆኑ በሚባሉ ሰዎች መካከል የአመለካከት ግጭቶች እንዲፈጠሩ ብሎም በእርግማን ምክንያት በሚገለሉት ሰዎችና በማህበረሰቡ መካከልም እንደዚሁ ግጭቶች እንዲፈጠሩ ምክንያት በመሆን አገልግሏቸዋል፡፡

ፎክሎራዊ ጉዳዮች የበቀሉበትን ዘመንና ቦታ ባህላዊ አስተሳሰብና ድርጊት ያንጸባርቃሉ፡፡ በተለይ ለጥናት የተመረጡት ስራዎች ውስጥ በስፋት የሚገኙት በዘመኑ የነበሩ በወንድና በሴት መሃል ያለ ከፍተኛ የሆነ የባህላዊ ደረጃ ልዩነቶች ናቸው፡፡ ከነዚህም መካከል *በእምቢታ* ታሪካዊ ልቦለድ ውስጥ ለአብነት ያክል "አንቂትን" ፤ *ከመኤኒት* ደግሞ "አሻን" ለማሳያነት እንመለከታለን፡፡

ይህ ፅሁፍ የተጻፈበት ዘመን አጠቃላይ መንፈሱ የጉራጌ ባህል ለወንዶች እጅግ ያደላ መሆኑን ቀደም ብለን ከልቦለዶቹ በተመዘዙ ማስረጃች ተመልክተናል፡፡ በተቃራኒው በዘመኑ ሴቷ በብዙ ጎኖች እንደምትበደልና በደሏንም የሚሰማ አካል እንዳልነበረ የቃቄ ወርድወት ምስክር ነች፡፡ ቀጣዩን ከልቦለዱ የተቀነጨበና በወርድወትና በማህበረሰቡ እንዲሁም በወርድወትና በባህሉ መካከል የተፈጠረን ግጭት ለማባባስ ደራሲያኑ ሃገረሰባዊ ልማድን እንዴት እንደተገለገለበት እንመልከት፡፡

> እናንተም እኔም እንደምናውቀው አንቂት የሴት ልጅ እዳ ነው፡፡ ትዳር ላይ የሴት ልጅ እዳ ብዙ ነው፡፡ በባህላችን መሰረት እሱ እሷን የመፍታት መብት አለው፡፡ ከፈታት በኋላ የፈለገችውን ሰው እንዳታገባ የማድረግ ስልጣን ግን የለውም፡፡ እንዴት ነው ሊኖረው የሚችለው? ባህላችን ግን ይሄንን ይፈቅድለታል፡፡ የፈታትን ሴት አልፈልግሽም ውጪልኝ ያላትን ሴት አብረው በጋር ካፈሩት ንብረት ምንም እንዳይደርሳት የፈረዱባትን ሴት እኔ ብፈታሽም እንቶኔ ግን እንዲያገባሽ አልፈልግም አልፈቅድልሽም ብሎ ማለት ምንድነው?... እምቢታ (37-38)፡፡ እኛ ሴቶች ስንት የሚነድና የሚንቀለቀል ነገር ይዘን ነው የምንዞረው፡፡ እኔ አሁን አያርገውና ባሌ ቢሞት ምንድ ነው የሚደረገው? በቁም እያለ የተበደልኩት ሳያንስ ከሞተ በኋላም ሃዘኑ ይጸናብኛል፡፡ ልቅሶ መነሳቱን፤ የሃዘን ጊዜ ማብቃቱ ለማሳየት ያው የምታውቁት ነገር ነው ሴራ ይዘጋጃል፤ የሽክላ ገበቴ፡፡ በገበቴ ውሃ ይሞላና ውሃው በወተት ይበረዛል፡፡ ይህ ከሆነ በኋላ ልቅሶ ሊደርሱኝ የመጡ ወደ ገበቴው ይጠጋሉ፡፡ የቅርብ ዘመዴ ወይም ጎረቤቴ በውሃ መቅጃ በወተት ከተበረዘው እየቀነሰች በለቀስተኛው ተረከዝ ላይ ከረጨች በኋላ አይደለም ወይ የመጨረሻው የመረረ ለቅሶ የሚደረገው?! ባሌእኔ ብሞትበት ከዚህ ቀን በኋላ የኔ ነገር ያበቃለታል፡፡ አለሁ እንጂ እኔ እሱ ቀድሞኝ ከሞተ በኋላ ሁለትና ሶስት ዓመት በሃዘን ተቆራምጄ ፤ራሴን በመብል ቀጥቼ፤ከመዋብና ከመኳኳል ተቆጥቤ፤ ራሴን እንድጎዳ ባህሉ ያሰረኝ ሰውነቴ እንዲከሳና ፊቴ እንዲገረጣ ተብሎ አይደል አመድ እንዲቦንብኝ ምድጃ ስር እንድተኛ የሚደረገው? በመስቀል ቀን እንኳን ባሌ ሞቶ፤ሁለት ሶስት አመት ሳይቆጥር ክትፎ መብላት አልችል! አምሮኝ ብጎርስ እንኳ ባሌን ገፍቼ እንደገደልኩ አይደል የሚቆጠረው?!...ነቀፌታውንስ በምን አቅሜ እችለዋለው? እኔ ብሞት ግን እሱ ይሄ ሁሉ አይመለከተውም፡፡እንደኔ አይጎሳቆልም፡፡ ራሱን ቢጠብቅ ነውረኛ ብሎ የሚዘልፈው የለም፡፡ ተዝካሬን ካወጣ በኋላ እኔ ሞቼ ወር ወይ ሁለት ወር ሳይቆይ ሌላ ይታጭለታል፡፡ ራሱን አይቀጣም! ለምን? ቆይ በስንቱ እንጎዳ?...የአንቂት ህግ ልክ አይደለም ጨቁኖናል፡፡ ደፍጥጦናል፡፡ የፍች ጥያቄ ማቅረብ ለኛ ያልተፈቀደ ሆኗል፡፡ እነሱ ሁለት ሶስት እያገቡ ፤ እኛ በአንድ ወንድ ብቻ የምንወሰንበት ምክንያት ምንድነው? እነሱ በየጉዳዮቻቸው የሚመክሩበት ቋሚ መሰብሰቢያ ቦታ ኖሯቸው እኛ ግን ከጓዳ እንዳንወጣ የምንገደድበት ምክንያት ምንድነው? ወላጆቻችን ለወንድሞቻችን ከከብቶቻቸው ቆጥረው ከመሬቶቻቸው ቀንሰው ሲያወርሱ እኛ ግን ባዶ እጃችንን አጨብጭበን

> እንድንገባ፤ የወንድ እጅ ጠባቂ እንድንሆን የሚፈረድብን ለምንድን ነው?!...(እምቢታ፤ከ88-91) (አፅንኦት የራሴ)።

ከላይ የተመለከትናቸው ከልቦለዱ ከተለያዩ ገፆች የተቀነጫጨቡና የሃሳብ ተመሳስሎ ያላቸውን ሲሆን የልቦለዱ አብይና መሰረታዊ ጉዳይ ናቸው፡፡ ልቦለዱ እንዲፃፍ ምክንያት የሆነውም ይህ ነው፡፡ ወርድወትን እየጠዘጠዘ አላስቀምጥ ያላትና እብድ፤የተረገመች ባህሏን የምትጥስና የማታከብር፤ እምቢተኛ ተደርጋም እንድትታይ ያደረጓት እነዚሁ መሰረታዊ ጉዳዮች ናቸው፡፡ የልቦለዱ ጭብጥም የሚያጠነጥነው በዚሁ ዙሪያ ነው፡፡ በዘመኑ ማለትም ከዛሬ 150 ዓመት በፊት በጉራጌ ባህል ዘንድ ይህ ነበር የተከሰተው ይህ ነበር የሆነው፡፡ በዘመኑ የነበሩት ሰዎች ለባህላቸው የሚገዙና ባህላቸው ከፈቀደውውጭ ቢያፈነግጡ ፈጣሪ ትልቅ መአት እንደሚያወርድ የሚያምኑ እንደነበሩ ለመረዳት ችለናል፡፡ ሌላው በተለይ በወንድ ልጅና በሴት ልጅ መሃል ከፍተኛ የሆነ የባህላዊ ደረጃ ልዩነቶች እንዳለም ለመረዳት ይቻላል፡፡ የጉራጌዎች ባህል በርካታ ሁኔታዎችን ለወንዶች ምቹ እንዲሆኑ ያደረገ፤ ወንድ ሆኖ መፈጠር እንደ ትልቅ ፀጋር የሚቆጠርበት በተቃራኒው ባህሉ ሴት ልጅን ከበርካታ ሁኔታዎች የገደበና የከለከለበት ዘመን እንደነበረ እንድንረዳ ከማድረጉ ረገድ ከላይ ከተለያዩ ገፆች ወንድነትንና ሴትነትን በማነፃፀር ለማሳያነት የተወሰዱት ሃገረሰባዊ እምነቶች ምስክር ናቸው፡፡

*በመኤኒት* ልቦለድ ውስጥም በተመሳሳይ መልኩ የፎክሎር ዘርፍ የሆኑት የሃገረሰባዊ እምነት ምድቦች የባህላዊ ደረጃ ልዩነት ማሳያ በመሆን ይገኛሉ፡፡ ከነዚህም ውስጥ የ"አሻ" ስርአተ ክዋኔ ዋነኛው ነው፡፡ "አሻ" ልክ እንደ "አንቂት" ሁሉ በሴት ልጅ ላይ ብቻ የተጣለ ባህላዊ ቅጣት ነው፡፡ አሻ ሴት ልጅን የሚያስር የሚጎዳና ያለፍላጎቷ ህይወቷን እርሷ ሳትሆን ሌሎች እንዲወስኑላት የሚፈቅድ በተቃራኒው ደግሞ ወንድ ልጅን ተጠቃሚ የሚያደርግ ከፍተኛ የባህላዊ ደረጃ ልዩነት የሚንፀባረቅበት የመኤኒቶች ባህል ነው፡፡ አሻ ማለት በመኤኒት ባህል አንድ ሰው በሰው እጅ ህይወቱ ካለፈ የገዳዩ ቤተሰብ ከሟች ቤተሰብ ጋርእርቅ ለማውረድ ሲባል በአሻ ክፍያነት የገዳይ እህት የምትሰጥበት ሂደት ሲሆን ይህ የብሄረሰቡ የኖረ ልማድ ነው፡፡ በካሳነት ከሰባት ከብቶች ጋር የምትሰጠው ልጃገረድ አሁን አሁን ግን የሰብዓዊ መብት ይከበር የሚሉ አካላት መበራከት ሴት ልጅ እየታነቀች ለማትፈልገው ሰው በአሻነት መከፈል እየቀነሰ እንደመጣና በልጃገረዷ ምትክም 7 ከብቶች በካሳነት ደግሞ 7 ከብቶችን በድምሩ 14 ከብቶችን የመስጠት ጅማሬዎች እንዳሉም ከዚሁ ልቦለድ ለማወቅ ተችሏል፡፡ ይሁንና ይህ ባህል በመኤኒቶች ዘንድ በሆነ

ዘመን ይከሰት የነበረ እውነት ሲሆን በሴቶች ላይም ከፍተኛ አሉታዊ ተፅዕኖንም ይፈጥር እንደነበር ለማወቅ ይቻላል፡፡ የአሻ ባህላዊ ስርዓት በማህበረሰቡ ዘንድ በዘመኑ በወንዶችና በሴቶች መካከል የነበረውን ከፍተኛ የሆነ ልዩነት የሚያሳይ መሆኑን ከልቦለዱ በተቀነጨበ ጽሁፍ እንዲህ መመልከት ይቻላል፡፡

"ማነው ያመጣኝ?" አለቻት ፍራኦል አብራት የነበረችውን ሴት፡፡

"ባሌ ባሌ ነው ያመጣህ" አለች በብዙ ፈገግዋ እንደታጀበች፡፡

"ባሌ?" ፍራኦል አይኖቿ ተጎለጎሉ፡፡

"የአንተ ወንድም ሰው ገደለ፡፡ አንተ አሻ ተከፈልክ፤ የኔ ባል አንተን አግብቶ መጣ፡፡"

ፍራኦል የአሻው ስም ሲነሳ ነገሩ ሁሉ ተገለጠላት፡፡ እያንዳንዱ ትዕይንት፣ እያንዳንዱ ስቃይ ወለል ብሎ ተመልሶ መጣባት፡፡ የዓለምሰገድ በዚያው ሄዶ መቅረት፤ለአሻ ተሰጥታ የሆነው ሁሉ፤በፈረስ ተጭና ስትጮህ እየተቆነጠጠችና እየተገረፈች ረጂምና አታካች መንገድ ተጉዛ እዚህ መድረሷ ታወቃት፡፡

…ዴጊያ ረዘም ላለ ጊዜ ስለ አሻ ምንነት እና በአሻ የተከፈለች ሴት ወዴትም መሄድ እንደማትችል ገለፀችላት፡፡ አንዲት ልጃገረድ በአሻ እስከተከፈለች ድረስ የሟች ቤተሰቦች እቃ ወይም ንብረት ሆና እንደምትኖር አብራራችላት፡፡ ሌላው ቀርቶ ያገባት ወንድ ወይም ባሏ ቢሞት ወይም ቢፈታት እንኳ የእሱ ወንድም በደም አጥቦ እንደሚወርሳት ነገረቻት፡፡

"ምን መውረስ? ፍራኦል ጮኸች፡፡

ዴጊያ ማስረጃ እየነቀሰች ከአካባቢው ሰዎች ስም እየጠራች በአሻ እንደተከፈሉ እና አንዱ የፈታትን ሌላኛው እያገባና በተለይ በልጅነታቸው ለአሻ የሚከፈሉ ልጆች የሚደርስባቸውን የስራ ጫና ፣ ድብደባና መደፈር ሁሉ አንድበአንድ ተረከችላት፡፡ (መኤኒት፤251-252)፡፡

በአጠቃላይ ለጥናት የተመረጡት የሁለት ስራዎች ደራሲያን በልቦለድ ስራዎቻቸው ውስጥ በርካታ ሃገረሰባዊ ልማዶችን መጠቀማቸውን ተመልክተናል፡፡ የልማዶቹ ተደጋግሞ መጠቀስ ደራሲያኑ በልቦለዳቸው ታሪክ ውስጥ ወደፊት ሊከሰት የሚችለውን ጉዳይ ለአንባቢያን በንግር ቴክኒክ መልክ ለማሳወቅና ጭብጡንም ለማመልከት ፤ የልቦለዱን ታሪክ በግጭት እያናሩና መልሰውም እያበረዱ የፅሁፉን ፍሰት ጠብቀውና ኪናዊ ውበት አላብሰው የአንባቢን ስሜት ከመቆጣጠራቸውም በላይበዘመኑ የነበረውን ባህላዊና ማህበራዊ መንፈስ ከማስተዋወቅ ብሎም የልቦለዱ ታሪክ የሚያጠነጥንበትን ዘመንና ቦታ በቀላሉ ለመግለፅም ግልጋሎት ሰጥተዋል፡፡

### 4.2.2.2 ክብረ-በዓል

ክብረ-በዓልን በተመለከተ የማህበረሰቡ ባህል፣ ሀይማኖት፣ እምነትና ማንነትን መሰረት አድርገው የሚከወኑና ማህበረሰቡም ለአንድ ለሚፈልገው ቋሚ ዓላማ ሲል በተደጋጋሚ የሚከውናቸው ክብረ በኣላት በሁለቱም ስራዎች ውስጥ የሚታዩ ሲሆን

*በእምቢታ ታሪካዊ ልቦለድ ውስጥ (አንትሮሽት) በጉራጌ መሃበረሰብ ዘንድ በእናቶች ብቻ የሚከበር በዓል ፣ (ኩርፍወን) ከፋሲካ በዓል አንድ ሳምንትቀደም ብሎ በሴቶች ብቻ የሚከበር በዓል ፣ (የንፖር) ጥር ወር በገባ በ21ኛው ቀን በወንዶች የሚከበር ክብረ በዓልና በጉራጌዎች ዘንድ ከሌሎች ክብረ በዓላት በተለየ መልኩ በድምቀት የሚከበረው የመስቀል በዓል አከባበር ስርዓት ፣የሚገኙ ሲሆን ከልቦለዱ ውስጥ ለአብነት ቀጣዮቹን እንመልከት፡፡*

> ባልና ሚስቱ ይነታረካሉ…
>
> "……ወርድወት አንቺ ብዙ ቦታ ሄደሽ ብታውቂ ኖሮ በምትናገሪው ነገር ታፍሪ ነበር፡፡ እዚህኮ ሴቶች የተሻለ ነፃነት አላችሁ፡፡ …እስኪ አስቢው የትኛው ነገድ ነው ዓመት ቆጥሮ አንትሮሽት የሚል ስም ሰጥቶ እናቶችን ብቻ ለይቶ የሚያከብር በዓል ያለው? በዚህ በአንትሮሽት በዓል እኮ ነው እናቶች በገዛ ልጆቻቸው እንደበት የሚመሰገኑት ፣ ስጦታ የሚቀበሉት፡፡ እስኪ ንገሪኝ ማነው እንዲህ የሚያደርገው? እናት ትበልጣለች ብለው ቢያምኑ አይደል አባቶቻችን በዓመት አንድ ቀን አንትሮሽት ብለው መታሰቢያ ያደረጉላችሁ?...ተሳሳትኩ?" ጠየቃት አጋርዝ…፡፡
>
> "እኔ እየጠየቅኩ ያለሁት ያጣነውን ነው፡፡ የጎደለብንን"፡፡ አለች ወርድወት
>
> አውቃለሁ ምንም አልጎደለብሽም፡፡ሙህሮችከማግባታቸው በፊት የሚያደርጉትን ሁሉ አድርገሽ ነው ያደግሽው፡፡ ኩርፍወን ተጫውተሽ የለ? ነግረሺኛልኮ ፋሲካ የሚባለውን በዓል ከመምጣቱ ሳምንት ቀደም ብሎ እና ካለፈ በኋላ የሚከበረውን ኩርፍወን ተጫውተሻል…"(እምቢታ፣70-71)፡፡

ከላይ ከቀረበው ሃሳብ እንደምንረዳው በጉራጌ ብሄረሰብ ዘንድ ባህል፣ ሀይማኖት፣ እምነትና ማንነትን መሰረት አድርገው የሚከወኑና ማህበረሰቡም ለአንድ ለሚፈልገው ቋሚ ዓላማ ሲል በተደጋጋሚ የሚከውናቸው ክብረ በኣላት እንዳሉት ነው፡፡ ደራሲው እነዚህን ክብረ በዓላት በፅሁፉ ውስጥ እንዲገኙለት የፈለገው በሁለቱ አብይ ገፀ ባህሪያት መካከል የነበረው አለመግባባት እንዲረግብ ለማድረግ ነው፡፡ ወርድወት ባህላችን ለወንዶች ብቻ ያደላል ለኛ ለሴቶች ምንም ክብር የለውም በሚል ከባሏም ከማህበረሰቡም ሆነ ከባህሉ ጋር ከፍተኛ ግጭት ውስጥ የገባች ሲሆን ባለቤቷ አጋዝ ደግሞ ይህን በማስተባበልና ከገባችበት ግጭት

እንድትወጣ ባህሉ ለሴቶችም ያለውን ክብር በየአመቱ ለሴቶች ብቻ ተብለው የሚከበሩ ክብረ በዓላትን በመጥቀስ በልመና መልክ ይነግራታል፡፡ይህም ግጭቱን ለማርገብ አገልግሏል፡፡

*በመኤኒት* ልቦለድ ውስጥም በተመሳሳይ (ኬት) ለአቅመ አዳምና ሄዋን የደረሱ ልጆች የሚያደርጉት የጥርስ መንቀል ስርዓት አንዱ ሲሆን ይህ ስርዓት በተለያዩ ዝግጂቶች እንደሚታጀብና የሚነቀለውም የወንድም ሆነ የሴቷ የፊት ጥርሳቸው እንደሆነ የጥርስ መንቀሉ ጠቀሜታ አንድም ከልጅነት ሕይወት ወደ ወጣትነት መሸጋርገራቸውን ለማመልከት ሲሆን በሌላ ጎን ደግሞ መኤኒቶች በከፍተኛ ህመም ወቅት ምግብ ለመውሰድ እንዳይቸገሩና በተነቀለው ጥርሳቸው አማካይነት ፈሳሽ የሆኑ ምግቦችን ለበሽተኛው ለመስጠት እንደሚጠቀሙና በእለቱም ትልቅ የሆነ ድግስ እንደሚደገስ በልቦለዱ ውስጥ በገፅ 122 ላይ እንዲህ ተገልፆ ይገኛል፡፡

> "ምንድነው? ሰርግ ነው?" አለ አለምሰገድ ወደ ሰዎቹ እየተመለከተ፡፡
>
> "አይ አይደለም፡፡ "የአቶ ጳንጎ ልጅ ጥርስ የምታወልቅበት ቀን ነው፡፡" አለ አስተርጓሚው፡፡
>
> "ጥርስ ማውለቅ ማለት?" ጠየቀ ዓለምሰገድ፡፡
>
> "የጥርስ ማውለቅ ባህል አለን እኮ እኛ" አለና በኩራት ፈገግ አለ፡፡ በፈገግታውውስጥ ደግሞ ከፊት ጥርሶቹ ሁለቱ አለመኖራውን የዚያን ሰዓት ልብ አለ አለምሰገድ፡፡ በዚያው ሰዓት ካገኛቸው አብዛኞቹ ሰዎች ከፊት ጥርሶቻቸው ሁለቱ አለመኖራውን በሚገባ አስተዋለ፡፡
>
> በኛ በመኤኒቶች ባህል የቆየ ከሚባሉ ልማዶች አንዱ ጥርስ የማውለቅ ልማድ ነው፡፡አንድ ወንድ እድሜው ለአቅመ አዳም ወይም አንድ ሴት ለአቅመ ሄዋን መድረሷን የምታበስርበት መንገድ ነው ጥርስ የማውለቅ ስነ-ስርዓት ማለት፡፡
>
> አንድ ወጣት ለአቅመ አዳም ሲደርስ ቤተሰቦቹ ድግስ ያዘጋጃሉ፡፡ በእለቱ የሚበላው ለየት ያለ የእሸት በቆሎ ገንፎ እና ቦርዴ ይዘጋጃል፡፡ ከእሸት በቆሎ የሚዘጋርጀው" ባዕሣ" የሚባል ዳቦ ሲሆን ይህም የልጆቹን ከለጋነት ወደ ወጣትነት መሸጋገር ያመለክታል፡፡ እንዲሁም "ቃንሪን" የተሰኘ ባህላዊ ምግብ ይቀርባል፡፡የመንደሩ ወጣቶችም"የረት" የተባለ ጭፈራ ይጨፍራሉ፡፡
>
> የጥርስ ማውለቅ ሌላው ምክንያት ደግሞ አንድ ሰው ህመም ባጋጠመውጊዜና ሰኣት እህል በስርዓቱ አይመገብም፡፡ ምግብ የማይወስድ በሽተኛ ደግሞ እጣው ሞት ነው፡፡ እኛ በዚህ ጊዜ …" ንግግሩን ገታ አድርጎ በመኤኒትኛ አንድ ወጣትን የሆነ ነገር አነጋገረው፡፡ልጁም እራሱን በአዎንታ በመነቅነቅ

ለጥያቄው መልስ ሰጠው፡፡ አስተርጓሚውም የልጁን ምላሽ ከሰማ በኋላ ወደ ትረካው በመግባት "ሰው በሚታመምበት ጊዜ በነዚህ ቀዳዳዎች አማካይነት በቀሰም በማድረግ ወተትና ማር እንዲወስድ እናደርግበታለን አለው (መኤኒት፤122-123)፡፡

የልቦለዱ ደራሲ በዚህ የሃገረሰባዊ ልማድ በሆነ በክብረ በዓል በተገለፀ ቅንጫቢ ፅሁፍ የልቦለዱን ትልም እንዴት እንዳዋቀረ እንገነዘባለን፡፡ ጥርስ ማውለቁ ውጤት ሲሆን ምክንያቱ ደግሞ ለአቅመ አዳምና ሄዋን መደረሱ ነው፡፡ ሌላው ጥርስ ማውለቁ ምክንያት ሲሆን ውጤቱ ደግሞ በህመም ወቅት ፈሳሽ የሆኑ ምግቦችን ለበሽተኛው በመስጠት ብርታት መስጠቱ ይሆናል፡፡ በተጨማሪም በእለቱ ለከበራው ተብሎ የሚዘጋርጀው ምግብ ምክንያቱ እለቱን ለማድመቅ ሲሆን ውጤቱ ግን ትዕምርታዊነት ያለው ሆኖ የእድሜ ሽግግሩን ለመግለፅ ነው፡፡ በአጠቃላይ የልቦለዱ የምክንያትና ውጤት ፎክሎራዊ በሆኑ ጉዳዮች እየተሰናሰሉ ቀርበውበታል፡፡

(አሻ) የባህላዊ እርቅ ስርዓት ክዋኔ በተመለከተ በልቦለዱ ውስጥ በስፋት የተዳሰሰ ሲሆን ይህ ስርዓተ ከበራ ሲካሄድ በርካታ ባህላዊ ዝግጅቶች እንደሚደረጉና በመኤኒት ብሄረሰብ ባህላዊ የእርቅ ሥነ-ስርዓት የሚፈጸምበት የራሱ የሆነ ህግና ስርዓት እንዲሁም የተለየ ቦታ ያለው ሲሆን ይህንን ስርዓተ ከበራ ለማካሄድ የሚደረጉት አጠቃላይ ሁኔታዎች ምን ለምን ተደረገ? ብለን ስንጠይቅ ጥቂያቸውም መልሳቸውም በአብሮነት እየተሰናሰሉ ሲመጡ ይስተዋላል፡፡ በእለቱም በከፍተኛ ወጪ የሚዘጋጁ ምግብና መጠጦች ፤በዳይና ተበዳይ ለእርቁ መስማማታቸውንየሚያረጋርግጥ ለሚች መቀበሪያ የሚሰጠው ኮርማ፤ከሁለቱም ወገኖች የተውጣጡ ሽማግሌዎች የሚያነቡት አንጀት፡በሚችና በገዳይ ወገኖች መሃል የሚደረገው የአንጀት መጓተት ስርዓት በሙሉ አንዳች ትርጉም ያላቸው ከመሆናቸው በተጨማሪ የልቦለዱን ምክንያትና ውጤት እያዋቀሩ የመጡ ናቸው፡፡ የአሻ ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት ለማህበረሰቡ ትልቅ ፋይዳ ያለውና በተለያየ መልኩ ግጭትን እንደሚያስወግድ የደም ብቀላ ስርአትንም እንደሚያጠፋና በአሻ የተሰጠች ሴት ሂዳ ልጅ በመውለድ በሚወለደውም ልጅሚች ይረሳል፤ይካሳልም፡፡ልጁ ከተወለደ በኋላ በገዳይና በሚች ቤተሰብ መሀል ያለ ደም ይደርቃል ተብሎ የሚታመንበት መሆኑ በልቦለዱ ታሪክ ውስጥ በስፋት ተጠቅሷል፡፡እነዚህ ስርዓተ ክዋኔዎች ደግሞ የልቦለዱን የምክንያና ውጤት ትስስር እየጠበቁና አካሄዱን እያሳመሩ ሲመጡ ተስተውለዋል፡፡

በአጠቃላይ በሁለቱም ልቦለዶች ውስጥ የተጠቀሱትና የሃገረሰባዊ ልማድ ምድብ የሆኑ የክብረ በዓላት ብንመለከት በተለይ ከበራዎቹ ደራሲያኑ የልቦለዶቻቸውን ግጭት ከማርገብ አልፈው አብዛኛውን የፅሁፉን ትልም ያዋቀሩባቸው ፎክሎራዊ በሆኑ ጉዳዮች ነው፡፡ እነዚህ ፎክሎራዊ ጉዳዮች አንድ ጊዜ ምክንያት በሌላ ጊዜ ደግሞ ውጤት አንዳንዴ ምክንያትም ውጤትም በመሆን የፅሁፉን ፍሰት እየጠበቁና ልብ እየሰቀሉ ከጅማሬው እስከ ፍፃሜው አብረው ይጓዛሉ፡፡ የአንድ ልቦለድ ትልም መሰረቱ ደግሞ አቀንቃኙ ገጸባህሪ ነው፡፡ እነዚህ አብይ(አቀንቃኝ) የምንላቸው ገጸ-ባህርያት የሚፈፅሟቸው ድጊቶች፤የሚገቡባቸውን አጠቃላይ ሁነቶች፤ ስብዕናቸውንና ሥነ-ልቦናዊ መልካቸውን በማየት ትልም እንደሚዋቀር ዘሪሁን(159) ያስረዱናል፡፡ በመሆኑም የሁለቱንም ልቦለዶች ማለትም የእምቢታ ታሪካዊ ልቦለድ የዋና ገፅ ባህሪ የወርድወትን የመኤኒት ልቦለዷን ፍራኦል አጠቃላይ ድርጊት የሚገጥሟቸውን የህይወት ፈተናዎች እንዲሁም ከገቡበት ፈተና ለመውጣት በሚደረጉ ስርዓተ ከበራዎችና የሚከወኑ ድርቶቹን በሙሉ ብናጤን የልቦለዱን ትልም ለማዋቀርና ልቦለዱ ተጠየቃዊነቱን ጠብቆ እንዲፈስና ፅሁፉ ሳቢ እንዲሆን ከማድረግ አንፃር አስተዋፅኦ ሲያበረክቱ ይስተዋላሉ ፡፡

### 4.2.2.3 ሃገረሰባዊ ስያሜዎች

ሃገረሰባዊ ስያሜዎችን በተመለከተ በሁለቱም ለጥናት በተመረጡ ልቦለዶች ውስጥ የሚገኙ ሲሆን

በእምቢታ ታሪካዊ ልቦለድውስጥ የሚገኙት ሃገረሰባዊ ስያሜዎች በማህበረሰቡ ዘንድ በትክክለኛነታቸው የሚታመንባቸውና ለግለሰቦቹ ወይም ለነሳዎቹ በሚሰጠው ስያሜ ከማህበረሰቡ ጋር በአብሮነት ረጅም ዘመናትን ያስቆጠረ ከመሆኑም በተጨማሪ የግለሰቦች የደረጃ ልዩነት የሚፈጠርባቸውና ማንነታቸውን እንድንረዳ የሚያደርጉ ሲሆን አንዱን ከሌላው ለመለየት የሚሰየሙ መሆናቸውንና ትላልቅ ሰዎች ፣ ጀግኖች ፣ በለጋስነታቸው የሚታወቁ ግለሰቦች፤ ባለሙያ ለሆኑ ሴቶችና በሃብት ንብረታቸው አንቱ ለተባሉ የማህበረሰቡ አባላት የሚሰጡ ስያሜዎች እንዳሉ በልቦለዱ በተለያዩ ገፆች ላይ ተገልጿል፡፡

በዚሁ ታሪካዊ ልቦለድ ውስጥ ከፎክሎር ዘውጎች መካከል የሃገረሰባዊ ልማድ ምድብ የሆነው ሃገረሰባዊ ስያሜዎች በታሪካዊ ልቦለዱ የተቀረፁትን ገፀ-ባሕርያት ማንነት ከመግለፅ ረገድ ጉልህ ሚና አበርክተዋል፡፡ በታሪኩ ውስጥ የተቀረፁት ገፀ ባሕርያት ስንመለከት አብዛኞቹ

የሚጠሩበት የማእረግ ስሞች አሏቸው፡፡ ከነዚህ ስሞች ተነስተን ደራሲው እገሌ እንዲህ ነው እንዲያ ነው እያለ ከእያንዳንዳቸው ገፀባህሪያን ጋር ሳያስተዋውቀን ማህበረሰቡ የተስማማባቸውን ባህላዊ የማዕረግ ስሞችን ብቻ በማየት ገፀባሕሪው ጀግና ይሁን ፈሪ፤ ደግ ይሁን ንፉግ ፤ባለሙያ ትሁን ሌላ አጠቃላይ በልቦለድ አለሙ ውስጥ የሚንቀሳቀሱትን ገፀ-ባሕርያት ማንነት በውል እንድንረዳ ያግዛል፡፡

ጉራጌዎች ከጥንት ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ባህላዊ የማእረግ ስሞች አሏቸው፡፡ እነዚህ የማእረግ ስሞች በሁለት መልኩ እንደሚገኙ ይነገራል፡፡ አንደኛው ከቤተሰብ በውርስ የሚሰጥ ስያሜ ሲሆን ሁለተኛው ማህበረሰቡ ለአንድ ሰው የሠራውን ትልቅ ስራ፣ ባህሪውን፣ የኑሮ ደረጃውንና ማንነቱን ወዘተ አይቶና መዝኖ የሚሰጠው መሆኑ ከታሪካዊ ልቦለዱ ታሪክ ለማወቅ ተችሏል፡፡

ከቤተሰብ በውርስ የሚገኘው ስያሜ “አዝማች” የሚል ሲሆን ትርጉሙም “ንጉስ” እንደ ማለት ነው፡፡ ይህ ስያሜ የተሰጠው ልጅ አባት በሚሞትበት ጊዜ ከሌሎች ልጆች በተለየ ሁኔታ ንግስናውን ይረከባል[3]፡፡ ሁለተኛው የስም አወጣጥ ስርዓት ደግሞ ከላይ እንደተገለፀው በማህበረሰቡ ተቀባይነት አግኝቶ የሚሰጠው የማእረግ ስም ሲሆን ስያሜዎቹም የማህበረሰቡ ነባር እውቀቶችና ፍልስፍናዎች የሚንጸባረቁባቸው በመሆናቸው አጠቃላይ የተሰያሚው አካል ማንነትንና ምንነትን ከግምት ውስጥ ያስገባ መሆኑም በልቦለዱ ውስጥ ተነስቷል፡፡ በታሪካዊ ልቦለዱ ውስጥ ያሉትን የገፀባህሪያት ማንነት የሚያስረዱ የማዕረግ ስሞችን እንደሚከተለው እንመልከት፤-

“ዳሞ”፡- የወርድወት አባት ቃቄ በሀብታቸው ብዛትና በለጋስነታቸው የተነሳ ዳሞ የሚል ስያሜ ተሰጥቷቸዋል፡፡ ዳሞ ማለትደግሞ ብዙ ሀብት ያለውና የተከበረ እንዲሁም ለጋስ ለሆነ ሰው የሚሰጥ የማእረግ ስም ነው፡፡ ቀጣዩን ከልቦለዱ የተወሰደ ደጋፊ ሃሳብ እንመልከት፡፡

---

[3]አባት በሚሞትበት ጊዚ ከሚወለዱ ልጆች አንጋፋው ወይም የተመረጠው ንግስናውን ይቀበላል፡፡ የንጉሳውያን ዘር በመሆኑ ማሳያም እጁ ላይ የሚጠልቅ ጌጥ መሳይ ምልክት ያደርጋል፡፡ ስሙም “ ጎርዲ” ይባላል፡፡ ከዘያ ከአያት ቅድመ አያት የተወረሰውን ንግስና ሲቀበል ንጉስ ይባላል፡፡ በማህበረሰቡ ዘንድ ንጉስ ይከበራል፤ ከሌላው ማህበረሰብ በበለጠም በማህበረሰቡ ዘንድ ንጉስ ይከበራል፤ ከሌላው ማህበረሰብ በበለጠም ከበሬታይቸረዋል፡፡በተጨማሪም ንጉስ ከሆኑ በኋላም ይዘፈንላቸዋል ፡፡

> “ሰዎች በሃብታቸውና የባለብዙ ከብት ባለቤት በመሆናቸው፤ እንዲሁም ሃብታቸውን ደግሞ ለሌሎች ጥቅም በማዋላቸው “የዳሞነት” ማዕረግ ካገኙ ሰዎች ይልቅ የተመጠነ አቅም ካለው ከአጋዥ ፋርችዬ ጋር ወዳጅነት መመስረቱን ይወዱታል…”(እምቢታ፤16-17)፡፡

ዳሞ ቃቄ በመንደሩ አንቱ የተባሉ የሚከበሩ፤ የሚመርቁና የሚረግሙ የሃገር ሽማግሌም ናቸው፡፡ ይህንንም ለማሳየት ከልቦለዱ ውስጥ ቀጣዩን ቅንጫቢ እንመልከት፡-

> “አመሻሻ ላይ ደመራ ይለኮሳል ደመራውን መጀመሪያ ሽማግሌዎች ፣ ቀጥሎ ወጣቶች፣ ቀጥሎ ታዳጊዎች ይዞሩታል፡፡ ከሽማግሌዎች መካከል በእድሜ የሚተልቁና የሚከበሩት ለምሳሌ ቃቄ ዳሞ በመንደሩ ዝነኛም ናቸውና ደመራውን ይለኩሱታል፡፡…ወጣቶቹን ይመርቃሉ ልምዶቻቸውን ያካፍላሉ…”(እምቢታ፤15)፡፡

አጅየት፡- ይህ ስያሜ ለሴቶች የሚሰጥ የማእረግ ስም ሲሆን እንግዳ ተቀባይ፤ የላቀች ባለሙያ፣ለጋስና ሩህሩህ እንደ ማለት ነው፡፡ በዚህ የማዕረግ ስያሜ የምትጠራው የወርድወት እናት አሚና ስትሆን ከመፅሃፉ እንደተረዳነው አሚና በህይወት የሌለች ሴት መሆኗንና ወርድወትን የማሳደግ ሃላፊነት የአባቷና የባሪያዋ ብቻ እንደነበር ነው፡፡ ይሁንና የወርድወት እናት አሚና በህይወት ሳለች ምን አይነት ሴት እንደነበረች በማዕረግነት ከተሰጣት ስያሜ በቀላሉ ለመረዳት ይቻላል፡፡ ቀጣዩ ከልቦለዱ የተወሰደ ሃሳብ ነው፡፡

> አባትሽ የታወቁና የብዙ ከብቶች ጌታ ናቸው፤የሙህር ተወዳጅ ሰው ፡፡ “ዳሞ” የሚለውን ማዕረግ እንደ ቀልድ አይደለም ያገኙት፡፡በሃብታቸውነው፡ እናትሽም ነፍሳቸውን ይማረውና ባለሙያና መስተንግዶ አዋቂ እንዲሁም ቤታቸውን ተቆጣጣሪ ስለነበሩ “አጅየት” የተባለ የማዕረግ ስም ነበራቸው…(እምቢታ፤71)፡፡

አጋዥ፡- እጅግ ተፈሪ የሆነ ጦረኛ፣ ገና ሲያዩት የሚያስደነግጥ ትልቅ ግርማ ሞገሰ ያለው ጀግና ማለት ነው፡፡ የአጋዝነት ማእረግ የሚሰጠው ግለሰብ በድፍን ሰባት ቤት የሚከበርና የሚወደድም ጭምር ነው፡፡ ለፋርችዬ ወርድወት የተዳረችለትም ይህ ክብር ታይቶ ነው፡፡ ከታሪካዊ ልቦለዱ ተቀንጭቦ የተወሰደ ሃሳብ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

> ስሚኝ ልጄ እኔኮ ትክክል ነበርኩ “ያኔ የሚመጥንሽን አውቃለሁ ብዬ እኮ ነው ፋርችዬን ያጨሁልሽ፡፡ አጋዥ ደግሞ የዚህ ዘመን ቁጥር አንድ ላይ የሚቀመጥ የኧኸር ጦረኛ ነው፡፡ ሰባት ቤት በዚህ ዘመን ሰባት ጀግናዎችህን አሳልፈህ ይዘህ ና የሚለው ቢኖር ጨሃ የጌረሞ ፉጋንና ዑመር ፋርዳን ፣ እነሞር አጋዥ ለማዳን፣ ሙህር አኅትሽ የኤሰኪ አርብ ሸበታን፣ጉመር የኬሮ ዴርሳሞን ማምጣቱ የታወቀ ነው…(እምቢታ፤25)፡፡

ኤሰኺ አርብ ፡- የማይፈራ፣ በውጊያ ወቅት ከጦር ሜዳ የማይሸሽ ማለት ሲሆን በጦር ግንባር ወይም በሌላ ትላልቅ የዱር አራዊትን በመግደል ጀግና ሆኖ ብዙ ጠላቶችን የተዋጋም ይህ የማእረግ ስም ይሰጠዋል፡፡ ትርጉሙም "አርብ" ማለት ጦርነት ማለት ወይም ውጊያ ማለት ሲሆን "ኤሰኺ" ማለትደግሞ የማይሸሽ የማያፈገፍግ እንደ ማለት ነው፡ ፡ ኤሰኺ አርብ ፉጋ ወርድወት ትዳሯን ከፈታች በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ ቀልቧን የሳበውና የወደደችው ወንድ ሲሆን የጌረሞ ፉጋር ካሏቸው ሶስት ጀግኖች ልጆች አንደኛውነው፡፡ ኤሰኺ አርብ ፉጋ ተብሎ የሚጠራዉ በድህነቱ ሳይሆን በዚህ ማበረሰብ ዘንድ ፉጋ የክብርና የጀግንነት ስያሜ በመሆኑ ነዉ፡፡

እንግዲህ በእምቢታ ታሪካዊ ልቦለድ ውስጥ የሚገኙ የማዕረግ ስያሜዎች ለማሳያ ያህል እነዚህን ተጠቀምን እንጂ በርካታ ናቸው፡፡ ደራሲ እንዳለጌታ ከበደ እነዚህን ስያሜዎች በሥነ-ፅሁፍ ስራው ውስጥ የተጠቀመው ለአንዳች ፋይዳ ሲሆን በልቦለዱ ውስጥ የቀረፃቸው ገፀ-ባሕርያት ጋር አንባቢያን በቀላሉ እንዲተዋወቁና ገፀ-ባሕርያኑ የተቀረፁበትን መንገድ፣ በማህበረሰቡ ዘንድ ያላቸውን ቦታና አጠቃላይ ማንነታቸውን ለመግለፅ ተጠቅሞበታል፡፡

*በመኤኒት* ልቦለድ ውስጥ ደግሞ የሚሰጠው ሃገረሰባዊ ስያሜ ከላይ ካለው በተለየ መልኩ ሆኖ በገጠመኝ ነው፡፡ ለምሳሌ በልቦለዱ በገጽ 117 ላይ ፍራኦል የሚለውን የኦሮምኛ ቃል ከዘመድም በላይ የሚል ትርጓሜ ያለውን ስያሜ አዛውንቱ ኬላጊ ለልጅ ልጃቸው የሰየሙት በአጋጣሚ አለምሰገድና ፍራኦል አዛውንቱ ቤት በእንግድነት ወቅት በመጡበት ወቅት የአዛውንቱ ልጅ ሴት ልጅ ስለወለደች ይህ ደግሞ የመልካም አጋጣሚ ተምሳሌት በመሆኑ ስያሜው እንደተሰጠ የተገለፀ ሲሆን በተመሳሳይም በገፅ 116 ላይ መኤኒቶች ለየት ያለ የስም አወጣጥ ልማድ እንዳላቸውና ሴት ልጅ በተለያዩ ማህበራዊ አጋጣሚዎች ላይ ብትወልድ የሚወለደው ህጻን ከነዚያ ልዩና እንግዳዊ ከሆኑ አጋጣሚዎች ጋር የተሳሰረ ቋሚ ስሞችን እንደሚወርስ የተገለፀበትም ሁኔታ አለ፡፡ ቀጣዩን ከልቦለዱ የተቀነጨበ አስረጂ እንመልከት፡፡

> "በኛ በመኤኒቶች ዘንድ ለየት ያለ የስም አወጣጥ ልማድ አለን፡፡ድንገት ደራሽ እንግዳ በአካባቢያችን መጥቶ እያለ አንድ ሴት ብትወልድ ልጁ በእንግዳው ስም ይሰየማል፡፡"ከዚህ በተጨማሪም አንድ ሴት በተለያዩ ማህበራዊ አጋጣሚዎች ላይ ብትወልድ የሚወለደው ልጅ ከነዚያ ልዩና እንግዳዊ አጋጣሚዎች ጋር የተሳሰሩ ቋሚ ስሞችን ይወርሳል" አሉ፡፡...እናም አንዲት የመኤኒት እናት ከትልቅ ሰው ቀብር ላይ ብትወልድ ወይም ቀብሩ ተጠናቆ ወደ ቤቷ ስትመለስ ብትወልድ ህጻኑን "ሞናይ" ብላ ትሰይመዋለች፡፡ እንደ

> አጋጣሚ ሆኖ ደግሞ ሴቲቱ ከቦርዴ ቤት ወይም መንገድ ውላ ስትመለስ ብትወልድ ልጁን "ኑርጌ" ወይም "ሹሉዋ" ብላ ትጠራዋለች" አሉ፡፡… "እናም ዛሬ የእኔ ሴት ልጅ የእናንተ እግር እዚህ እንደረገጠ ሴት ልጅ ወለደች" አሉ፡
>
> "ሴት ልጅ?" ዓለምሰገድ በደስታ ተውጦ ፍራኦልን አየት፡፡ፍራኦል በተደበላለቀ ስሜት ውስጥ ሆና በግራ እጇ ጠበቅ አድርጋ ያዘችው፡፡ "በመሆኑም የልጅ ልጄ ስም ፍራኦል ሆኗል" … የስምሽ ትርጓሜ "ከዘመድም ከወገንም በላይ ማለት አይደል" አሉና አዛውንቱ ፍራኦልን ለመጨበጥ እጃቸውን ዘረጉ…(መኤኒት፤116-117)፡፡

ከዚህ ጽሁፍ የምንረዳው መኤኒቶች ለልጆቻቸው ስያሜን የሚሰጡት ከአጋጣሚዎች ጋር በተያያዘ እንደሆነ ነው፡፡ ዓለምሰገድና ፍራኦል በአጋጣሚ አዛውንቱ ቤት ሲደርሱ የአዛውንቱ ሴት ልጅ በመውለዷ አዛውንቱ የልጅ ልጃቸውን የኦሮምኛ ቃል የሆነውንና ከወገንም (ከዘመድም) በላይ የሚል ትርጉም ያለውን ፍራኦል የሚል ስያሜ ይሰጧታል፡፡ እንግዲህ የዚህ ልቦለድ ደራሲ ይህንን ሃገረሰባዊ ስያሜ በልቦለዱ ውስጥ የተገለገለው ልክ እንደ እምቢታው ደራሲ የገፀ ባህርያትን ማንነት እንድናውቅ ሳይሆን ታሪኩን በንግር ቴክኒክ ለማስኬድ ነው፡፡ በልቦለዱ ታሪክ መቋጫ ላይ አለምሰገድና ፍራኦል በመኤኒት ሰማይ ስር ያገኟቸው አዛውንት ከነ መላው ቤተሰቦቻቸው ከዘመድም ከወገንም በላይ ሆነውላቸው እናገኛለን፡፡ ይህንንም ውለታ ለመክፈልና ሁሌም ያደረጉላቸውን ለማስታወስ ወደ አዲስ አበባ ከመጡ በኋላ የሚወልዱትን ልጅ ስም መኤኒት ብለው ሲሰይሙት እናያለን፡፡ በመሆኑም ደራሲው ይህን ስያሜ በማምጣት ወደ ፊት በልቦለዱ ውስጥ ሊከሰት የታሰበውን መሰረታዊ ጉዳይ ወይም አንድ ጭብጥ ከወዲሁ ለመጠቆም ተጠቅሞበታል፡፡

### 4.2.3 ቁሳዊ ባህል

ቁሳዊ ባህልን በተመለከተ በሁለቱም ስነ-ፅሁፋዊ ስራዎች ውስጥ የተነሱ ሲሆንእነዚህ ቁሳዊ ባህሎች የማህበረሰቡን ማንነት፤እምነት፤ ፍልስፍና፤ ታሪክ ፤ ሃይማኖት ወዘተ መሰረት ያደረጉና የግለሰቦች ኢኮኖሚያዊና ባህላዊ ደረጃዎች የሚገለፁባቸውና የማህበረሰቡን የረጂም ዘመን አሻራዎችን የሚያንጸባርቁ ናቸው፡፡ ከነዚህም መካከል ባህላዊ አልባሳቶች፤ ጌጣጌጦች፤ ሃገረሰባዊ ምግብና መጠጦችና ባህላዊ ቦታዎች በሁለቱም ስራዎች ውስጥ የተገኙ ሲሆን "በእምቢታ ታሪካዊ ልቦለድ ውስጥ ደግሞ ሃገረሰባዊ ትዕምርቶች ተገኝተዋል፡

### 4.2.3.1 ባህላዊ አልባሳትና ጌጣጌጦች

ለጥናት ከተመረጡት ሁለት ስራዎች ውስጥ *በእምቢታ ታሪካዊ* ልቦለድ ውስጥ የቁሳዊ ባህል ምድብ የሆኑ ሃገረሰባዊ አልባሳትና ጌጣጌጦች ልቦለዱ የተፃፈበትን የዘመን መንፈስ (የታሪካዊ ልቦለዱን መቼት) ከማሳየት አንፃር ላቅ ያለ አስተዋፅኦ ሲያበረክት ይታያል፡፡ በተለይምአልባሳቶቹ በዘመኑ የነበሩ ኢኮኖሚያዊ ደረጃዎች የፈጠሩትን ልዩነትና እውነታዎችን ከማሳየት በተጨማሪ ጭብጥ የመሆን አጋጣሚም የሚኖራቸው ናቸው፡፡

*በእምቢታ* ታሪካዊ ልቦለድ ውስጥ ጀግና ወንዶች የሚለብሷቸው ከነብር ቆዳ የተዘጋጁ አልባሳትና ከእንጨት የተሰሩ መጫሚያዎችን እንደሆነና በተቃራኒው አገልጋዮቻቸው የሚለብሱት ከበግ ቆዳ የተዘጋጀ ልብስና ከኮባ ቅጠል የተዘጋጀ መጫሚያ እንደሆነ ሴቶች ምንም ያህል ሃብት ቢኖራቸውና የተከበሩ ቢሆኑ እንደ ወንዶች ጫማ ማድረግ እንደማይችሉ ሁሉ በልቦለዱ ውስጥ የተጠቀሰ ሲሆን ባህላዊ አልባሳቱ በዘመኑ የነበረውን ኢኮኖሚያዊ ደረጃ በመግለፅም አገልግሎት እንደሰጡ ለማወቅ ተችሏል፡፡ደራሲ የቁሳዊ ባህል አንድ ዘርፍ የሆነውን ሃገረሰባዊ አልባሳትና መጫሚያዎችን በማውሳት የልቦለዱን መቼት ከመግለጽ በተጨማሪ በዚያ ዘመን የነበረውን የኢኮኖሚ ደረጃ ልዩነቶች ለማመልከት እንዴት እንደተጠቀመበት እንመለከታለን፡፡

> ወርድወት ክብሯና ሃብቷ በሚፈቅድላት ልክ ነው የምትሽሞነሞነው፡፡ የተለፋ የነብር ቆዳ ነው ከወገቧ በታች የምታገለድመው፡፡ በቆዳው ግርጌ ዛጎሎች አሉበት ከወገብ በታች የጎፈርያም በግ ቆዳ ጣል ታደርጋለች፡፡ ጫማ አታደርግም ጫማን የሚያደርጉት ወንዶች ናቸው፡፡ ጫማውን የሚሰሩት ፉጋዎች ናቸው፣ እነዚያ የተናቁና የተጠሉት፡፡ የመስቀል ቀን ማለትም "የወኼምያ" በዓል ሲመጣ እንጨት ጠርበውና አለስልሰው መርገጫ አበጅተው፣ ቃጫ ገምደው ፣ በመርገጫው ላይ አጠላልፈው ለጌቶች ስጦታ ያበረክታሉ፣ አጋዝ እድለኛ ነውብዙ ጫማዎችአሉት...(መኤኒት፣12) (አፅንኦት የራሴ)፡፡

በታሪካዊ ልቦለዱ ውስጥ በሌላ ገፅ ላይም ይሄው የኢኮኖሚ ደረጃ ልዩነትን የሚፈጥሩ የቁሳዊ ባህል ዘርፍ እንዲህ ተገልፆ እናገኘዋለን፡፡

> አጋዥ አሽከሮቹን አስከትሎ ገባ፡፡ በነብር ቆዳ የተሰራ ሱሪ ለብሷል፡፡ የአሽከሮቹ ሱሪ ግን አጭር ነው፡፡ በበግ ቆዳ የተሰራ ሱሪ፡፡ እንደሱ በእንጨት የተበጀ ጫማ አላጠለቁም፡፡ እንቅፋት እንዳይመታቸው ያህል የሚከለክል በኮባ የተበጀ ጫማ እንጂ...(እምቢታ፣19) (አፅንኦት የራሴ)፡፡

ከላይ ከቀረቡት ሁለት ፅሁፎች እንደምንረዳው በዚያን ዘመን ማለትም ከዛሬ 150 ዓመት በፊት በጉራጌ ማህበረሰብ ዘንድ ጀግኖች፣የተከበሩና የባለሃብት ቤተሰቦች የሆኑ ወንዶች

የሚለብሷቸውና የሚጫሟቸው ጫማዎች ከነብር የሚገኝ ቆዳና ከእንጨት የተሰራ መጫሚያ ሲሆን ይህንን አይነት አለባበስ የለበሱ ወንዶች ሃብታቸው ከፍ ያለ አልያም በጀግንነታቸው በማህበረሰቡ ዘንድ የሚከበሩና የሚወደዱ መሆኑን በዚህ አለባበሳቸውም ከተራው ህዝብ እንደሚለዩና በተቃራኒው ደግሞ በዘመኑ የሚናቁና የሚጠሉ "ፋጋዎች" ተብለው የሚጠሩ በደረጃቸው እጅግ ዝቅ ያሉና እንደ ደረጃቸው የሚጫሙትም ከኮባ ቅጠል የተሰራ መጫሚያ ሲሆን ምንም እንኳ ወንድ ቢሆኑም ደሃ በመሆናቸው ብቻ የሚለብሱት የበግ ቆዳ መሆኑን ነው፡፡ እነዚህ የተናቁ ሰዎች ስራቸው በነዚህ ደረጃቸው ከፍ ባሉ ሰዎች ቤት በአገልጋይነት ያለምንም ክፍያ ከብቶችን ማገድ፣ስር እየማሱና ቅጠል እየበጠሱ ቁስለኞችን በመፈወስ ነው፡፡ በአጠቃላይ እነዚህ አልባሳቶች የልቦለዱ ታሪክ የሚያጠነጥንበትን ዘመን (መቼውን) ብሎም በዘመኑ በሁለቱ መካከል የነበረውን ከፍተኛ የሆነ ኢኮኖሚያዊ ደረጃ ልዩነቶች እንደፈጠሩ ለመግለፅ አገልግለዋል፡፡

ሃገረሰባዊ ጌጣጌጦችን በተመለከተ ዋናዋ ገፀ ባህሪ ወርድወት እንደ ሃብቷና ክብሯ መጠን ከሌሎች የምትለይባቸው ከወገቧ በታች በምታገለድመው ከቆዳ የተሰራ አልባሳት ግርጌ ላይ የተለያዩ ውብ ዛጎሎችን ጣል ጣል የተደረጉበት መሆኑ በዘመኑ እንደሷ የባለጠጋ ልጅ እንጂ ማንም ተራ (ከደሃው) ቤተሰብ የተገኘች ሴት ይህን ጌጣጌጥ ማድረግ እንደማትችል የሚጠቁም ሲሆን ደራሲው እነዚህን አልባሳትና ጌጣጌጦች በልቦለዱ ታሪክ ውስጥ በማስገባት አንባቢያን በዘመኑ ከነበረው መንፈስ ጋር እንዲተዋወቁና ፣ ያ ዘመን ምን ይመስል እንደነበረና ዛሬ ካለው ጋር በንጽጽር እንዲመለከቱት ያስችላል፡፡

### 4.2.3.2. ሃገረሰባዊ ምግብና መጠጥ

በሁለቱም ስራዎች ውስጥ የሚገኙት ሃገረሰባዊ ምግብና መጠጦች የበቀሉበትን ማህበረሰብ ባህልና እምነት መሰረት በማድረግ በአካባቢው በሚገኙ ግብዓቶች ተጠቅመው በየ እለቱ (ዘወትራዊና) በተመረጡ ቀናት የተለያዩ ክብረ በዓላትን ተመርኩዘው የሚሰሩ ናቸው ፡፡

በእምቢታ ታሪካዊ ልቦለድውስጥበጉራጌዎች ዘንድ ክትፎና ቆጮ መመገብ፣ እንዲሁም የቅቤ ቡና መጠጣት እንደመገለጫቸው ተደርጎ የሚወሰድ ሲሆን በተለያዩ ሰርዓተ ከበራዎችን ተመርኩዘው የሚዘጋርጁ ምግቦችም አሏቸው፡፡ ለሴቶች በዓል ከበራ ተብሎ ከጎመን ፣ከደቆ፣ ከቅቤና ከአይቤ የሚዘጋጀው ጣፋጭ ምግብ እንዲሁም በዋዜማው በ"ዋኽምያ" በዓል ከበራ ወቅት ከሚታረደው በሬ የሚዘጋጅ ለየት ያለ ክትፎ በዚህ ስራ

ውስጥ የተጠቀሱ ሲሆን ጉራጌዎች እነዚህን ምግቦች ለማሰናዳትም ሆነ ለመመገቢያነት የሚጠቀሙበት ቁሳቁስ የማህበረሰቡ የራሱ ውጤቶች እንደሆኑና በኮባ ቅጠል የተሰራ ሰሃንና ከቀንድ የተሰራ ማንኪያም ለዚሁ ተግባር እንደሚውል ተገልጿል፡፡ ሌላው በዚሁ ማህበረሰብ ዘንድ ከሌሎች በተለየ መልኩ ያላቸው ባህላዊ ምግብ መስከረም ወር በገባ በአስራ ስምንተኛው ቀን "እርስ ባር" በሚባል ቀን የበሬ ሻኛ በህብረት የሚበላበት ቀን መሆኑንና ምግቡም የሚበላው በባል ቤተሰቦች ቤት ወይም በባል ታላቅ ወንድም ቤት ሲሆን ይህ የበሬ ሻኛ ከዚህ ውጭ በሆነ አጋጣሚ ወደ ሴቷ ቤተሰቦች ቤት ሄዶ የመበላት አጋጣሚ ቢኖረው የወንዱ ወኔ ይጠፋል፤አቅሙን ጀግንነቱን ሁሉ ያጣል ሴቷ የበላይ ትሆናለች ወግ ባህላችንም ይጠፋል ብለው እንደሚያምኑም ጭምር በልቦለዱ በገፅ 16 ላይ ተጠቅሷል፡፡ይህ ሃገረሰባዊ ምግብ በልቦለዱ ውስጥ በወርድወትና በባሏ በአጋዥ በኩል ተከስቶ የነበረውን ግጭት እንዲካረር የበኩሉን ሚና ሲጫወት ተስተውሏል፡፡ ለአስረጂነት ቀጣዩን ከልቦለዱ ተመዞ የመጣ ጽሁፍ እንመልከት፡፡

> "ጓደኛዬ አንተም እኔም እናውቃለን ወንድ ልጅ ጎጆ ከወጣ በኋላ እንኳንስ በመስቀል በኣል ይቅርና በአዘቦት ቀንም ቢሆን ከብት ሲያርድ ሻኛውን ፤ በግ ሲያርድ ደግሞ ፍሪምባውን ለወላጆቹ ወይም ለታላላቅ ወንድሞቹ ይሰጣል፡፡ እነዚህን ብልቶች ወደ ቤተሰቦቹ ይልካል እንጂ በገዛ ቤቱ እንደማይበላቸው የታወቀ ነው አይደል?" አለ አጋዝ ፍርችዬ
>
> "ይሄ ታዲያ ምን አዲስ ነገር አለው? ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲተላለፍ የመጣ አይደለም ወይ?" አለ ጓደኛው ግራ ተጋብቶ አይኑን ከአጋዝ አይን ሳይነቅል፡፡
>
> "ነው፣ ለሚስት ወላጆች ፣ለሴት ቤተሰቦች የተላከ እንደሆነ ነው ነውሩ!"
>
> "አዎ!"
>
> አጋዝም "የኔ ሚስት የኔይቱ የቃቄ ወርድወት ግን አድርጋዋለች" አለ አንገቱን ደፍቶ፡፡
>
> ጓደኛው ቀኝ እጁን ጭንቅላቱ ላይ ጫነ፡፡ በግራ እጁ የያዘውን ብትር ጣለ፡፡
>
> "ምን?"
>
> "...ሄደች አባቷ ቤት ይዛው ሄደች ፣ያረድኩትን የበግ ፍሪምባ
>
> "ሄደች ነው የምትለኝ?
>
> "አዎን ሄደች፡፡"

"…ምን አልካት? ዝም አልካት? ልብሷን አስወልቀህ ገላዋ በሰንበር

እስኪሞላ አልገረፍካትም?"" በየትኛው ጉልበቴ? አባቴ ፍሪምባ ይወዳል ብላ ከመገበችው በኋላ ፤ ይሄው በወጣትነቴ አረጀሁ፤ልቤ ከዳኝ፤የኔ ጀግንነት ወደ ቤተሰቦቿ ሄደ፡፡ አባቷና ሁለቱ ትላልቅ ወንድሞቿ ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ዝናቸው ከፍ አለ፡፡ አቅም አጣሁ፡፡ የገዛ ሚስቴን የምቆጣጠርበት አቅም አጣሁ፡፡ይሄው በዚህ ምክንያት መጋጨት ብቻ ሆነ ስራችን ተራ ሰው ሆንኩልህ ጓደኛዬ…"

ጓደኛው በጣም ተናደደ "አንተ ነህ ያባለግካት! አንተ ነህ ያጨማለቅካት! እውነትም ጉድ ሆነሃል ጓዴ! ተዋርደሃል! እኔም የሆንከው ነገር እንዳለ ጠርጥሬ ነበር፡፡ በቅርቡ ባደረግነው የጦርነት ዘመቻ ለጥቂት እኮ ነው የተረፍከው፡፡ በሃድያዎች እጅ ብትገባ ኖሮ ምን ይውጥህ ነበር?" ብሎ ጠየቀው…(እምቢ.ታ፤58)፡፡

ከላይ ከቀረበው ሃሳብ መረዳት እንደሚቻለው ሃገረሰባዊ ምግብ የሆነውና በዓመት አንድ ጊዜ በክብር የሚበላው የበግ ፍሪምባ ለባልና ሚስቱ ፀብ ማክረሪያ ሲሆን ነው፡፡ አጋዝ ከወርድወት ጋርግጭት ውስጥ የገባበት አንዱ ምክንያት የዚህ ፍሪምባ ባህሉና ልማዱ ከሚፈቅደውውጭበሴቷ ወገኖች ቤት ሄዶ መበላቱ እንደሆነ አምኖ ተቀብሏል፡፡ በመሆኑም ደራሲው ይህንን ትእምርታዊ ፍቺ ያለውን ሃገረሰባዊ ምግብ በማምጣት በልቦለዱ ውስጥ ተከስቶ የነበረውን ግጭት ይበልጥ እንዲባባስ ሲያደርገው ይስተዋላል፡፡

*በመኤኒት* ልቦለድ ውስጥ ደግሞ በተቃራኒው ሃገረሰባዊ ምግብ የግጭት ማብረጃ ሆኖ ሲያገለግል ይታያል፡፡ መኤኒቶች በአብዛኛው አዘውትረው የሚጠቀሙት የበቆሎ ገንፎ ሲሆን ለመጠጥነት ቦርዴን አልፎ አልፎ አረቄና ጠጅም እንደሚጠቀሙ ተገልጿል፡፡ በተለይ በተለያዩ ስርዓተ ከበራዎች ላይ ከዘወትራዊው በተለየ መልኩ ትዕምርታዊነት ያዘሉ ምግቦችን የሚመገቡ ሲሆን መኤኒቶች ከዘወትሯዊው አመጋገባቸው ውጭ በአሻ (በባህላዊ የእርቅ ስነስርዓት ወቅት) የማሽላ ገንፎን ለእርቅ ከታረደው በግ ጥብስ ጋርእየቀላቀሉ እንደሚመገቡና ይህ የማሽላ ገንፎ የተመረጠበትም ሁኔታ ማሽላ በበሃሪው አንዴ አፍርቶ የሚያቆም ሳይሆን በየጊዜው እንደአዲስ የሚያብብና የሚያፈራ በመሆኑ በአሻነት የተከፈለችው ሴትም እንደ ማሽላው እንድትወልድና እንድትከብድ ፤የሟችንም ወገኖች እንድትክስ በማሰብ እንደሆነ ተገልፆ እናገኘዋለን፡፡ ይህም በልቦለዱ ታሪክ መካከል ተፈጥሮ የነበረውን ግጭት እንዲረግብ በማድረግ አስተዋጽኦ ሲያበረክት ይታያል፡፡ ለአብነት ያክል ቀጣዩን እንመልከት

የመኤኒቶች ዘወትራዊ ምግብ የበቆሎ ገንፎ ቢሆንም በአሻ ሥርዓት ክዋኔ ወቅት የሚያገነፉት የማሽላ ገንፎን ለእርቅ ከታረደው የበግ ጥብስ ጋርአቀላቅለው ለሽማግሌዎች አቀረቡ፡፡ ሽማግሌው ቅርቴችና ከሚች ወገን በእድሜ ተለቅ የሚሉት ሽማግሌ የተደበላለቀውን ሥጋና የማሽላ ገንፎ በቅድሚያ ቀምሰው በአካባቢው ለተሰበሰቡት ሁሉ እንዲቃመሱ አደረጉ (መኤኒት፤223)፡፡

### 4.2.3.3 ህዝባዊ ስፍራዎች

እነዚህ ስፍራዎች በሁለቱም ስራዎች ውስጥ የሚገኙ ሲሆን ህዝባዊ ስፍራዎቹ በማህበረሰቡ ዘንድ ማህበራዊ ዋጋ የሚሰጡና በማህበረሰቡ ባህል መሰረት የተለያዩ ባህላዊና ማህበራዊ ስርዓቶች የሚከወኑባቸው ናቸው፡፡አጠቃላይ የማህበረሰቡ አባል እነዚህን ስፍራዎች ከሌሎች ስፍራዎች በተለየ መልኩ የሚንከባከባቸውና የሚጠብቃቸው ሲሆኑ የማህበረሰቡን ባህል፤ እምነትና ፍልስፍና ይንፀባረቅባቸዋል፡፡

በእምቢታ ታሪካዊ ልቦለድ ውስጥ በጉራጌዎች ዘንድ የህዝብ አደባባይና ሰፊ ክፍት ቦታ "ጀፎረ" በመባል የሚታወቅ መሆኑንና በዚህ ህዝባዊ ቦታም ሴቶች መገኘት የማይችሉ መሆኑ በስፍራው የተለያዩ የመስቀል በዓል የሚከበርበት፤ የሽምግልና ስርዓት የሚካሄድበት ስፍራ እንደሆነና ወርድወት እዚህ ስፍራ በመገኘቷ ባህሉን እንደጣሰና እንዳፈነገጠች የተቆጠረችበት ስፍራም መሆኑን በታሪካዊ ልቦለዱ በገጽ 52 ላይ እንዲህ ተገልፆ እናገኘዋለን፡፡

"ዳሞ!"

"ዮ!" አሉ የወርድወት አባት አቤት" ማለታቸው ነው፡፡

"የያዝነው ጉዳይ ትልቅ አይደለም ወይ?"

"ነው!" ምላሽ ሰጡ፤ ምን ልጠየቅ ይሆን የሚል ጉጉት እየታየባቸው፡፡

"ታዲያ ሴት ልጅህ በኛ መሃከል መገኘቷ ነውር አይደለም ወይ?"

"…ተዋት የሌለች ያህል ቁጠሯት፡፡" አሉ ዳሞ፡፡ የዳኝነት ማዕረግ ለሴት ልጅ ሰጥተን አይደል እኛ መሃል የተገኘችው፡፡ እንዲያው ገና ከአሁኑ የትዳር ህይወት እየመረራት እና በባልዋ እያጉረመረመች ስለሆነ ዛሬ የሚባለውን መስማቷ ትምህርት ይሰጣታል፡፡"

ጠያቂው አላስጨረሳቸውም፡፡ በስጨት ቆጣ ብለው "የመረራት እንደሆነስ፤ ከእኛ ጋር እኩል ቤት እመካከላችን ሆና መቀመጧ እንዴት ያለ ነገር ነው?እንዴትስ ብትንቀን ነው?" አሉ፡፡

…ሽማግሌዎቹ አንድ የተፋለሰ ስርዓት መኖሩን ልብ ካሉ ወዲህ ልባቸው

መረጋጋት አልሆነለትም፡፡

"እኛ በመሃላችሁ ብንገኝ ምን እናጎድልባችኋለን?" አለች ወርድወት፡፤ እኔ እዚህ ስለተገኘሁ በምክክራችሁ ስለተሳተፍኩ ሴት በመሆኔ ብቻ ያለባላ የቆመው ሰማይ አይወድቅም፤ ምድርም ተደርምሳ አትውጠንም፡፡

"ምን?" ይህንን ቃል የተናገሩት ሁሉም ናቸው፡፡

"ምን እናጎድልባችኋለን?" ደገመችው ኮስተርተር ብላ፡፡

ማጉተምተም ከየጥጋጥጉ ተሰማ፡፡ ኣባቷም በዓይናቸው ገሰጿት፡፡ነገር

እንድታበርድ ፈልገው…(እምቢታ፤28-33)፡፡

ከዚህ የገፀባህርያት ምልልስ የምንረዳው በጉራጌ ባህል በዘመኑ ሴት ልጅ የማትገኝባቸው በአካባቢው ተመራጭ ሽማግሌዎች መሪነት በወንዶች ተሰብሳቢነት የተለያዩ ውይይቶች እና ስር ያልሰደዱ ሽምግልናዎችን በአጠቃላይ ስለ ሃገራቸው ፣ ስለቤተሰቦቻቸው የሰላም ጉዳይ በጋራ የሚሰባሰቡና የሚመክሩበት የተለየ ስፍራ እንዳላቸው ሲሆን ወርድወት ይዛው ከተነሳችው አብይ ጥያቄ አንዱ ሴት ልጅም እንደ ወንድ ሁሉ በህዝባዊ ስፍራዎች ተገኝታ ሃሳቧን በነፃነት የመግለጽ ነፃነት ይሰጣት ፤ስለ ሃገሯም ሆነ ስለቤተሰቧ ህልውና ለመወያየት ትቻል የሚል በመሆኑ ሽማግሌዎቹ ደግሞ ይህ ከተደረገ እንደተናቁ ባህላቸው እንደተደፈረና ነውር እንደሆነ በማመን ክልከላ ያደርጋሉ፡፡ በዚህ ወቅት በሽማግሌዎችና በወርድወትና በደጋፊዎቸቿ መካከል ከፍተኛ ግጭት ሲፈጠር ይታያል፡፡

በሌላም በኩልጉራጌዎች እጀካ (ባህላዊ ሸንጎ) የሚካሄድበት ታሪካዊ ስፍራም እንዳላቸው ተገልጿል፡፡ ይህን ስፍራ መርገጥ የተፈቀደላቸው የሰባት ቤት ሽማግሌዎች እንደሆኑና እነዚህም ሽማግሌዎች ቃላቸውየማይሻር፤ ሃሳባቸው የማይታጠፍ ሲሆኑ ቁጥራቸው ከ12 የማይበልጡና ከነሱ ውጭ ከሳሽ ተከሳሽና ጉዳዩ በቅርብ የሚመለከታቸው ሰዎች ብቻ የሚገኙበት ልዩና ታሪካዊ ስፍራ መሆኑ በዚህ ስፍራም በተመሳሳይ ሁኔታ ሴት ልጅ መገኘት እንደማትችል ተገልጿል፡፡ይህ ደግሞ ከላይ እንደተገለፀው ሁሉ ለግጭቱ መባባስ ከፍተኛውን ድርሻ ሲወስድ ይስተዋላል፡፡ በአጠቃላይ የታሪካዊ ልቦለዱ ደራሲ ይህን

የቁሳዊ ባህል ምድብ የሆነውን ህዝባዊ ስፍራ በልቦለዱ ውስጥ በማስገባት በልቦለዱ ውስጥ ተከስቶ የነበረውን ግጭት ይበልጥ ለማክረርና ለማጦዝ ተጠቅሞበታል፡፡

*በመኤኒት* ልቦለድ ውስጥ ደግሞ በተቃራኒው ይህ ህዝባዊ ስፍራ የልቦለዱ ግጭት እንዲበርድ በማድረግ ረገድ አገልግሎት ላይ ሲውል ይታያል፡፡ ይህ ስፍራ ለማህበረሰቡ ልዩ ማህበራዊና ባህላዊ ጠቀሜታ የሚሰጥሲሆን ስፍራው የተመረጠበት አንዳች ትዕምርታዊ ፍቺን የያዘ ነው፡፡ እርሱም መኤኒቶች በባህላቸው መሰረት በገዳይና ተገዳይ መካከል የተከሰተን ጸብ ለማብረድና የእርቅ ስርዓት ለመፈጸም የሚመርጡት ስፍራ ወራጅ ወንዝ ዳር መሆኑንና ይህም የሆነበት ዋነኛ ምክንያት በሁለቱ ወገኖች መካከል ተፈጥሮ የነበረውን የመበቃቀልና ቂም የመያያዝ ሁኔታ ወንዙ ጠራርጎ እንዲወስደውና በምትኩ ሰላም እንዲመጣ በማሰብ መሆኑን በልቦለዱ በገጽ 217 ላይ እንዲህ ሰፍሮ እናገኘዋለን፡፡

> በመኤኒት ብሂረሰብ ልማድ ለአሻ እርቅ ሥነ ስርአት የሚመረጠው ቦታ ወንዝ ዳር ወይም ሸጥ ዳር በመሆኑ ከሚች ወገኞችና ከአዛውንቱ ኬላጊ መንደር መካከል ወደ ሚች መንደር አካባቢ ጠጋ ወዳለ ሸጥ ስፍራ አሻው እንዲከናወን በሁለቱም ወገን ሽማግሌዎች ተቀጠረ፡፡የገዳይ ወገኖች ከወንዙ ወዲህ ማዶ የሚች ወገኖች ደግሞ ከወንዙ ወዲያ ማዶ ቆመው ደቂቃዎች ተቆጠሩ፡፡ የሁለቱም ወገን ሽማግሌዎች ከሸጡ አካፋይ ላይ ሲደርሱ ቆሙ፡፡ የሚች ወገን ሽማግሌዎችም "ቀሪ ከብቶቻችንን አምጡ" አሉ፡፡ ከብቶቹን በገመድ አስረው የነበሩት ጎልማሶች ፈጠን ፈጠን እያሉ ከብቶቹን ከኋላ ኋላቸው እየገረፉ ለሽማግሌዎች አቀረቡ ሽማግሌዎችም ተቀብለው ለሚች ወገን ሽማግሌዎች አስረከቡ፡፡ የሚች ወገኖችም በሆነው ነገር የመፎከርና የደስታ ስሜት አሰሙ፡፡ ደግመውም "ልጃችንን አስረክቡን" አሉ፡፡ የገዳይ ሽማግሌዎችም "ሾንቤ መንዴ ኤጉዋ ወሽጋዲንያ ጣዲያቦይ" አሏቸው "የልጃችሁ ምትክ ይችትና ተቀበሉን" ለማለት፡፡ የገዳይ ሽማግሌዎች መጥተው ከአዛውንቱ ኬላጊ ሚስት ተቀብለው ፍራኦልን ለገዳይ ሽማግሌዎች አስረከቧት፡፡ ፀባችን እንደዚህ ወንዝ ይውረድ" ተባባሉ ተደሰቱ (*መኤኒት*፤217-220)፡፡

መኤኒቶች የሚሰበሰቡበት ህዝባዊ ቦታ እንደ ጉራጌዎች ባህል ሴቶችን የማያሳትፍ ሳይሆን ማንኛውም ሴትም ሆነ ወንድ የሚች አልያም የገዳይ ወገን እስከሆነ ድረስ ቂም በቀሉና መፈላለጉ የማይቀርለት መሆኑን በማወቅ መገኘት ግዴታው ነው፡፡ በዚህ ልቦለድ ውስጥ ደራሲው ይህንን ህዝባዊ ስፍራ የጠቀሰው ለአንዳች ፋይዳ ሲሆን በሁለቱ ወገኖች መካከል በከፍተኛ ሁኔታ ተካሮ የነበረውን ፀብ ዳግም በመበቃቀል እንዳይቀጥልና ግጭቱ እዚሁ ላይ እንዲያበቃ ለማድረግ ሲሆን በዚህ ፎክሎራዊ ጉዳይ አማካይነት በልቦለዱ ውስጥ በከፍተኛ ደረጃ ተካሮና ጫፍ ወጥቶ የነበረን የሁለት ወገኖች ግጭት ለማርገብ እንደቻለም እንረዳለን፡፡

### 4.2.3.4 ሃገረሰባዊ ትዕምርት

*በእምቢታ ታሪካዊ ልቦለድ ውስጥ ትዕምርታዊነት ያላቸውና በልቦለዱ ውስጥ እንደ መባያ ጉዳይ ሆነው የመጡ ማህበረሰቡ በትርጓሜያቸውና በውክልናቸው ላይ እርስ በርስ የሚግባባቸው ብሎም የሚተገብራቸው የማንነቱ መገለጫ የሆኑ ቁሳዊ ባህሎች እንደ "ምድጃ" "ምሰሶ" "ችቦ" እና "እንሰት" አይነት ቃላት በስፋት በታሪካዊ ልቦለዱ ከሃያ በላይ በሆኑ ገፆች ውስጥ ተደጋግመው ሲመጡ ታይተዋል፡፡ እነዚህ ሃገረሰባዊ ትዕምርቶች የመባያ ጉዳይ ሆነው በመምጣት የማህበረሰቡን ፍልስፍና፣ አመለካከት፣ እምነትና ባህል የሚያንፀባርቁ ናቸው፡፡መኤኒት በተሰኘው ስራ ውስጥ ግን እነዚህን የመባያ ጉዳዮች ለማግኘት አልተቻለም (አፅንኦት ከራሴ)፡፡*

*እነኚህ ቃላት በታሪካዊ ልቦለዱ ውስጥ ከጅማሬው እስከ ፍፃሜው ድረስ ከ20 በላይ በሆኑ ገፆች ተደጋግመው ተወስተዋል፡፡ ቃላቱ ትዕምርቶች ሲሆኑ ምንም እንኳ የገቡበት ቦታ የተለያየ ቢሆንም በተገኙበት ቦታ ሁሉ ተመሳሳይነት ያለው የውክልና ትርጓሜ ይዘው እናገኛቸዋለን፡፡ በአብዛኛው የቃላቱ እንደ መባያ ጉዳይ ሆኖ የመምጣት ዋናው ዓላማ የልቦለዱን ጭብጥ ለማመልከት (ለመጠቆም) እና ለማጉላት ሲሆን ቀጣዮቹን ለአብነት እንመለከታለን፡፡*

> *ቀና ትልና ደግሞ በር በሩን ታያለች ፣ ምንም የለም፣የሚገባም የሚወጣም የለም፡ ፡አጋዝ አልመጣም፡፡ገብቶኛል፡፡ሁላችንም ገብቶናል፡፡ ልቧ እዚህ አይደለም፡፡ አጋዝ ወዳለበት ነው፡፡ምድጃው ላይ ያለው እሳት በነበልባሉ ቤቱን በብርሃን አጥለቅልቆት እንዳልነበር አሁን የቤቱን እመቤት መስሏል፡፡ ፈዝዟል ቀዝቅዟል ድንገት ብድግ አለች ሳይታወቀኝ እኔም ብድግ አልኩ፡፡ ምሰሶው ስር ነበርኩ እሷ ደግሞ ወዲያ ከከብቶቹ ትይዩ ባለ ጥግ ተቀምጣ ነበር፡፡ብድግ አለችና እኔን አዝዛማስፈፀም ስትችል ራሷ ምድጃው ላይ የነበረውን እሳት በጥድፊያ አጠፋችው፡፡ ቤቱ በሚያስቀይም ጭስ ተከበበ ፣ በሚያስነጥስ ጭስ ተወረረ አይኖችን በሚያጨናብስ፡፡ ምንም አልመሰላትም፡፡ በየእሳቱ ሳይበቃት ወደ ምሰሶው ተጠጋችና ሰብ ይፈዝ ከሚባለው ባሪያ ችቦውን ተቀበለችው፡፡ ይህ በመጠኑ አነስ ከቁመቱ አጠር የሚለውሰብ ችቦዎቹን የማሰናዳት፤ሲመሽ አንዱን ችቦ መርጦ የመለኮስ፤ የለኮሰውንም ችቦ ይዞ ምሰሶው አቅራቢያ የመቆምና ቆሞ ደግሞ ለጎጆው ተጠላዮች ብርሃንየመስጠት ሃላፊነትተተጥሎበታል፡፡ባልና ሚስቱ ለመተኛት ዝግጁ ሲሆኑ ነው የምሽት ስራውን እንዳገባደደ የሚያውቀው፡፡ አሁን ቀጥ ብሎ አንገቱን ደፍቶ የለኮሰውን ችቦከአናቱ በላይ አድርጎ የጌታውን መምጣት በንቃት በሚጠባበቅበት ሰዓት እመቤት ወርድወት ወደ አጠገቡ መጣችና ችቦውን በግራ እጇ የመመንተፍ ያህል ወሰደችበት፡፡ ደነገጠ እንዲህ አድርጋ አታውቅም ፤እንዲህም አይደረግም ችቦውን የማጥፋት ስልጣን በእጁ*

> ነው፡፡ ማንም አይነጥቀው ወርድወት ግን <u>ችቦውን</u> ተቀብላ <u>ምድጃው</u> ላይ ወርውራ ከሶስት ጉልቻዎች አንዱን አንስታ <u>ችቦው</u> ላይ ጫነችበት፡፡ ጎጆ ቤቱ ጨለመ <u>ምድጃው</u> ላይም ውሃ ቸለሰችበት (እምቢታ፤11-12)፡፡ (አፅንኦት የራሴ)

ከላይ ከቀረበው ሃሳብ እንደምንመለከተው ትዕምርታዊ ፍቺን የያዙ እነዚህ ቃላት በአንዲት ገፅ ላይ ብቻ እንኳ ምን ያህል ተደጋግመው መፃፋቸውን ነው፡፡ የተደጋገሙት ቃላት በትዕምርታዊነት የልቦለዱ የመባያ ጉዳይ ሆነው የሚያገለግሉ ሲሆን የልቦለዱን ጭብጥ ለማግኘት የሚረዱ ናቸው፡፡ የልቦለዱ አንድ ጭብጥ የወርድወትን “እምቢተኝነት” የሚገልጽ ነው፡፡ ወርድወት እኛ ሴቶች በወንዶች የበላይነት በሚያምነው ልማድና ባህል መገዛት ይብቃን የራሳችንን ህይወት ካለማንም ጣልቃ ገብነት ራሳችን እንምራው የሚል ሃሳብ ይዛ መጓዟና በሃሳቧም እስከመጨረሻው እንደምትገፋበት የሚነግረን ጉዳይ የልቦለዱ አንድ ጭብጥ ነው፡፡ ከላይ የቀረበው ሃሳብም ይህንኑ ጭብጥ የሚጠቁም ነው፡፡

በአንድ ገፅ ላይ ተደጋግመው ከመጡት መባያ ጉዳዮች በተጨማሪም በተለያዩ ገፆች የተገለፁትንም በመውሰድ ቃላቱ ምን ያህል ትዕምርት እንደሆነና የመባያ ጉዳይነታቸውም እርግጠኛ እንደሆነ ለማሳያነት ቀርበዋል፡፡

ምድጃ፤- ምድጃ የሸክላ ምርት የሆነና ምንም አይነት ዘመናዊ ማሽን ሳይፈልግ በእጅ የሚሰራ ጉልቻ መሬት ላይ ተጎልቶበት የተለያዩ ምግብና መጠጦችን ለማብሰል የምንገለገልበት ስፍራ ሲሆን በዚህ መፅሃፍ ውስጥ የገባው ግን ይህን ትርጓሜ ይዞ ሳይሆን በትዕምርትነት ነው፡፡ምድጃ ትዳርን የሞቀ የደመቀ ኑሮን የሚያመላክት ሆኖ እናገኘዋለን፡ ፡ወርድወት ትዳሯ እንዳበቃለት ከዚህ በኋላ ባለቤቷ የነበረውን አጋዥ እንደማትፈልገው ለመንገር ደራሲው ምድጃው ላይ ውሃውን ስትቸልስበት ያሳየናል፡፡ ይህን ስታደርግ ደግሞ እንደሌላውጊዜ ባሪያዋን አዝዛ አልነበረም በራሷ እጅ ነው፡፡ ይህም ወደ ጭብጡ ይመራናል እንደተባለውም መጨረሻ ላይ የወርድወትና የአጋዥ ያማረና የደመቀ ትዳር ከወግና ባሉ ውጭ፣ ያለ ባለቤቷ ፍቃድ ፣ ያለሽማግሌዎች ፍላጎትና ያለ ማንም ረዳት በወርድወት እምቢተኝነት ብቻ ሲፈርስ ይታያል፡፡ “ምድጃን” በታሪካዊ ልቦለዱ በሌላ ገፅ ላይም እንዲህ ተገልፆ እናገኘዋለን፡፡

> አጋዝ ፋርችዩ ከሙህር ተነስቶ ኧገር ደረሰ፡፡ “የተረገመ ቀን”! ብሎ ተራገመ፡፡ የሙህር ሰማይ ፈገግ ብሎ አልተቀበለውም፡፡ ፊቱንም ልቡንም እንዳጠቆረበት የገባው ባዶ እጁን ሲመለስ ነው፡፡የቃቄ ወርድወትን አጥቶ፡፡ ሙከራው ሁሉ ጉም የመጨበጥን ያህል ፈታኝ መሆኑ አናዶታል፡፡ ቤት ውስጥ እንደገባ <u>ምድጃው</u> ላይ

የተጣደውን ጀበና በያዘው ከዘራ መታው፡፡ ጀበናው ውሃ ነበረው፡፡ ከዘራ ሲወርድበት ተፈረካከሰ፡፡ የነበረውን ክብር አጣ፡፡ ውሃው እሳቱ ላይ ፈሰሰ፡፡ እሳቱ የመጣበትን ድንገተኛ አደጋ መቋቋም አልሆንልህ ብሎት ብስጭቱን ተፋ፡፡ አመዱንም አቦነነው ቤቱ በጭስ ተሞላ፡፡ ተጨናበሰ፡፡ (እምቢታ፤130) (አፅንኦትየራሴ)፡፡

ይህ አንቀፅ እንደሚያስረዳው ትዳሩን መፍታት ያልፈለገው አጋዝ ወርድወትን ክሶና መልሶ በክብር ሽማግሌ ልኮ የማግባት መብት አለኝ ብሎ ያስብ የነበረው አጋዝ የወርድወትን ለሁለተኛ ጊዜ አስደንጋጭ እምቢታ ከሰማ በኋላ ወደ መኖሪያ ቤቱ ሄዶ ትዳሩ እንዳበቃለት በሴቶች ዘንድ የነበረውን ክብር እንዳጣና ይህንን ድንገተኛ ክስተት መቋቋም ያለመቻሉንና አጋዝ ወርድወትን ከፈታ በኋላ ህይወቱ እንደበፊቱ ያማረና የሰመረ እንዳልነበረ ለመንገር ደራሲው የተጠቀመው ሲሆን ይህም በንግር ቴክኒክ ምክንያት አንባቢያንን ወደ ጭብጡ እንዲያመሩ ሲያደርግ ተስተውሏል፡፡ "ምድጃ" የሚለውን ቃል ትእምርታዊነትን የያዘ የመባያ ጉዳይ መሆኑን ለማረጋገጥ ይረዳ ዘንድ ቀጣዩን ከልቦለዱ ከሌላ ገጽ የተቀነጨበ ሃሳብ ለማሳያነት እንመልከት፡-

"ምነው ሳልዘጋጅ!? እንግዳ ሆናችሁ እንደምትመጡብኝ ለምን ቀደምብላችሁ አልነገራችሁኝም?" አሉ ዳሞ ፤ቤታቸው ተዝረክርኮ በመገኘቱ አፈር ብለው፡፡ ቁርበቶቹ እዚህም እዚያም ተነጣጥፈዋል፡፡ ጉልቻዎቹ ተዝረክርከዋል፡፡ <u>ምድጃውም</u> ሰውም፤ እንስሳውም ከእንቅልፉ አልነቃም ሁሉም ቀዝቅዟል፡፡

"ቁጭ በሉኣ! ዳሞ መቀመጫ በርጬማዎችን አቀራረቡ፡፡

"አንቀመጥም! የምንቀመጠው የመጣንበት ጉዳይ ሲሳካ ነው!"

"ታዲያ ልስማዋ ፣ ምንድነው ጉዳዩ?"

"ልጅዎትን ለልጃችን ልንጠይቅ ብለን ነው!"

ዳሞ ሳያስቡት በርጩማ ስበው ተቀመጡ፡፡እኔ ደግሞ የተፈለጠ እንጨት ከቆጥላይ አውርጄ <u>ምድጃውን</u> ሞቅ ሞቅ ማድረግ ጀመርኩ፡፡ ይህ ሁሉ ሲሆን ወርድወት ወደዚህ አልመጣችም እርሷ ያለችው እልፍኝ ውስጥ ነው(እምቢታ ፤ ፤118-119)(አፅንኦት የራሴ)፡፡

ከላይ ከቀረበው ሃሳብ የምንረዳውየምድጃው መቀዝቀዝ እና አለመንቃት በዚህ ታሪካዊ ልቦለድ ውስጥ ምድጃ የሞቀና የደመቀ ትዳርን ወክሎ የቆመ በመሆኑ ወርድወት እንደዚያ የሞቀ ትዳርዋን ከበተነችና የመጀመሪያ ባሏን ከፈታች በኋላ ለብዙሃኑ ሴቶች የታገለችለት

ዓላማ እሷን ብቻ ነጻ አውጥቶ ለሌሎቹ ያልተረፈች በመሆኗ ወደ አባቷ ቤት ተመልሳ የምትኖረውን የቀዘቀዘና የብቸኝነት ህይወትና የትዳሯን መፍረስ ለመጠቆም የገባ ሲሆን ሁለተኛው ላይ የምናገኘው ምድጃ ወርድወት እንደገና ለትዳር መጠየቋንና ትዳሯ ዳግመኛ ሊሞቅ መሆኑን ደራሲው በንግር ቴክኒክ ተጠቅሞ ጭብጡን ለመጠቆም (ለማመልከት) ያስገባው መሆኑን እንረዳለን፡፡ ቀጣዩም በተመሳሳይምድጃን በትዕምርትነት በመያዝ ደራሲው እንዴት ጭብጡን ለማጎልበት እንደተጠቀመበት የሚጠቁም በታሪካዊ ልቦለዱ ማብቂያ አካባቢ የተገኘ ሃሳብ ነው፡፡

> የጌረሞ ፉጋና ወርድወት በግ አርደው ፤ክትፎ አሰናድተውና አረቄ አስገዝተው አካባቢው ያፈራቸውን ምሩጣንን ለምሽት ሽንጎ ጋብዘው ሳቅና ጨዋታ የበዛበት ማታ እያሳለፉ ነው፡፡
>
> “አባ” አለች ወርድወት አባቷ ትከሻ ላይ መርጋት ያቃተውን ብሉኮ እያስተካከለች፡
>
> “እንዴት አገኘሽኝ?” ብላ ጠየቀቻቸው፡፡
>
> ፈገግ አሉ፤ ዳሞ ቃቄ፡፡ ቤቱ በብርሃን ደምቋል፡፡ብርሃኑ ከምድጃው ስር የሚወጣው ነበልባልና አሽከሩ ከያዘው የተለኮሰ ችቦ የወጣ ብቻ አይመስልም ከእሳቸው ፈገግታ የፈለቀም ጭምር እንጂ (እምቢታ፤161) (አፅንኦት የራሴ)፡፡

ወርድወት ሁለተኛ ባሏን ወድዳ በራሷ ፍቃድ ካገባች በኋላ እንደዚያ ቀዝቅዞ የነበረው ስሜቷ ጠፍቶ በምትኩ ደስተኛ ሴት ሆና እርሷና ባለቤቷ አባቷን ጨምረው ሌሎች እንግዶችን ቤቷ የጋበዘችበትን ሁኔታ ከላይ ከተቀነጨበው ሃሳብ የምንረዳ ሲሆን ከምድጃው ስር የሚወጣው ነበልባል ማማር የነወርድወትን አዲስ የትዳር ህይወት መሞቅና የሰመረ መሆን የሚገልጽና አባቷም በልጃቸው አዲስ የትዳር ህይወት ደስተኛ እንደሆኑ ለመንገር ደራሲው ምድጃን በትዕምርትነት የመባያ ጉዳይ አድርጎ ያመጣ ሲሆን ከነበልባሉ የወጣዉ ብርሃኑ ከችቦዉ ብቻ የወጣ አይመስልም የሚለዉ አባባልም ወርድወት ባህሉ ከሚያስገድዳት ወጥታም የተሻለ ሕይወት እንዳገኘችና ደስታ የሚገኘዉ የግድ ሰዉ በወሰነልን ህይወት ብቻ ስንኖር ሳይሆን የሚጠቅመንን ማድረግ እንዳለብንም ለማሳወቅ ተጠቅሞበታል፡፡

ምሰሶ ፡-ምሰሶ ቤት ሲሰራ የቤቱን ሙሉ ሃይል የሚሸከም ቋሚ እንጨት ሲሆንከጉራጌ ማህበረሰብ ጋርየጠበቀ ቁርኝት አለው ምክንያቱ ደግሞአብዛኛውየዚህ ማህበረሰብ መኖሪያ ቤት ባህላዊ ጎጆ ነው፡፡ ማህበረሰቡ መኖሪያ ቤቱን ለመስራት ከሸክላና ብረት ጋርየተገናኘ

ዝምድና የለውም ከእንጨት እንጂ፡፡ ከእንጨትም ምሰሶ ነው እጅግ አስፈላጊያቸው፡፡ ያለ ምሰሶ ቤት ማቆም አይታሰብም ሌሎች እንጨቶች በሙሉ ምሰሶ ከሌለ እንዳሉ አይቆጠሩም፡፡ የፈለገ ብዛት ቢኖራቸውም ብቻቸውን መቆምና ቤት መሆንም አይችሉም፡፡ አንድ ትልቅ የሚያምር የጉራጌን ጎጆ ለመቀለስ ሁሉም እንጨቶች ከምሰሶው ጋር በህብረት መቆምና ተያይዘውም መታሰር አለባቸው፡፡ ምሰሶ በዚህ ታሪካዊ ልቦለድ ውስጥ የጉራጌን የረጂም ዘመን የቆየና የጠነከረን ባህል ወክሎ የቆመና ትዕምርታዊ ፍቺ ያለው የመባያ ጉዳይ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ በጉራጌ ማህበረሰቡ ዘንድ  አጠቃላይ አባላቱ ተስማምተው ከሚተገብሩት አንዱ ባህል ደግሞ ወንድ ልጅ ከሴቶች በተለየ መከበር አለበት የሚለው ነው፡፡ በጉራጌ ባህል ወንድ ያሻውን ማድረግ እንዲችል፣ የፈለገውን ማግባትና ባሻው ጊዜም መፍታት እንዲችል፣ ፈቶም የፈታት ሚስት በሰላም የመኖርና ሌላ የማግባት ህልውናዋ በወንዱ እጅ እንዲሆን የቤተሰቦቹን ሃብትና ንብረት በብቸኝነት የመውረስ ፣ በተለያዩ ሸንጎዎች ላይ በነጻነት ሃሳቡን የማንሳትና የመጣል አጠቃላይ ነፃነት የተሰጠው ለወንድ ልጅ ነው፡፡ይህ ምሰሶም በታሪካዊ ልቦለዱ ውስጥ በትዕምርትነት የጉራጌን “ባህል” ወክሎ የቆመ ሲሆን የልቦለዱ የመባያ ጉዳይ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ይህ የቁሳዊ ባህል ምድብ የሆነው ምሰሶ ትዕምርታዊነትን በመያዝና የልቦለዱ የመባያ ጉዳይ በመሆን የታሪካዊ ልቦለዱ አንዱ ጭብጥ የሆነውን ህብረት (አንድነት) ለማጉላት ሲገባ እናገኘዋለን፡፡

“ድንገት ብድግ አለች ሳይታወቀኝ እኔም ብድግ አልኩ፡፡ “<u>ምሰሶው</u> ስር ነበርኩ፡፡ እሷ ደግሞ ወዲያ ከከብቶቹ ትይዩ ባለ ጥግ ተቀምጣ ነበር” (፣ገፅ፣11)፡፡ ከዚህ ሃሳብ የምንረዳው በዚህ ማህበረሰብ ማንም ይሁን ማን ባህሉ በሚያዘው ልክ መኖር እንዳለበትና ለባህሉም ተገዚ መሆን እንደሚገባው ሁሉ ተራኪዋ ሴት ምሰሶ ስር መቆሟ ለባህሉ ተገዢ መሆኗን ሲያመላክት ወርድወት ግን ወዲያ ከምሰሶው ርቃ መቆሟ ስርዓቱንና ወጉን መቃወሟና ባህሉ በፈቀደላቸው በወንዶች ፈላጭ ቆራጭነት የመኖሯ ጉዳይ እንዳበቃለት ለማሳየትና ጭብጡንም ለማጉላት ገብቶ እናገኘዋለን፡፡ በልቦለዱ በሌላ ገፅ ላይም እንዲሁ ይህ ምሰሶ የጉራጌን የረጂም ዘመን ፍልስፍናና ባህል ወክሎ ሲቆም እንመለከታለን፡፡

“ለቡና ቁርስ የሚሆን ቆጮ ተፈርፍሮ የሚሰራ “ባራንብራት” ተብሎ የሚጠራ ምግብ ተሰርቶ ነበርና ይጎፍላቸው ገባሁ፡፡ <u>ምሰሶው</u> አጠገብ የተቀመጠችው፣የአጋዝ ዳርሳሞ አገልጋይ ቡና እየቀዳች ነው፡፡እሷ የቀዳችውንና ቅቤ የተንሳፈፈበትን ቡና ዘበርጋ ተቀብሎ ለእንግዶቹ እያደረሰ ነው…(ገፅ፣190)፡፡” በዚህ ገፅ ላይ ምሰሶ ከወርድወት ቤት ወጥቶ ወደ

አጋዝ አባት ወደ ዳርሳሞ ቤት ሲሄድ ይስተዋላል፡፡ የአጋዝ አገልጋይ ምሰሶውስር የመቀመጢ ምክንያት ምሰሶ የማህበረሰቡን ወግና ባህል ወክሎ የቆመ በመሆኑ ምንም እንኳ የጉራጌ ባህል ለወንዶች የሚያደላና በተቃራኒው ሴቶችን የሚገድብ ቢሆን ይህችም ሴት ሴት ብትሆንና የገፈቱ ቀማሽ ብትሆንም ለወጉና ልማዱ እንደምትገዛ፤ ባህሉ ባለው የምትስማማና በባህሉ ውስጥ ያለች ሴት መሆኗን ለመንገር ነው፡፡ ከቀጣዩ ከታሪካዊ ልቦለዱ ለአስረጂነት ተቀንጭቦ ከተወሰደ ሃሳብ መመልከት እንደሚቻለውም "ምሰሶ" ባህሉን ወጉንና ስርዓቱን ወክሎ ለረጅም ዘመን ከማህበረሰቡ ጋር የተቆራኘ እንደሆነ ነው፡፡

> ቤቶቹ ክቦች ናቸው፡፡ ምሰሶው ከሚቆምበት ቦታ አንስቶ እስከ ግድግዳው ድረስ ያለው ክፍት ቦታ በእግር ነው የሚለካው፡፡ ስፋቱ እንደየሰው አቅምና የኑሮ ደረጃ ይለያያል፡፡ትንሽ የተባለው ቤት በስምንት የእግር ኮቴ ሲለካ፤ትልቁ ደግሞ አስራ አራትም አስራ ስድስትም ይደርሳል፡፡ ግድግዳው በሰፋፊ የጥድ ፍልጦች ነውየሚበጀው፡፡ በጥድ ከታጠረ በኋላ ከውስጥም ከውጭም በቀርከሃ ይከበባል፡፡ በቃጫ ገመድ ይታሰራል፡፡ ግድግዳው ከቆመ በኋላ ነው <u>ምሰሶው</u> የሚተከለው፡፡ <u>ምሰሶው</u> ቀጥ ያለና ብዙ አመትን ያስቆጠረ ሲሆን ርዝመቱና ክብደቱ እንደየሰው አቅም ይለያያልአንዱን <u>ምሰሶ</u> ለማቆም ቢያንስ የሃያአምስት ወይም የሰላሳ ሰው ድጋፍና ጉልበት ይጠይቃል፡፡ <u>ምሰሶው</u> ከቆመ በኋላ ጣሪያው ይጀመራል፡፡ እንዳንዱ በቁመት እኩል የሆነ ማገር ከግድግዳው ጫፍ ይዞ እስከ <u>ምሰሶው</u> አናት ድረስ ቀጥ እያለ በአግድም ይቆማል፡፡ ከዚያ ሳር ይለብሳል፡፡ ፀሃይ እንዳያስገባም ሳሩ ተደራርቦ በጥንቃቄ ነው ጣሪያው ላይ የሚከመረው፡፡ ግድግዳውንም ደግፎ እንዲይዘው በውስጥ በኩል <u>ምሰሶውን</u> ከግድግዳው ጋር የሚያገናኙ ጣውላዎች በዙሪያው ይመታበታል፡፡ ከጥንካሬው የተነሳ እያንዳንዱ ቤት ሰባ ሰማንያ ዓመት ይኖራል...(እምቢታ፤41-42)(አፅንኦት የራሴ)፡፡

ከላይ በቀረበው አንቀፅ ላይ "ምሰሶ" የሚለው ቃል ወደ ስድስት ያህል ጊዜ ተደጋግሞ ሲመጣ ይታያል፡፡ ደራሲው በዚህ አንቀጽ እንዲተላለፍለት የፈለገው መልእክት ስለ ጉራጌ ቤት አሰራር ሳይሆን በትዕምርትነት በማህበረሰቡ ዘንድ ስላሉ ባህሎች እና ባህሎቹ ያስቆጠሩት ረጂም ዘመናት እንደሆነ፤ ልክ ምሰሶ ከሌለ ቤት ማቆም ከባድ እንደሆነ ሁሉ ባህሉ ከሌለ እነርሱም ለተለያዩ አደጋዎች እንደሚጋለጡ ደጋፊያቸውና ጠባቂያቸውወጉና ባህሉ እንደሆነ፤እያንዳንዱ የማህበረሰቡ አባላት ይህንን የማንነታቸው መገለጫ የሆነውን ወግ፣ ባህልና ፍልስፍና በህብረት የመደገፍ የመንከባከብና ቀጣይነት እንዲኖረውየማድረግ ሃላፊነት እንዳለባቸው፤ይህ ከሆነ ደግሞ ባህላቸው ሳይበረዝና ሳይከለስ ምንም አይነት አደጋሳያጋጥመው ረጂም ዘመናትን አብሯቸው እንደሚቆይ ለመግለጽ የተጠቀመበት በመሆኑ ይህ ሃገረሰባዊ ትዕምርታዊነት ያለው የመባያ ጉዳይ የታሪካዊ ልቦለዱን ህብረት (አንድነት) ለማጉላት ጥቅም ላይ ሲውል እናገኘዋለን፡፡

ችቦ፡-ችቦ ብርሃን የሚሰጥ ብርሃኑም ረጂም ቦታዎችን ሽፍኖ የሚያደምቅሲሆን በአብዛኛው ችቦ የብዙሃን የአንድነትና የህብረት ተምሳሌት ተደርጎም ይወሰዳል፡፡ በብዙ ቦታዎች ይህ ችቦ የሚበራው ሃይማኖታዊ በኣላትን ተመርኩዞ ነው፡፡ በጉራጌ ባህል ግን ከዚህ ይለያል በነወርድወት አይነት ባለትዳሮች ቤት ዘወትር በምሽት ባልና ሚስቱ ወደ መኝታቸው እስኪደርሱ ድረስ በአገልጋያቸው እጅ ተይዞ ችቦው ሳያቋርጥ ይበራል፡፡ ችቦውየጉራጌ ባህል በሚፈቅደውና በሚያዘው ልክ የባልና ሚስቱን ጥምረትና መዋደድ እንዲሁም ለደስተኛ ቤተሰብነት ሴቷ የግድ ወንዱን የመደገፍ የመተባበርና ባለው ሃሳብ የመስማማት ግዴታ እንዳለባት ማንጸባረቂያ ነው፡፡ በዚህ ታሪካዊ ልቦለድውስጥ "ችቦ" በትዕምርትነት የገባዉም ይህንኑ ወክሎ ነዉ፡፡ "ችቦ አብሪ ምንጊዜም ወንድ ነው፡፡ በምሽት የፈለገውን ችቦ መርጦ የማብራትም ስልጣን የርሱ ብቻ ነው፡፡ የሚቆምበት ስፍራም አይቀየርም ምሰሶው ስር ነው፡፡" ምሰሶ ደግሞ የጉራጌን ማንነት የሚያንፀባርቅ ቋሚና የማለወጥ ባህልን የሚወክል ሲሆን ችቦ አብሪው ወንድ መሆኑና በምሽት ያሻውን ችቦ መርጦ የመለኮስ መብት ያለው መሆኑ የጉራጌ ባህል ምንጊዜም ሴት በወንድ ስር እንድትሆን፤ ያለ ወንዱ ፈቃድ ምንም ማከናወንና ወደየትም ማፈንገጥ እንደማትችልና ከወንዱ ፈቃድ ወጣች ማለት ባህሏን እንደጣሰች የሚቆጠርመሆኑን የሚያመላክት ሲሆን በምሽት ያሻውን ችቦም መርጦ መለኮሱ ችቦ ሴቷ በወንዱ ስር ብቻ እንድትሆን (የቤት ራስ ወንድ ብቻ ነዉ) የሚለዉን ወክሎ የቆመ እንደመሆኑ አባወራው በምሽት ካሉት ሚስቶች መሃል የፈለጋት ጋርመርጦ ማደር እንዲችል ባህሉ የፈቀደለት መሆኑን የሚያመላክት ሲሆን ይህም ማህበረሰቡ ለወንዶች ያለውን የቆየ ልማድና ፍልስፍና ያንጸባርቃል፡፡

ወርድወት ወደ ምሰሶው ተጠግታ ችቦውን ከባሪያው ተቀብላ ወደ ምድጃው በመወርወር ከሶስቱ ጉልቻዎች አንዱን ጉልቻ አንስታ በችቦው ላይ መጫኗ ምሰሶው ተወልዳ ያደገችበት የማህበረሰቡ ወግና ልማድን የወከለ ሲሆን ወርድወት ከባህሉ ጋር የነበራት ቁርኝት እንዳበቃለትና እንደተዳፈነ ያደገችበትንም ባህል እንደጣሰች የሚያመላክት ነው፡፡ ችቦው ደግሞ ሴት ልጅ ለወንድ መገዛት አለባት የሚለውን የማህበረሰቡን ህግ የሚወክል ሲሆንችቦውን ከአሽከሩ እጅ ተቀብላ መወርወሯ ከዚህ በኋላ በዚህ ህግ መተዳደር አለመፈለጓን የሚያመላክት ነው፡፡ ወርድወት ከሶስቱ ጉልቻዎች ውስጥ አንዱን ጉልቻ አንስታ ችቦው ላይ መጫኗ ደግሞ የትዳሯ መፍረስ ምክንያት የሆኑ ባለቤቷ 3 ሚስቶች ያሉት መሆኑ ሲሆን አንዱን ጉልቻ ያነሳችው ባለቤቷ ከሁለቱ ሴቶች ጋር ባህሉ

በሚፈቅድለት ልክ መኖር እንደሚችልና ከሷ ጋርያለው ትዳር ግን እንደተከደነ እንዳበቃለት ለማመልከት ነው፡፡ የልቦለዱ አንዱ ጭብጥም ወርድወት በቃኝ ሴት ልጅ ለወንድ ልጅ ሶስተኛ ሚስት ሆና መኖር ይብቃት የሚል እምቢተኝነት ላይ የተመረኮዘ ነው፡፡ ስለዚህም ደራሲው እነዚህን የመባያ ጉዳዮች በታሪካዊ ልቦለዱ ውስጥ መጠቀሙ አንባቢያን በቀላሉጭብጡን እንዲያገኙ ያግዛቸዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በመፅሃፉ በሌላ ገፅ ላይ ይህ የመባያ ጉዳይ የሆነው "ችቦ" እንዲህ ተገልፆ እናገኘዋለን፡፡

> ጨለማው እየጨከነ ሲመጣ ፣ሰብይፈዝ፣ችቦውን ለኩሶ የተለመደ ስራውን ቀጠለ እሳት የጎረሰ ችቦውን ከፍ አርጎ ይዞ ምሰሶው አጠገብ ቆመ፡፡ ከምሰሶው አጠገብ የሚንቀሳቀሰው እራት ሲቀርብ ብቻ ነው፡፡ እራት ሲቀርብ ችቦውን ይዞ ጀርባውንአዙሮና ለቀረበው ምግብና ተመጋቢዎች አቀብሎ አጠገባቸው ይቆማል፡፡ ችቦውንም ከፍ አድርጎ ይይዝና ተመግበው ሲጨርሱ ደግሞ እንደገና ወደምሰሶው ያመራል...(እምቢታ፣27)(አፅንኦት የራሴ)፡፡

ከላይ ከቀረበው ሃሳብ እንደምንረዳው እሳት የጎረሰው ችቦ በትዕምርትነት የቆመ ሲሆን የሚወክለውም የወርድወትን በሴቶች ላይ በተጣለዉ ህግ እጅግ የመናደድ ስሜት ነዉ፡፡ ምንም እንኳ ወርድወት እጅግ የተከበረች ተወዳጅና በማህበረሰቡ ዘንድ ትልቅ ቦታ የተሰጣት ሴት ብትሆንና በአገልጋዮቿም ብትወደድ ፣ምንም ያክል በባህሉ ቅር ብትሰኝና ብታዝንም አገልጋዮቿ ግን አሁንም ምሰሶው ስር ናቸው በባህሉ ከለላ ስር፡፡ ደራሲው ይህንን ለማመልከት ችቦ አብሪውን ምሰሶው ስር አቁሞ ያሳየናል፡፡

ሌላው በመጽሃፉ ውስጥ ትዕምርታዊነትን በመያዝ ተደጋግሞ በመምጣት የመባያ ጉዳይ የሆነው ቆጮ(እንሰት) ነው፡፡ ይህ ተክል በተለይ በሀገራችን በደቡብ ምዕራብ አካባቢ ተዘውታሪ ምግብ በመሆን የሚያገለግል ሲሆን በጉራጌ ማህበረሰብ ዘንድ ደግሞ ከምግብነት በተጨማሪ ሌላ ትዕምርታዊ ትርጓሜን ሲይዝ ይስተዋላል፡፡ ይህም በመፅሃፉ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

> ከወርድወት ጋር ማን ይዳረቃል? እሷ ማለትኮ ኔያ ናት፣ ጃርት፡፡ ዛሬ እንሰትህን እየበላች የምታስቸግርህን ጃርት ነው በቁም የገደልካት፡፡ ከዚህ በላይ ሰላም ከየት ይመጣል?! ጃርትን እበቀላታለሁ ብለህ ጦርህን ሰብቀህ ወደ ጓሮህ ብትገባኮሽታህን ሰምታ እሾህዋን አስፈንጥራ ልታጠቃህ ትሞክራለች፡፡ ወርድወት ስንት ጊዜ ነው በእሾህ ምላሷ የወጋጋችህ? እንሰትኮ ወንድ ልጅ ነው፡፡ መብልም፣መድሃኒትም፣ጌጥም፣ንጣፍም ነው፡፡ ጃርት ግን ይህን ስለማታውቅ ጨለማ ለብሳ፣ጉድጓድ ቆፍራ፣ የእንሰቱን አምቾ (ሥር) እየቆረጠመች እየቆረጣጠመች ትበላዋለች፡፡ ታነክተዋለች፡፡ አጋዝ! አንተእንሰታችን ነህ ፣ መድሃኒትና ጌጣችንም ነህ፡፡ የእጆካ ሽማግሌዎች ግን

> ወርድወት ጃርት ሆና እንድትበላህና ከስርህ ገዝግዛ እንድትጥልህ አልፈለጉም፡፡ አየህ አዋቂ ሰው እንዲህ ነው የሚፈርደው፡፡…የጃርቷን እሾህ ነቅለህ አትጨርሰውም፡፡ እሾህ ቢያልቅባት ወይም በእርጅና ምክንያት ቢረግፍባት እንደገና ታበቅላለች እንጂ ሌጣዋን አትሆንም፡፡ አየህ አጋዝ ፋርችዬ! ሁሏም ሴት እንደ ጃርትናት፡፡ ወርድወት ብቻ አይደለችም፤እኛ ወንዶች መከላከያችንን ጉልበታችንን፤ እውቀታችንንና ገንዘባችንን ይዘን ስለምንነጥቃቸው ነው እንጂ የሴት ልብ እንደጃርት ነው፡፡ እሾህ ያበቅላል፡፡ እንዴ ከወጉህ መርዝ-በቃ-ተመርዘህ ነው የምትወድቀው!… እርግጥ ነው የወርድወት የባሰ ነው፤ ሰባት ቤት ጉራጌ እንደሷ አይነት አመፀኛ ተወልዶበት ያውቃል?! የለም፤የለም፡፡ አያውቅም…የእጆካ ሽማግሌዎች ከቤትህ እንድትወጣ ባይፈርዱ እንኳን እኛ ያንተ የልብ ወዳጆች ሰበብ ፈልገን ነበር ከቤትህ አስፈንጥረን የምናስወጣት፡፡ ጃርት <u>እንሰት</u> ላይ የምታደርሰው እልቂት ከበዛ ምንድነው የምናደርገው? ተጠራርተን ከተወሸቀችበት ጉድጓድ እንድትወጣ እንነተጉታታለን፤ ጉድጓድ ውስጥ በጪስ ተጨናብሳ እንድትሞት በሚጥሚጣ እናጥናታለን፤ በሙቀት እናፍናታለን፤ በቃ ይሄው ነው፡፡አንተ <u>“እንሰታችን</u> <u>ነህ፤</u> <u>እንሰት</u> ህወታችን ነው፤ቢርበን መብላችን፤ ብንታመም መዳኛችን፡፡ <u>ከእንሰት</u> ጠላቶች መካከልግን አንዷ ጃርት ናት፡፡ ለመኖር ብላ ታጠፋዋለች፤ ትበላዋለች፡፡ ሁላችንም <u>እንሰት</u>ነን የምንል ወንዶች ሁሉ ጃርቷን አቅፈን ነው የምናድረው…”(እምቢታ፤99-100)(አፅንኦት የራሴ)፡፡

የእንሰት ተዋፅኦ (እንሰቱ ተፍቆ የሚገኘዉ ምርት) በፎክሎር ዘርፉ በቁሳዊ ባህል ስር የሚመደብ ሆኖ ሃገረሰባዊ ምግብ ሲሆን በዚህ መፅሃፍ ውስጥ በተደጋጋሚ የተለያዩ ትርጓሜዎችን በመያዝ እንደ መባያ ጉዳይ ሆኖ መጥቷል፡፡ በእርግጥ ከላይ በቀረበው ፅሁፍ ላይ እንሰት ብቻ ሳይሆን “ጃርት” የሚለውም ቃል ተደጋግሞ መጥቷል ነገር ግን የመባያ ጉዳይ ነው ለማለት አያስደፍርም፡፡ ምክንያቱ ደግሞ ይህ ቃል የተገለፀው በዚህች ገፅ ላይ ብቻ በመሆኑና በልቦለዱ በቀሪዎቹ ገፆች ላይ ባለመገኘቱ ነው፡፡ ከላይ ከቀረበው ፅሁፍ ሃሳብ መረዳት እንደሚቻለው “እንሰት” ወንድ ልጅን ወክሎ የቆመ መሆኑን ነው፡፡ ለጉራጌ ማህበረሰብ እንሰት ህልውናቸው ነው፡፡ እንሰት መብል፤ መድሃኒት፤ ጌጥና ንጣፍ እንደሆነና እንሰትን የህይወታቸው አጋዥ፤ ኑሮአቸውን አቅላይና ማንነታቸውን ገላጭ እንደሆነ ሁሉ ወንድ ልጅም ለሴቷ መድሃኒቷ፤መጋቢዋ፤ማጌጫዋና አጠቃላይ ህልውናዋ የተመረኮዘው በወንዱ እጅ እንደሆነና ያለወንድ አጋዥነት ሴት ብቻዋን መኖር አለመቻሏን እንድያውም ለሴት ልጅ ፊት መስጠት እንደሌለባቸውና እንሰታቸውን ከጃርት እንደሚጠብቁ ሁሉ ወንዶች ላይ የሚደርስ በደል እንዳይኖር፤ ሴትን ልጅ ከጓዳ እንዳትወጣ፤የራሷ የሆነ ገንዘብም ሆነ እውቀት እንዳታፈራ በአጠቃላይ ብቻዋን እንዳሻት እንዳትሆን የማድረግ ሃላፊነት የሁሉም ወንዶች መሆኑን ያመላክታል፡፡ የጉራጌ ሽማግሌዎች ወንድነትን ያገዝፋሉ ፤ያለ ወንድ ሃገራቸው መቆም እንደማትችል ያምናሉ፡፡

ፈጣሪያቸው "የቸሃ ዋቅ" እንኳ ለወንድ እንደሚያደላና ከወንድ ትዕዛዝ መውጣትን እንደሚረግምና እንደሚቆጣም ጭምር አምርረው ያምናሉ፡፡ጉልበት ፣እውቀትና ገንዘብ ያለውና የሚኖረውም ሊኖረው የሚገባም ወንድ ልጅ ብቻ ነው ብለው ያምናሉ፡፡ ደራሲው ይህንን የመባያ ጉዳይ በማምጣት የልቦለዱን ጭብጥ አጉልቶ አሳይቶበታል፡፡ ቀጣዩ ደግሞ በልቦለዱ በሌላ ገፅ ላይ የእንሰትን የመባያ ጉዳይነት የሚያሳይ ሃሳብ እንመልከት፡፡

> "ለሃገራችን እንሰት እንሁን ፣እንደ እንሰት እንሁን፡፡ እሷም የሆንላትን ነው የምትሆንልን፡፡ እንሰት ምግብም ፣ ውበትም ፣ መድሃኒትም ነው፡፡እኛ እንሰትን በደንብ ነው የምናውቀው፡፡ ያለ እንሰትህይወት የለንም፡፡ በዕለት ተዕለት ህይወታችን ውስጥ የእንሰት አስተዋፅኦ ቀላል አይደለም፡፡እንሰትንቆጮ ፣ገንፎ ፣ ዳቦ ሆኖ እንበላዋን፡፡እንሰት ግቢያችንን እንዲያሳምርልን ጓሯችንን እንዲያቆነጅ እንተክለዋለን፡፡ እንሰት ብንሰበር አካላችንን እንዲጠግንልን እንመርጠዋለን፡፡ ሰው ብቻ ሳይሆን የቤት እንስሳቱና የዱር አራዊቱ በርሃብ እንዳይጎዱ ያደርጋል፡፡ ግንዱ ደርቆ ሲተለተል ገመድ ሆኖ ቤት ይሰራበታል፣ ቁስ ይታሰርበታል፣ጌጥ ይበጅበታል ፣ምንጣፍም ሰፌድም በእንሰትውጤት ነው የሚሰራው፡፡ እንሰት ህይወታችን ነው፡፡ አክብረነዋል፡፡ የሚገባውን አጉድለንበትም አናውቅም፡፡ ስንተክለውም ስንነቅለውም ተጠንቅቀን ነው፡፡እያንዳንዱ እንሰት ከጨቅላነት እድሜው አንስተን ለእህልነት እስኪበቃ ድረስ ስምንት ዓመት አይደል የሚፈጅበት? በዚህ ሁሉ እድሜው -ህፃን ልጅን አጥንት እንደማናስግጠው ሁሉ-ቡቃያው እንሰትም እንደ እድሜው ነው የምንከባከበው፡፡ እንሰትን እናከብረዋለን፡ ፡ አስከብሮናልም፡፡እኛም ለሃገራችን ልክ እንደ እንሰት አንዳችን ምግብ፣ አንዳችን ውበት፣ አንዳችን መድሃኒት እንሁን፣ ግንዳችንም ፣ ቅጠላችንም ፣ ስራችንም ለሃገራችን የሚጠቅም ይሁን!" አሉ አጋርዝ ዳርሳሞ (እምቢታ፣ 199)(አፅንኦትየራሴ)፡፡

ይህ ፅሁፍ በምርቃት ወቅት የጉራጌ ሽማግሌዎች አንድነታቸውንና ህብረታቸውን ለማጠናከር ብሎም ለሃገራቸው ልክ እንደ እንሰት ጥቅም በተለያየ መስኩ ተሰልፈው አንዱ የሌለውን ሌላው እያሟላ በህብረትና በአንድነት ከሚመጣባቸው ጠላት በሙሉ እንዲታደጓት የሚመርቁበት ነው፡፡ ይህም ወደ ጭብጡ ያመራናል የመፃሃፉ አንዱ ጭብጥ ህብረት ነው የጉራጌ ህዝብ እንዴት ብሎ በህብረትና በአንድነት የሚኒሊክ ጦር ላይ እንደዘመቱበትና ለሸዋ ንጉስ ግብር አንገብርም በማለት በእምቢተኝነት የሸዋ ጦር ሶስት አራት ጊዜ ያህል ወደ ጉራጌዎች ምድር ቢዘምትም በህብረታቸው ሃገራቸውን ሊታደጓት እንደቻሉ የሚነግረን የመፀሃፉ አንዱ ጭብጥ ነው፡፡ ታዲያ ሽማግሌዎች ይህ ህብረታቸውና ሃገራቸውን ለጠላት አሳልፈን አንሰጥም የማለት እንሰትን በምሳሌነት እየጠቀሱ እምቢተኝነታቸው ወደ ልጅ ልጆቻቸውም እንዲሸጋገር ዘወትር በምርቃታቸው መሃል

ያስገቡታል፡፡ ይህም ህብረት ፤አንድነት፤ትብብር የሚለውንና በልቦለዱ ሊተላለፍ የተፈለገውን መልዕክት ለማጎልበት ይረዳል፡፡

በታሪካዊ ልቦለዱ በገፅ 71 ላይ እንዲሁ የመባያ ጉዳይ የሆነው እንሰት በትዕምርትነት እንዲህ ተገልፆ እናገኘዋለን፡፡

> "የመጪው ዘመን ህይወታችሁ የተቃና ብሎም ትዳራችሁ የሰመረ እንዲሆን ታቀርቧቸው ስለነበረ ዜማዎች ትነግሪኝ አልነበረ? በባህሉ መሰረትስ በበዓሉ ማጠናቀቂያ ላይ ወገባችሁ ላይ ያሰራችሁትን ቅጠል ማንም ሳያያችሁ ከጓሮ <u>እንሰት</u> ስር በተማሰ ጉድጓድ ትቀብሩት አልነበር? ወንዶች ቅጠሉን ፈልገው ካገኙት እንደ መልካም ገድ ይቆጠር እንደነበርና አንቺ የደበቅሺው ቅጠል ባለመገኘቱ ራስሽን እንደ እድለኛ በመቆጠርሽ የተሰማሽን ደስታ ነግረሺኝ አልነበር?" ይላል አጋዝ በሚያሳዝን ቃና (እምቢታ፤71) (አፅንኦት የራሴ)፡፡

ከዚህ ሃሳብ የምንረዳው አንሰት አሁንም ምን ያህል የወንዶችን የበላይነት እና ፈላጭ ቆራጭነት እንደሚገለፅበት ነው፡፡ ጉድጓድ ውስጥ የሚቀበረው የሴቶቹ ሚስጥር ሲሆን የመቀበሪያ ቦታው ደግሞ እንሰት ስር መሆኑ በባህሉ መሰረት ከወንዶች የሚደበቅ ምንም አይነት ሚስጥር ሴቷ እንደማይኖራትና ሊኖራትም እንደማይችል፤ ምንጊዜም ሴቷ በወንዱ ስር ሆና መኖር እንዳለባት የሚያመላክት ነው፡፡ ወርድወት የደበቀችው ቅጠል አለመገኘቱ ደግሞ ወርድወት ለወንድ ልጅ በሚወግነውና በተለያዩ ሁኔታዎች ሴቶችን በማያካትተው ባህል ቅሬታ እንዳለባትና በመጨረሻም ከዚህ ባህል ራሷን እንዳላቀቀች የራሷ የሆኑ ሚስጥሮችና የራሷ የሆኑ መብቶቿን ማስከበርና መጠበቅ እንደምትችል በንግር ታሪክ ወደ ፊት የሚከሰተውን ጉዳይ የሚጠቁም ሲሆን ይህም ወደ ልቦለዱ ጭብጥ ይወስደናል ፡፡ የልቦለዱ ጭብጥ የሚያጠነጥነው ወርድወት ከባህሉ አፈንግጣ አንቂቷን አስነስታና ያሻትን መርጣ እንዳሰበችው ሆና እንደምትኖር በመጽሃፉ መቋጫ ላይ የተገለፀ ታሪክ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡

ከላይ ካየናቸው በቃላት ከተገለፁት ትዕምርች በተጨማሪ በልቦለዱ ታሪክ ውስጥ ትዕምርታዊነትን ይዘው ታሪኩን በንግር የሚያስኬዱ ፎክሎራዊ ጉዳዮችም በዚሁ ልቦለድ ውስጥ ይገኛል፡፡ ንግር(ጥቆምታ)፤-ማለት ልቦለድ ከሚቀርብባቸው ዘዴዎች አንዱ ቴክኒክ ሲሆን (ዘሪሁን፤211) እንደሚያስረዱት "ንግር በታሪኩ ሂደት ውስጥ ወደፊት ለሚፈፀም ድርጊት፤አጋርጣሚ፤ወይም ሁኔታ ፍንጭ ወይምጥቆማ የሚሰጥ እንደሆነና በንግር ደራሲው ስለትልሙ አካሄድ፤ ስለግጭቱ ሁኔታ እንዲሁም ስለገፀባህርያቱ ማንነትና በታሪኩ ውስጥ

ስለሚገጥማቸው አብይ ጉዳይ አስቀድሞ ለአንባቢ እውቂያ የሚሰጥበት ቴክኒክ ነው፡፡” በማለት ንግር ወደፊት ለሚሆነው ጉዳይ ጭላንጭል ለማሳየት ልብን ለመስቀል አልያም ልብ ሰቀላን ለማስቀረት የምንጠቀምበትና አንድ ፀሃፊ አበይት የሚባሉ ድርጊቶች ምን ሊሆኑ እንደሚችሉ ፤እንዴት ሊፈፀሙ እንደታሰቡና በማን አማካይት ማን ላይ ምን ሊፈፀም እንደታሰበ በታሪኩ ሂደት አልፎ አልፎ ፍንጭ ማሳየት እንደሚኖርበትም ይናገራሉ፡፡

በእምቢታ ታሪካዊ ልቦለድ ውስጥ በአብዛኛው የሚገኙት ወደፊት በታሪኩ ሂደት የሚፈፀሙ አብይ ጉዳዮች በተለይም ደግሞ ጭብጥ ሊሆኑ የሚችሉና በአብዛኛው ትዕምርታዊነት ያላቸው ሲሆኑ በታሪኩ ሂደት ፍንጭ በመስጠት ረገድ በርካታ ፎክሎራዊ ጉዳዮች አገልግሎት ሰጥተው እናያለን፡፡ ከብዙ በትንሹ ቀጣዮቹን ለማሳያነት እንመልከት

> ችቦውን በግራ አጇ የመመንተፍን ያህል ወሰደችበት፡፡ ደነገጠ እንዲህ አድርጋ አታውቅም፤ እንዲህም አይደረግም ችቦውን የማጥፋት ስልጣን በእጁ ነው፡፡ ማንም አይነጥቀው ወርድወት ግን ችቦውን ተቀብላ ምድጃው ላይ ወርውራ ከሶስት ጉልቻዎች አንዱን አንስታ ችቦው ላይ ጫነችበት፡፡ ጎጆ ቤቱ ጨለመ ምድጃው ላይም ውሃ ቸለሰችበት (እምቢታ፤11-12)፡፡

ገና ከታሪካዊ ልቦለዱ ጅማሬ ላይ የምናገኘው ይህ ሃሳብ ትዕምርታዊነት ያለው ሆኖ በቀጥታ ወደ ጭብጡ የሚመራን ነው፡፡ ደራሲው ወደፊት በታሪኩ ሂደት የወርድወትና የባለቤቷ የአጋዝ ትዳር እንደሚያበቃለት ለመንገር ወርድወት ምድጃው ላይ ውሃ ስትቸልስበት ያሳየናል፡፡ ምድጃ ደግሞ ከላይ በመባያ ጉዳይ ላይ እንዳየነው በማህበረሰቡ ዘንድ ምድጃው ሲሞቅ የትዳር ህይወት የሞቀና የደመቀ በተቃራኒው ደግሞ ምድጃው ሲቀዘቅዝና ሲጠፋ ትዳሩም አብሮ እንደሚጠፋ ለመግለጽ በውክልና የቆመ መሆኑን ተመልክተናል፡፡በዚህም መሰረት ይህ ንግር የወርድወት ትዳር ወደፊት እንደማይቀጥል የሚያመላክት ሲሆንወርድወት ከሶስቱ ጉልቻዎች ውስጥ አንዱን አንስታ ችቦው ላይ መጫኗም በተመሳሳይ ችቦ ሴትን ወክሎ የቆመ እንደመሆኑ ሁሉ አጋዝ ባህሉ በፈቀደለት መሰረት ሶስት ሚስቶች ያሉት ሲሆንከሁለቱ ጋርእንደፈለገው መሆን ቢችልም ከሶስተኛዋ ከወርድወት ጋርግን ከዚህ በኋላ መቀጠል እንደማይችል ያደረገችው መሆኑን ለመንገር የቀረበ ነው፡፡ከዚህ በመነሳት የማህበረሰቡ ፍልስፍናና እምነት የሚንፀባረቅባቸው ፎክሎራዊ ጉዳዮች እንደ ንግር(ጥቆምታ) በመሆን አንባቢው ከወዲሁ ከታሪኩ ምን ሊጠብቅ

እንደሚችልና የታሪኩ ሂደት ምን ሊመስል እንደሚችል እንዲገምት እድል ፈጥረውለታል፡
፡

# ምዕራፍ አምስት

## 5.1 ማጠቃለያና ይሁንታ

### 5.1.1 ማጠቃለያ

በዚህ ጥናት *በመኤኒትና በእምቢታ* ታሪካዊ ልቦለዶች ውስጥ ልቦለዱ የተከየኑባቸውን ፍክሎራዊ ጉዳዮች መዞ በማውጣት ለልቦለዶቹ ያበረከቱትን ፋይዳ ለማሳየት ተሞክሯል፡፡ እነዚህ ሁለት ስራዎች የቅርብ ጊዜ ህትመት በመሆናቸውና በስራዎቹ ላይ ይህ ነው የሚባል ረብ ያለው ሥነ-ፅሁፋዊ ሂስ ተሰጥቶባቸውያልታዩ ሲሆን ልቦለዶቹ ባህልንና ታሪክን ቀርሰው የማስቀረት ሃይል ያላቸው ሆነው ተገኝተዋል፡፡ወጥ ልቦለዶች እያነሡ፤ የትርጉም ሥራዎች ቦታችንን እየወሰዱ ባሉበት ዘመን የራሳችንን ታሪክ መልሰን እንድናይ የሚያደርጉ እንዲህ ያለውን ሥራ ማግኘት ለሥነ ጽሑፋችን አንድ እመርታ ነው፡፡

ጥናቱ አይነታዊ ሲሆን በአላማ ተኮር የንሞና ዘዴ ተመርጦ ከ Intertexuality የመተንተኛ ንድፈ ሃሳብ አንፃር ተተንትኖ የቀረበ ሲሆን የጥናቱን አካሄድ በተመለከተ አለን ደንደስ ፎክሎር በሥነ-ጽሁፍ ውስጥ ሲጠና የመለየትና የመፈከር ሁለት ደረጃዎችን ሊከተል ይገባል በማለት ያስቀመጠውን መርህ የተከተለ ነው፡፡ በመሆኑም በሁለቱም ልቦለዶች ውስጥ የሚገኙ አጠቃላይ ፎክሎራዊ ጉዳዮች ተለይተው የወጡ ሲሆን በዋናነት የስነቃል ፣ የሀገረሰባዊ ልማድ እና የቁሳዊ ባህል ምድቦች በሁለቱም ስራዎች ውስጥ በስፋት ተገኝተዋል፡፡

በሁለቱም ስራዎች ውስጥ የሚገኙት ፎክሎራዊ ጉዳዮች የራሳቸው የሆነ አንዳች ፋይዳ ያላቸው ሲሆን የሥነ-ቃል ምድብ የሆኑት ቃል ግጥሞች የታሪክ ገፀባህርያትን ማንነት ከማሳየት አንፃር ጉልህ ድርሻን አበርክተዋል፡፡ በልቦለዶቹ ውስጥ የሚገኙት ቁሳዊ ባህሎች ደግሞ በዘመኑ የነበረውን አጠቃላይ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ባህላዊ የደረጃ ልዩነት በመግለጽ ረገድ ከፍተኛ ሚና እንደነበራቸው የጥናቱ ውጤት ያመላክታል፡፡

በተጨማሪም *በእምቢታ* ታሪካዊ ልቦለድ ውስጥ የሚገኙ ፎክሎራዊ ጉዳዮቹ ትዕምርታዊ ፍቺን በመያዝ እንደ መባያ ጉዳይ ሆነው ሲመጡ ተስተውለዋል፡፡ እነዚህ የመባያ ጉዳዮች ደግሞ የማህበረሰቡ ፍልስፍና፣ አመለካከት፣ እምነትና ባህል ውጤት የሆኑና ማህበረሰቡ

እነዚህን ጉዳዮች በቁሳዊ ባህሎቹ የሚወክልበት ሁኔታም እንዳለ ፤ እነዚህ የመባያ ጉዳዮች የልቦለዱን ጭብጥ ከማመላከት አንፃር አስተዋፅኦ እንዳደረጉም ከጥናቱ ለማወቅ ተችሏል፡፡

በሁለቱም ስራዎች ውስጥ የሚገኙ የፎክሎር ዘርፍ የሆኑ የሥነ-ቃል ምድቦች እንደ እርግማን ፤ ምሳሌያዊና ፈሊጣዊ አነጋገሮች ፤ ፉከራና ቀረርቶዎች በልቦለዶቹ ውስጥ የተፈጠረውን ግጭት ከማክረር (ከማናር) አንፃር ከፍተኛውን ሚና የተጫወቱ ሲሆን በተለይ በመኤኒት ልቦለድ ውስጥ የሃገረሰባዊ ልማድ ምድብ የሆኑ ሃገረሰባዊ እምነቶች በልቦለዱ ውስጥ ጫፍ የወጣን ግጭት በማብረድ በምትኩ ሰላምና መረጋጋት እንዲሰፍን ይህንንም ተከትሎ አንባቢዉ ፋታ እንዲያገኝና የልብ ሰቀላዉም አብሮ እንዲረግብ ከማድረግና ፅሁፉ ፍሰቱን ጠብቆ ሳይሰለች እንዲጓዝ ከማድረግ አንፃር ከፍተኛውን ግልጋሎት እንደሰጡና *በእምቢታ* ታሪካዊ ልቦለድ ውስጥ ደግሞ የስነቃል ምድብ የሆነው ምርቃት በተመሳሳይ መልኩ ግጭትን ለማብረድ እንዴት አገልግሎት ላይ እንደዋሉና እነዚህ ፎክሎራዊ ጉዳዮች የልቦለዱን የአፃፃፍ ቴክኒክ ከማጎልበት አንፃር ጉልህ ድርሻ እንዳላቸው በጥናቱ ተመላክቷል፡፡

በአጠቃላይ በጥናቱ ፎክሎርና ሥነፅሁፍ በእጅጉ የተሳሰሩ የሙያ ዘርፎች እንደሆኑና የልቦለዶቹ ደራሲያን እነዚህን ፎክሎራዊ ጉዳዮች በስራዎቻቸው ውስጥ መጠቀማቸው ቋንቋው ቀላልና በየትኛውም የእውቀት ደረጃ ላይ የሚገኝ አንባቢ ታሪኩን በቀላሉ እንዲረዳው ከማገዙም በላይ እያንዳንዱ አንባቢ ከማያውቀው አዲስ ማንነት ፣ ወግና ባህል ጋርእንዲተዋወቅ የሚያስችል መሆኑ በጥናቱ ለማወቅ ተችሏል፡፡

በመጨረሻም ደራሲያኑ እነዚህን ፎክሎራዊ ጉዳዮች በድርሰታቸው ውስጥ እንዲህ አጉልተው መጠቀማቸው በአጋጣሚ የሆነ ሳይሆን ሆን ብለውና ለዘርፉ ካላቸው ቅርበት አንፃር በፎክሎርና በሥነ-ጽሁፍ መካከል ያለውን ጥብቅ ቁርኝት ለማሳየት ከመፈለግ እንደሆነ ለመገመት ተችሏል፡፡ ይህም በፎክሎርና በስነፅሁፍ መካከል ያለዉን የጋራ ወሰን ለማመላከት ያደረጉት ጥረት ለጥናቱ ጥንካሬን ፈጥሯል፡፡

### 5.1.2 ይሁንታ

የተለያዩ የፎክሎር ዘርፎች በተለይም ሥነ-ቃሎች ትውልድን በስነምግባር ከማነፅ አንፃር አስተዋጽኦ የሚያደርጉ ሲሆን Bascom (1954) የአፍሪካ ምሳሌያዊ አነጋገሮች የማህበረሰቡን ስነ-ምግባር እና ማህበራዊ እንቅስቃሴዎችን በመቆጣጠር ውጤታማ

መሆናቸውን ይገልፃል፡፡ከዚህ አንፃር ደራሲያን በልቦለድ ስራዎቻቸው ውስጥ እነዚህንና መሰል የሥነቃል ዘርፎችን በተለያየ ጊዜ ወደ ህዝቡ በሚደርሱ የህትመት ስራዎቻቸው ውስጥ ማካተት ቢችሉ ሥነ-ቃሎቹ ከወግ ባህሎቻችን እንዳንወጣ የሚያስተምሩ፣ የሚመክሩና፣ የሚቆጣጠሩ እንደመሆናቸው በተለይ ወጣቶችን በስነምግባር ለማረቅ ጉልህ ድርሻ ስለሚኖራቸው ደራሲያን እዚህ ላይ አጠንክረው ቢሰሩበት፡፡

ፎክሎር ከቋንቋ ከትምህርት ጋርያለው ዝምድና ላቅ ያለ ነው፡፡ ፈቃደ(1991) ሥነቃል በትምህርት መስክ ከቋንቋ ጋርብቻ ሳይሆን በሌሎችም የማህበራዊና የተፈጥሮ ሳይንስ መስኮችም ጭምር ተካቶ ሊሰጥ እንደሚገባ ያስረዳሉ፡፡ በተለይ እንደ ኢትዮጵያ ባሉ የዳበረ ሥነቃላዊ ሃብት ባላቸው ሃገሮች የህብረተሰቡ ልዩ ልዩ የህይወት መልኮች፤ ለነገሮች ያላቸው አተያይ፤ በአጠቃላይ ማንነቱን የሚያንጸባርቅበት በአንድ ተሸክፎ የሚገኝበት በቀላሉ ጠልቀው የማይዘልቁት ምንጭ የሆኑ የሥነ-ቃል ሃብቶቻችን ህፃናት ብስለታቸው ተጠብቆ ከመዋዕለ ህፃናት እስከ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በደረጃ ሊጠቀሙበት ይችላሉ፡፡ በመሆኑም የሚመለከታቸው አካላት ተማሪዎቹ የፈለቁበትን ወግና ባህል የሚያንጸባርቁ ፎክሎራዊ ጉዳዮችን እንዲህ በሥነ-ፅሁፍ ስራዎች ውስጥ እያዋዙ በማቅረብ ለማስተማሪያ መሳሪያነት ቢጠቀሙበት ፡፡

ፎክሎር በባህሪውበቦታ፣ በጊዜና በመከወኛ አጋጣሚው ተለዋዋጭ በመሆኑ በአንድ አጋጣሚ ያገኘነውን የአንድ ማህበረሰብ የማንነት መገለጫ የሆነ ወግ፤ታሪክና ባህል በሌላ ጊዜ ስናገኘው ተበርዞና ተከልሶ አልያም ከነአካቴው ጠፍቶ ልናገኘው ስለምንችል በተለያዩ ጊዜያት ወደ ሰው በሚደርሱ የህትመት ስራዎች ውስጥ ማካተቱ ከዚህና መሰል አደጋ ሊታደገው ስለሚችል ባለድርሻ አካላት ርብርብ ቢያደርጉ ፡፡

የአንድ ማህበረሰብ አጠቃላይ ባህል በመሰል ሥነ-ፅሁፋዊ ስራዎች ውስጥ መካተቱ ምንአልባትም ስራዎቹ በዓለም ቋንቋ ተተርጉመው የሚሰራጩበት አጋጣሚ ቢኖር የዚያ ማህበረሰብ ወግና ባህል በዓለም ደረጃ ከመታወቁ ጋርተያይዞ በርካታ ጎብኚዎች ወደ ስፍራው እንዲመጡ ሊያደርግና ከቱሪዝሙ መንደር ከፍተኛ የሆነ ገቢን ሊያስገኝ ስለሚችል የሚመለከታቸው አካላት ለባህሉ መጠበቅ ክትትልና ድጋፍ እንዲያደርጉ ያስችላቸዋል፡፡ ሰው የሚያውቀውን ሲያቀርብ፣ የሚያቀርበውንም ሲያውቅ ደስ ይላል፡፡ የኖረበትን፣ የተሠራበትንና የተዋሐደውን ነገር ሲተርክ ከውስጡ ስለሚመነጭ ከዛፍ ሥር የሚፈልቅን ውኃ እንደመጠጣት ይቆጠራል፡፡ በመሆኑም ደራሲያን የትርጉም ስራ ላይ

ከማተኮር ይልቅ የሃገራችንን ተዝቆ የማያልቁ ባህላዊ እሴቶቻችን ላይ ትኩረት አድርገው በተለያዩ ሥነ-ፅሁፋዊ ስራዎቻቸው ውስጥ እያካተቱ ለህዝቡ ቢያደርሱ ፅሁፋቸው በቴክኒክ የጠነከረ ከመሆኑም በላይ ማህበረሰቡ ማንነቴ የሚለው ታሪክ ተፅፎለት በማግኘቱ የአንባቢያንን ቁጥር ከፍ ሊያደርግ ይችላል፡፡

# ዋቢዎች


ሊዲያ ተካ፡፡ (2005) ፡፡ "ፎክሎር በጫሙት ሸካ እና በተኬነት-አጃነት አንኪ የጉራጊኛ ልቦለዶች ከማንነት ፅንሰ ሃሳብ አንፃር፡፡"ለኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፤አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡ (ያልታተመ)

ሰለሞን ተሾመ፡፡ (2007)፡፡ ፎክሎር ምንነቱና የጥናቱ የትኩረት አቅጣጫ ፡፡ አዲስ አበባ፤ ፋሪኢስት ትሬዲንግ ኃላ.የተ.የግ.ማ፡፡

ታደሰ ሺበሺ፡፡ (2005)፡፡ "ሚቶሎጂያዊ ጥናት እቴሜቴ ሎሚ ሽታ እና ይወስዳል መንገድ ያመጣል መንገድ በተሰኙ የአዳም ረታ መድበሎች"፡፡ ለኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፤አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡ (ያልታተመ)

ቴዎድሮስ ገብሬ፡፡ (2001)፡፡ በይነ-ዲሲፒሊናዊ የስነ-ፅሁፍ ንባብ፤አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ፕሬስ፡፡

አንዷለም አባተ፡፡ (2005) መኤኒት ልቦለድ፡፡ አዲስ አበባ፤ኤች ዋይ ኢንተርናሽናል ፕሪንትስ

አዳነች አበራ፡፡ (2001) ፡፡ "የፎክሎር ቅርፅና ፋይዳ በተመረጡ የታሪክ መፃህፍትና ዜና መዋሎች ውስጥ"፡፡ ለኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፤አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡(ያልታተመ)

አገኘሁ አዳነ፡፡ (2007) "ሥዕል፣ ሠዓሊነት እና ሠዓሊ ገጸባሕርያት በተመረጡ የአማርኛ ዘመናዊ ልብ ወለዶች ውስጥ"፡፡ ለኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡(ያልታተመ)

እንዳለጌታ ከበደ ፡፡ (1996)፡፡እምቢታ ታሪካዊና ፎክሎራዊ ልቦለድ፡፡ አዲስ አበባ፤ አታፍዘር አሳታሚዎች፡

ወሰንባዩ፡፡ (2010) ፡፡ "በኢትዮጵያ ቴአትር የተነሱ ፎክሎራዊ ጉዳዮች ፋይዳ በተመረጡ ተውኔቶች ማሳያነት"፡፡ ለኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ለፒ. ኤች.ዲ ማሟያ የቀረበ ጥናት፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡ (ያልታተመ)

ዘሪሁን አስፋው፡፡ (1992)፡፡ የስነ ጽሁፍ መሰረታውያን፡፡ አዲስ አበባ፤ ንግድ ማተሚያ ቤት፡፡

ያለውእንዳወቅ፡፡ (1998)፡፡ የምርምር መሰረታዊ መርሆዎችና አተገባበር፡፡ማተሚያ ቤቱ አልተገለፀም፤ ባህርዳር

ፈቃደ አዘዘ፡፡ (1986)፡፡ ትውፊት በስነ-ፅሁፍ ውስጥ፡፡ የኢትዮጲያ ቋንቋዎችና ሥነ-ፅሁፍ፡፡ ቁጥር3፣ ከገፅ 1-19፡፡

ፈቃደ አዘዘ፡፡ (1991)፡፡ የስነ ቃል መምሪያ፡፡ ኢንተርናሽናል ጀርመናዊ

የጎልማሶች ትምህርት ተቋም፡፡

Allen, G. (2000). Intertextuality, Routledge, Taylor and Francis Group, London.

Bascom, William R. (1954). "Four Functions of Folklore".The Journal of

American Folklore.Vol.67, No. 266. American Folklore Society.

Ben-Amos, D. (1971) Toward A Definition of folklore in Context the Journal of

American Folklore,

(1975). Folklore in Africa Society Research in Africa Literature.

(1979). Toward definition of Folklore in context. The Journal of

American Folklore, Vol. 84,No.331

Dundes, Alan. (1965)The Study of Folklor.Englewood Cliffs;prentice-Hall.

Finegan, Ruth. 1970. *Oral Literature in Africa*. Oxford: Clarendon Press.

Goldstein, Kenneth S, (1964). A Guide for Field Works in Folklore. Pennsylvania,
Folklore Associates Inc.

Jani austen,(1992), Criticism in Focus. NewYork, NY: St. Martin's
Press,

Judith Still and Michael Worton,(1990) page 1-44 'Introduction' in Intertextuality:

Theories and Practices, edited by Michael Worton and Judith Still

(Manchester, Manchester University Press,

Lehner.E(1950) motives.themes and symbol, new york Routledge,

Pearl Amelia McHaney, (2008)pp.166-181.History and Intertextuality: ATransnational Reading

of Eudora Welty's "Losing Battles" and Sindiwe MagonaThe Southern Literary Journal, Vol. 40, No. 2, Special Issue:

Rose De Angelis (2002). Between anthropology and litrature: interdisciplinary discourse London; New York: Routledge,

Tolken, barre. 1996. Dynamics of Folklor.logan; Utha University press

Wellek, Rene and Austen Warren. (1980). Theory of Literature. London; PelicanBooks,

William A Wilson, (1980) "Documenting Folklore". Folk Groups and Folklore Genres: An Introduction (ed) Oring. Utah State University Press, USA

,